# በአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ዙሪያ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት የተዘጋጀ ፅሁፍ

**የኢትዮጵያ የምግብ፣የመድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን**

*ህዳር 2004 ዓም*
*አዲስ አበባ*

**ማውጫ** **ገፅ**


መግቢያ ..........................................................................................5

ክፍል አንድ

የአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ምንነት፣ ችግሮችና ያለአግባብ አጠቃቀም ምክንያቶች.....7

ምዕራፍ አንድ

አደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ..........................................................................8

ሀ. ናርኮቲክ መድሀኒቶችና እፆች----------------------------------------------------------8

1. ኦፒየም ተክልና ዝርያዎቹ (Opium)..............................................................8
2. ኮካ ተክልና ዝርያዎቹ (Coca).....................................................................11
3. ካናቢስ ተክልና ዝርያዎቹ (Cannabis) .........................................................14

ለ.የሣይኮትሮፒክ መድኃኒቶች’ ....................................................................17

ምዕራፍ ሁለት

ማህበራዊ አደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ...........................................................20

ሀ.የአልኮል መጠጦች’........................................................................................20
ለ. ጫት ...........................................................................................................24
ሐ.ትምባሆ........................................................................................................28
መ. የሚሸተቱ ኬሚካሎች (Inhalants)................................................................31

ምዕራፍ ሶስት
በአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ምክንያት የሚደርስ ፆታዊ ጥቃት................................35

ምዕራፍ አራት
አደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች በኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ ኑሮና በፖለቲካ ላይ
የሚያደርሱት ችግር’ .......................................................................................40

ሀ. በኢኮኖሚ ላይ የሚያደርሰው ጉዳት፣ ..............................................................40
ለ. በማህበራዊ ኑሮ ላይ የሚከሰት ችግር፣...........................................................42
ሐ. በፖለቲካ መረጋጋት ላይ የሚፈጠር ችግር፣ ...................................................43

ምዕራፍ አምስት
ሰዎች ለምን አደገኛ መድኃኒቶችንና ዕፆችን ይጠቀማሉ?......................................45

ምዕራፍ ስድስት
አደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ከኤች አይ ቪ/ኤድስ ጋር ያላቸው ቁርኝት ....................49

ክፍል ሁለት
የአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ህገ ወጥ ዝውውርና አጠቃቀምን የመከላከልና የመቆጣጠር ስልቶች

ምዕራፍ አንድ

ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና ድንጋጌዎች' ...............................................................58

ሀ.እ.ኤ.አ. በ1961 የወጣው የናርኮቲክ መድኃኒቶች ስምምነት'...............................59
ለ.እ.ኤ.አ. በ1972 የወጣውና የ1961 የናርኮቲክ ስምምነትን ያሻሻለው ፕሮቶኮል'.....60
ሐ.እ.ኤ.አ. በ1971 የወጣው የሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ስምምነት' ........................60
መ.እ.ኤ.አ. በ1988 የወጣው የናርኮቲክና የሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ህገ ወጥ ዝውውርን ለመግታት የወጣው ስምምነት'-----------------------------------------------61
ሠ.የትምባሆ ዝግጅቶችን ለመቆጣጠር የወጣ አለማቀፍ ድንጋጌ........................62
ረ.የተ.መ.ድ. አባል አገራት ህጎች......................................................................63

ምዕራፍ ሁለት

የአገራችን ህጎች...........................................................................................64

1. ስለናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶችና ዕፆች ህገወጥ አመራረት፣ዝውውርና አጠቃቀም66
2. ስለ አልኮል መጠጦች .......................................................................................... 72
3. ከአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ህገወጥ አጠቃቀምና ንግድ ጋር በተያያዘ ስለሚፈፀሙ ተጓዳኝ ወንጀሎች ........................................................................... 75
4. የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 661/2002 .......................................................................... 80

ምዕራፍ ሶስት

የአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ቁጥጥር ተግባር-------------------------------82

ሀ.ቅንጅታዊ አሠራርን ማዳበር'.......................................................................... 83
ለ.የፍተሻ ተግባር ማጠናከር' ............................................................................ 84
ሐ.ምንጩን ማድረቅ'....................................................................................... 85

## ምዕራፍ አራት


ስለአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ህገወጥ ዝውውርና አጠቃቀም ማስተማር-86

ሀ.መረጃ የማሰራጨት ሥራ'........................................................................ 87
ለ.በመደበኛ ስርዓተ ትምህርት የሚሰጠው ትምህርት'.............................................. 89
ሐየህብረተሰብ ተሳትፎ' ........................................................................................ 91


## ምዕራፍ አምስት


ህክምናና መልሶ ማቋቋም----------------------------------------------------94

ሀ. ህክምና'............................................................................................................ 94
ለ. መልሶ ማቋቋም' .................................................................................... 95

## 1. መግቢያ

የሰው ልጅ ታሪክ ከአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች አመጣጥና ታሪክ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ከብዙ ዓመታት በፊት የሰው ልጅ እፅዋት፣ ሥራ ሥር፣ ቅጠላ ቅጠል፣ ማዕድናትና የመሳሰሉትን ስቃይን ለማስታገስ ይጠቀም እንደነበረ የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ፡፡ ለዚሁ አገልግሎት ሲባል ይጠቀምባቸው የነበሩት አንዳንድ የባሕል መድኃኒቶች ሱስ የማስያዝ፣ ለጥቂት ጊዜ የሚቆይ የማነቃቃት፣ የማስፈንጠዝና የማስከር ባሕሪ እንደነበራቸው ይነገራል፡፡ ይህ ባሕሪ ያላቸው የባሕል መድኃኒቶች ከጥቅማቸው ይልቅ ጉዳታቸው እያመዘነ መምጣቱን አንዳንድ ጽሑፎች ይገልፃሉ፡፡ ይህም በመሆኑ የባሕል መድኃኒቶችና ሕክምና አዋቂዎች የተለየ ጥንቃቄ ያደርጉ እንደነበር መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡

የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ሕገወጥ ዝውውርና አጠቃቀም ከረጅም ዓመታት በፊት የነበረ ቢሆንም ችግሩ በከፍተኛ ደረጃ የተዛመተው ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ነው፡፡ ካለፉት ሁለት አሥርት አመታት ወዲህ የመድኃኒቶቹና እጾቹ አጠቃቀም ከጊዜ ወደ ጊዜ እንደወረርሽኝ በመዛመት አገሮችን ሊያዳርስ ችሏል፡፡ ለዚህም ዋናው ምክንያት አገሮች ለችግሩ ተገቢውን ትኩረት ባለመስጠታቸውና አንዳንዶቹ ደግሞ ከአቅማቸው በላይ በመሆኑ ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ከአገር ወደ አገር እንቅስቃሴ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ተስፋፍቶ ይገኛል፡፡ አንድ አካባቢ በሚበቅለው እጽ ወይም የሚፈበረከው መድኃኒት በአጭር ጊዜ ሌላው አካባቢ ይደርሳል፡፡ ዘመናዊ የመጓጓዣ ዘዴዎች ለዚሁ ሕገወጥ ተግባር ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡ ሌላው የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ሕገወጥ ተጠቃሚዎች ቁጥር እያደገ መጥቷል፡፡ ይህም ቢሆን የነዚህ መድኃኒቶችና እጾች ሕገወጥ አጠቃቀም በጤና፣ በማህበራዊ ኑሮ፣ በኢኮኖሚና በፖለቲካ መረጋጋት ላይ የሚያስከትሉት ችግር ተጠቃሚው እንዲያውቃቸው ባለመደረጉ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡

አደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች በሰው ልጅ አዕምሮ ላይ በመሥራት ላይ የሚታወቁ ሲሆኑ፣ እነሱም በዓለም አቀፍ ደረጃ ቁጥጥር የሚደረግባቸው የናርኮቲክና ሣይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ናቸው፡፡ እንዲሁም ቁጥጥር የማይደረግባቸውን እንደ ትምባሆ፣ ጫት፣ አልኮሆልና የሚሸተቱ ኬሚካሎችን የሚያካትት ነው፡፡

በአገራችንም የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ሕገወጥ ዝውውርና አጠቃቀም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል፡፡ በተለይም ወጣቱ ክፍል የነዚህ መድኃኒቶችና እጾች አለአግባብ ተጠቃሚ መሆን ከጀመረ ውሎ አድሯል፡፡ ሁኔታው ከወዲሁ ካልተቀጨ ከፍተኛ የሆነ ችግር ሊከሰት እንደሚችል ጥርጥር የለውም፡፡ ለዚህም አስፈላጊውን የመከላከል ጥረት ማድረግ ወሣኝ ነው፡፡

የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ሕገወጥ ዝውውርና አጠቃቀም አስከፊ ገጽታን ለመከላከል ትምህርት ዓይነተኛ መሳሪያ ነው፡፡ የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን ይህን መርህ ዕውን ለማድረግ ለተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ስለ ሱሰኝነት አስከፊ ገጽታ የሚያስተጋቡ ሴሚናሮችና ዓውደጥቶች በማዘጋጀት ሲያስተምር ቆይቷል፡፡ እንዲሁም የተለያዩ በራሪ ጽሑፎችና ፖስተሮች በማዘጋጀት ለሕብረተሰቡ አሰራጭቷል፡፡

የማስተማሩ ተግባር በተጠናከረ መልኩ እንዲቀጥል ለማድረግና የህዝብ ተወካዮች ምክርቤት አባላት በአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ዙሪያ ያላቸው ግንዛቤ እንዲጨምር በማድረግ በዚህ ዙሪያ ህጎችንና ደንቦችን እንዲያወጡና እንያፀድቁ ከዚህ በተጨማም በማስተማር መስክ የተሰማሩ ባለሙያዎች እንዲጠቀሙበት ይህንን ፅሁፍ ማዘጋጀት አስፈልጓል፡፡ ፅሁፉን በመጠቀም የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ለማስተማርና የባሕሪ ለውጥ ለማምጣት እንደሚረዳ አስፈላጊነቱ አያጠያይቅም፡፡

ፅሁፉ አስፈላጊ የሆኑና የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ሕገወጥ ዝውውርና አጠቃቀም አስከፊ ገጽታን ለማስተጋባት የሚያስችሉ ርዕሶች ይዟል፡፡ ማንኛውም የፅሁፉ ተጠቃሚ በፅሁፉ ውስጥ የተጠቃለሉ ርዕሶችን በማንበብ አስፈላጊውን ትምህርት ለመስጠት ይችላል ብሎ የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን ያምናል፡፡

# ክፍል አንድ

# የአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ምንነት፣ ችግሮችና ያለአግባብ አጠቃቀም ምክንያቶች

# ምዕራፍ አንድ
# አደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች

በዓለም አቀፍ ደረጃ ቁጥራቸው ከመቶ በላይ የሚደርሱ የናርኮቲክ መድኃኒቶችና እጾች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ሲሆን ከነዚህም ውስጥ የተወሰኑት በስፋት አለአግባብ ጥቅም ላይ ስለሚውሉ ችግሮች እያደረሱ ይገኛሉ:: በዚህ ርዕስ ከፍተኛ ችግር በማድረስ ላይ የሚገኙት የናርኮቲክ መድኃኒቶች ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርበዋል::

## 1. የኦፒየም ተክልና ዝርያዎቹ (Opium)

ኦፒየም የሚባለው አደገኛ ዕጽ በደቡብ ምስራቅና ደቡብ ምዕራብ ኢስያ በሚገኙ አገሮች ማለትም:-

- ወርቃማው ትሪያንግል (Golden Triangle) ተብሎ በሚታወቀው አካባቢ በሚገኙ በርማ /ሚያሚር/፣ ላኦስና ታይላንድ፣
- ወርቃማው ክረሰንት (Golden Crescent) ተብሎ በሚታወቀው አካባቢ በሚገኙ ፓኪስታን፣ ኢራንና አፍጋኒስታን በተባሉ አገሮች በስፋት የሚበቅል ሲሆን እንዲሁም በህንድ፣ ቱርክና ሌሎች የእስያ አገሮችም ይበቅላል::
- ኦፒየም Temperate እና Substropical የአየር ፀባይ ባላቸው አካባቢዎች ሊበቅል ይችላል:: (Temperate Zone የሚባለው ከምድር ወገብ North – South ከ$45^o$ – $66^o$ ያለው ሲሆን ፣Sustropical የሚባለው ደገሞ ከምድር ወገብ North – South ከ$23^o$ – $45^o$ ያለው ነው::

ኦፒየም በምስራቃዊ ሜዲትራያን በሚገኘው የዓለም ክፍል ከ5000 ዓመት በፊት ለሕክምና አገልግሎት ይውል እንደነበር በታሪክ መፃሕፍት ተጠቅሷል:: ከጊዜ በኋላም ዕጹም ሆነ "የሕክምናው ጥቅም" ወደ ግብፅ፣

ፐርሺያ፣ ቻይናና አውሮፓ ተስፋፍቷል። በነዚህ አገሮችም ውስጥ የነበሩ ማሕበረሰቦች ዕጹን ለብዙ ዓይነት በሽታዎች እንደፈዋሽ መድኃኒት ሲጠቀሙበት ቆይተዋል፣ አሁንም በአንዳንድ የእስያ ሀገሮች ጥቅም ላይ ይውላል።



ኦፒየም ተክል



ሞርፊን



ሄሮይን

የኦፒየም ተክል አካል የሆነውና ካፕሱል የሚባለው እንቡጥ ከመፈንዳቱ በፊት በስለት በሚበጣበት ጊዜ ነጭ ወይም ቡናማ ቀለም ያለው ወፍራም ፈሳሽ ይወጣና ወዲያው ይደርቃል:: በዚህ የሚያጣብቅ ፈሳሽ ውስጥ የተለያዩ ንጥረ ነገሮች /ኬሚካሎች/ ይገኛሉ:: ከነዚህም ውስጥ ሞርፊን (Morphine) የተባለው ዋናው ሱስ የማስያዝ ባህርይ ያለው ነው:: ከሞርፊን በተጨማሪ ኮዴይን (Codeine) የተባለ ሌላ አነስተኛ ሱስ የማስያዝ ባህሪ ያለው ኬሚካልም ይገኛል::

በሣይንሣዊ መድኃኒት ቅመማ ዘዴ (Drug Synthesis) ሌሎች እንደ **ፔቲዲን፣ ሜታዶን፣ ሄሮይን ...** ወዘተ ከኦፒየም ሊሠሩ ችለዋል:: ፔቲዲንና ሜታዶን የሕክምና ጥቅም ያላቸው ናቸው:: ሄሮይን ግን ከፍተኛ ሱስ የማስያዝ ባሕርይ ስላለው ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ስለሚያመዝን ሕጋዊ ጠቀሜታ የለውም:: በመሆኑም ሄሮይን በሚፈጥረው ከፍተኛ ሱስ የማስያዝ ባህርይ ሣቢያ ለሕገወጥ ጥቅም በድብቅ በመላው ዓለም በመዘዋወር በሚልዮን በሚቆጠሩ ሰዎች ላይ ከባድ ጉዳት በማድረስ ላይ ይገኛል::

ኦፒየምና ከላይ የተዘረዘሩት ውጤቶቹ አለአግባብ አጠቃቀም በመርፌ፣ በእንክብል፣ በሲጋራ መልክና በሱረት ይወሰዳሉ:: ለሕጋዊ አገልግሎት በሕክምና ዓለም በመርፌ፣ በእንክብል፣ በሲራኘና በመሳሰሉት ይሰጣል::

## በጤና ላይ የሚያደርሰው ጉዳት፣

ቀደም ብሎ እንደተገለፀው አንዳንድ የኦፒየም ውጤቶች በሕክምናው ዓለም ከፍተኛ ስቃይን በማስታገስ ረገድ የሚሰጡት ጥቅም ወደር የለውም:: ከዚሁ ጎን ሱስ የማስያዝ ባሕሪያቸው ከፍተኛ ነው:: ጊዜያዊ የደስታ (Euphoria) ስሜት የሚፈጥሩ በመሆናቸው ሰዎች ደጋግመው በሚወስዱበት ጊዜ የሱስ ተገዢ ስለሚሆኑ ለተለያዩ ዓይነት የጤና ችግሮች ይጋለጣሉ:: ከነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ፣

- የደስታ ስሜትን ሁልጊዜ ለማግኘት ሲባል ተደጋግመው ስለሚወስዱ በየጊዜው መጠን መጨመርን አስፈላጊ ያደርገዋል፣ በመሆኑም የደስታ ስሜቱን እየተከተሉ ከሚገባው በላይ መጠን መጨመር ስለሚያስከትል በዚህ ሣቢያ፣ የሰውነት መንዝ ፍዘፍ፣ ራስን መሣትና መጨረሻም ለሞት ሊዳርጉ ይችላሉ::

- የአእምሮ መናወጥ ስለሚያስከትሉ ለአእምሮ ሕመም ይዳርጋሉ፣ የማመዛዘን ችሎታም ይቀንሳሉ፣ /ለምሳሌ መኪና መንዳት ለአደጋ ያጋልጣል/

- የኦፒየም ውጤቶችን የሚወስዱ እናቶች የመወለጃ ቀኑ ያልደረሰ፣ ሙት ወይም አካላቱ ያልተስተካከለና የአእምሮ ዝግመት ያለበት ሕፃን ሊወልዱ ይችላሉ::

- የመተንፈሻ ስርዓት መዛባት ስለሚያስከትሉ ለሞት ይዳርጋሉ::

- ሄሮይን ወይንም ሌሎች የኦፒየም ውጤት የሆኑ መድኃኒቶች በመርፌ በጋራ የሚወስዱ ሰዎች ለኤች. አይቪ/ ኤድስ እና ለ Hepatitis B ሊጋለጡ ይችላሉ::

- ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ራስን እስከማጥፋት ድረስ ሊያደርስ ይችላል::

- ለእንቅልፍ ማጣት፣ ጭንቀትና መደበት ወ.ዘ.ተ.ይዳርጋሉ

## 2. የኮካ ተክልና ዝርያዎቹ (Coca)

የኮካ ተክል በደቡብ አሜሪካ ምዕራባዊ ክፍል በሚገኙ በአብዛኛው በፔሩ፣ ቦሊቪያና በኮሎምቢያ የሚበቅል ሲሆን ቁመቱ አጭር ሆኖ ዓመቱን በሙሉ ምርት ሊሰጥ የሚችል ዛፍ ነው::

እላይ በተጠቀሰው አካባቢ የሚኖሩ የአንዲያን ሕንዶች የተባሉ ብሔረሰቦች ረሀብን ለማስታገስ፣ ድካምን ለማስወገድና ለተለያዩ እምነቶች በማለት ከ2500 ዓመተ ዓለም ጀምሮ ቅጠሉን ሲቅሙት ቆይተዋል፣ አሁንም ይጠቀማሉ::

ከዚህ ዛፍ ቅጠል በቀላል ኬሚካላዊ ዘዴ ኮከይን (Cocaine) የተባለውና ከፍተኛ የማነቃቃትና ሱስ የማስያዝ ባህርይ ያለው ንጥረ ነገር ይገኛል::



ኮካ ተክል



ኮኬይን ሃይድሮክሎራይድ

# ኮኬይን

ኮኬይን በኮካ ቅጠል ውስጥ እንደሚገኝ የታወቀው በ1850 አካባቢ ነው። ከዚያም ለረጅም ዓመታት በመጠጥ መልክ በብዙ የዓለም ክፍሎች ጥቅም ላይ ሲውል ቆይቷል።
ለምሳሌ ይህ አሁን በመላው ዓለም ታዋቂ የሆነው ኮካ ኮላ የተባለው ለስላሳ መጠጥ ከ1886 እስከ 1904 /እ.ኤ.አ. ድረስ ኮኬይን ዋናው ይዘቱ እንደነበር ይታወቃል። ሆኖም ጎጂነቱ በመታወቁ ከ1904 ዓ.ም. ጀምሮ ኮኬይን ከመጠጡ እንዲወጣ በመደረጉ አሁን ገበያ ላይ ያለው ኮካኮላ ኮኬይን አልባ ነው።

ኮኬይን እስከአሁን በዓለም ከታወቁት አነቃቂ ኬሚካሎች ውስጥ በአነቃቂነትና ሱስ በማስያዝ ባህርይ ቁንጮ ቦታ ይዟል። በዚህም ምክንያት ኮኬይንን የሚጠቀሙ ሰዎች ቶሎ ሱሰኛ ይሆናሉ። ይህም ከኮኬይን ኃይለኛ ሱስ የማስያዝ ባህርይ የመነጨ ነው።

ኮኬይን በሕክምናው ዓለም ከአንገት በላይ ሕክምና ማለትም የአፍ፣ የአፍንጫና የጉሮሮ ቀዶ ሕክምና ለማድረግ በማደንዘዣነት (Local Anaesthesia) ጥቅም ላይ የሚውል ቢሆንም ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ስለሚያመዝንና ሌሎች ሱስ የማያስይዙ ነገር ግን እኩል ጠቀሜታ ያላቸው ማደንዘዣዎች ያሉ በመሆናቸው ከጥቂት አገሮች በስተቀር አብዛኞቹ ሕጋዊ ጠቀሜታውን አስቀርተውታል።

## በጤና ላይ የሚያደርሰው ጉዳት፣

ኮኬይን ከፍተኛ የማነቃቃት ኃይል ያለው በመሆኑ፣ ለአጭር ጊዜ፣

- ከፍተኛ የደስታ ስሜትን ይፈጥራል፣
- የምግብ ፍላጎትን ይዘጋል፣
- የድካም ስሜትን ያስወግዳል፣
- የጉልበት መጨመር ስሜትን ይፈጥራል፣

ነገር ግን እነዚህ ስሜቶች ከተወሰኑ ደቂቃዎች በኋላ ስለሚከስሙ በምትካቸው ብስጭትና ንዴት ይሰፍናል። በዚህም ሣቢያ የተፈጠረውን ብስጭትና ንዴት በማስወገድ ወደ ቀዳሚዎቹ ስሜቶች ለመመለስ ሲባል ተጠቃሚው በተወሰኑ ደቂቃዎች ልዩነት ኮኬይንን ደጋግሞ ለመውሰድ ይገደዳል። ውጤቱም፡-

ሀ. በአጭር ጊዜ ውስጥ የኮኬይን ሱሰኛ መሆን፣

ለ. ለተለያዩ በሽታዎች መጋለጥ፣ ለምሳሌ፣ የልብ በሽታ፣ የእፍንጫ መድማትና የአንጐል ኬሚካላዊ ይዘት ስለሚያዛባ እርጅናን ያፋጥናል።

ሐ. ቅፅበታዊ ሞት፣ በደስታ ስሜት ውስጥ ሰምጠው ባሉበት ጊዜ አንዳንድ ሱሰኞች /በመርፌ የሚወሥዱ/ መጠኑን መለካት ስለማይችሉ፣ ከሚገባ በላይ በመውሰድ ለቅፅበታዊ ሞት ይዳረጋሉ።

መ. የእንቅልፍ ችግር፣ ጭንቀት፣ የአመጋገብ ስርዓት ማጣት፣ መደበት፣

## 3. የካናቢስ ተክልና ዝርያዎቹ (Cannabis)

የእጸ-ፋሪስ ተክል በወይና ደጋ እና ቆላማ የአየር ጠባይ ባላቸው አካባቢዎች ይበቅላል። በአፍሪካና በእስያ በሚኖሩ ሕዝቦች ከ3000 ዓመታት ለማያንስ ጊዜ ለባሕላዊ ሕክምናና እምነቶች ጥቅም ላይ ውሏል። አሁንም በአንዳንድ አካባቢዎች በዚሁ መልክ ጥቅም ላይ የሚውል ነው።

ካናቢስ ውስጥ የሚገኘው ዋና ንጥረ ነገር ቴትራሃይድሮካናቢኖል (Tetrahydrocannabinol (THC)) የሚባልና የቁም ቅዠት ሊያመጣ የሚችል ሲሆን ሌሎችም ከዚህ ባላነሰ ደረጃ አእምሮን የሚያነቃቁ ንጥረ ነገሮች እንዳሉት በምርምር ተረጋግጧል።

ቴትራሃይደሮ ካናቢኖል በተክሉ የተለያዩ ክፍሎች የሚገኝ በመሆኑ ከተለያዩ የተክሉ ክፍሎች በሚገኙ ውጤቶች መሠረት የተለያዩ ስያሜዎች ይሰጠዋል። ይህም፣

- የደረቀው ቅጠልና የአበባው ክፍል - ማሪዋና (Marijuana) ፣
- ከቅጠሉና ከግንዱ የሚገኘው የማጣበቅ ባሕሪ ያለው ውጤት ሬዚን (Resin) ወይም ሐሺሽ (Hashish) ፣ እና



ካናቢስ



ሐሺሽ (Cannabis Resin)



Marijuana




የሐሽሽ ዘይት

- ከተክሉ ተጨምቆ የሚገኘው ዘይት - የካናቢስ ዘይት (Hash oil) ይባላል፡፡
  ከነዚህ ሶስት ዓይነት ዝግጅቶች መካከል ከካናቢስ ዘይት (Hash oil) ከፍተኛ የቴትራሃይድሮ ካናቢኖል (60%) መጠን የሚገኝ ሲሆን ከሬዚን (Resin) ደግሞ 25% በመያዝ በሚቀጥለው ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡

  የካናቢስ ውጤቶች ብቻቸውን ሆነ ከሲጋራ ጋር በአነስተኛ መጠን በሚወስዱበት ጊዜ በተጠቃሚው ላይ፡-
  - ጊዜያዊ የደስታ ስሜትን፣
  - ንግግር ማብዛትን፣
  - የስሜት ሕዋሳት ሥራ ማዛባትን /የድምፅ፣ የቀለም፣ የማየት .... ወዘተ/ ያስከትላሉ፡፡

ሆኖም እነዚህ ስሜቶች በሙሉ ጊዜያዊና የሚከስሙ በመሆናቸው ደጋግሞ መውሰድ ግዴታ ይሆናል፡፡

## በጤና ላይ የሚደርሰው ጉዳቶች፣

ቴትራሃይድሮ ካናቢኖል (THC) በባህሪው ሱስ አስያዥ በመሆኑ ቀደም ብሎ የተዘረዘሩትን ስሜቶች እንደገና ለማግኘት ሲባል መጠኑን መጨመር ግዴታ ነው፡፡ በመሆኑም የሚወሰደው መጠን እየጨመረ ሲሄድ የሚከተሉት ተጓዳኝ ችግሮች ይከሰታሉ፡፡

- የአእምሮ መዛባት (dellusion)
- የአእምሮ ብዥታ (illusion) ቀለም፣ ጊዜ፣ ርቀት ... ወዘተ በአግባቡ ለይቶ አለማወቅ ወይም አለመገንዘብ፣
- የአእምሮ መደነጋገር (confusion)
- የማስታወስ ችሎታ መቀነስ፣ (Memory impairment)
- ራስን መጣል (depersonalization)
- የሣንባ ካንሠርና (ካናቢስ ከሲጋራ የበለጠ ዝቃጭ (Tar) ስላለው) የመተንፈሻ አካላት ላይ ጉዳት ያደርሳል፡፡
- የማመዘን ችሎታ መቀነስ፣ የአእምሮ ድህነት (Poverty of ideas)፣ ለምንም ነገር ትኩረት አለመስጠት፣

## ለ. የሣይኮትሮፒክ መድኃኒቶች፣

ሣይኮትሮፒክ መድኃኒቶች የሚባሉት በሶስት ዋና ዋና ንዑስ ክፍሎች ይከፈላሉ:: እነሱም፡-

- የሚያነቃቁ (Stimulants) - እንደ አምፌታሚንና ዝርያዎቹ፣
- የሚያስተኙ (Depressants) - ባርቢቹሬትስና ቤንዞዳያዜኘንስ
- ሀሉሲጂንስ /የቁም ቅዠት የሚከቱ/ - ከተለያዩ የእንጉዳይ ዝርያዎችና አንዳንድ ኬሚካሎች የሚፈበረኩ ናቸው::

በዓለም አቀፍ ደረጃ ቁጥራቸው ከመቶ በላይ የሚደርሱ ሣይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ሲሆን ከነዚህ ውስጥ የተወሰኑት በስፋት አለአግባብ ጥቅም ላይ ስለሚውሉ የተለያዩ ችግሮች በማድረስ ላይ ይገኛሉ::

አገራችንም ለሕክምና አገልግሎት የምትጠቀምባቸውን የተወሰኑ ሣይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ወደ አገር ውስጥ በሕጋዊ መንገድ ታስገባለች::

ከነዚህም ውስጥ በአገራችን ከሌሎች ሣይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ይበልጥ ያለአግባብ ጥቅም ላይ የሚውለው ዲያዜፓም (Diazepam) የተባለው መድኃኒት እንደ ምሳሌነት በዚህ ፅሁፍ ተካትቷል::

### ዲያዜፓም (Diazepam)

ዲያዜፓም አፍዛዥ (Depressants) ተብለው ከሚታወቁት ሣይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ውስጥ አንዱ ሲሆን ለሕክምና ተግባር ከፍተኛ አገልግሎት የሚሰጥ መድኃኒት ነው::

ይህ በሐኪም ትእዛዝ ብቻ እንዲወሰድ የሚፈቀደው መድኃኒት፣ የአእምሮ መረበሽ፣ ጭንቀትና ያለመረጋጋት ችግር ላለባቸውና በዚህ ሣቢያ የእንቅልፍ እጦትና የደም ግፊት ላለባቸው ሕመምተኞች የሚሰጥ ነው::

ዲያዜፓም በአእምሮ ሕዋሳት ላይ የሚሠራ በመሆኑ ለረዥም ጊዜ አለአግባብ ከተወሰደ ተጠቃሚውን ሱሰኛ ያደርገዋል:: መድኃኒቱም በእንክብል፣ በመርፌና በሲረፕ መልክ ይዘጋጃል::

### በጤና ላይ የሚደርሰው ጉዳት፣

ዲያዜፓም በሐኪም ትእዛዝ ከአሥራ አምስት ቀን ለማይበልጥ ጊዜ ከተወሰደ በሱሱ ለመጠመድ ያለው ዕድል በጣም አነስተኛ ነው:: ከዚህ ጊዜ በላይ ከተወሰደ ግን በሱስ ከመያዝ በተጨማሪም መጠኑንም መጨመር አስፈላጊ ይሆናል::



ማይኮትሮፒክ መድኃኒት

በዚህም የተነሳ ሱሰኛው መድኃኒቱን በማይወስድበት ጊዜ፡-

- ይነጫነጫል፣
- መረጋጋት አይታይበትም፣
- የማስታወስ ችሎታው ይቀንሳል፣

ዲያዜፓም ከአልኮሆል ጋር በሚወሰድበት ጊዜ ችግሩ የባሰ ይሆናል፡፡

በኢትዮጵያ በመታየት ላይ ያለው የዲያዜፓም አለአግባብ አጠቃቀም ከሌሎች አገሮች ለየት ይላል፡፡ ይኸውም እንደሚታወቀው ሁሉ በኢትዮጵያ የጫት ተጠቃሚ ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ በመጨመር ላይ ይገኛል፡፡

ጫት አነቃቂ እንደመሆኑ መጠን ተጠቃሚዎች ጫት ከቃሙ በኋላ ቶሎ ያለመተኛት /እንቅልፍ/ ችግር ያጋጥማቸዋል፡፡ ይህን ከፍተኛ መነቃቃት ለመቀነስና እንቅልፍ አግኝቶ አእምሮን ለማሳረፍ አልኮል መውሰድ እየተለመደ መጥቷል፡፡ ይህም የተመረጠበት ምክንያት አልኮሆል የማድባት (Depressants) ኃይል ስላለው የጫትን የማነቃቃት ኃይል ለማዳከም ተብሎ ነው፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች /በተለያዩ ምክንያት/ አልኮሆልን መውሰድ የማይፈልጉ ከቅርብ ዓመታት ጀምሮ ዲያዜፓምን በአልኮሆል ምትክ በመውሰድ ላይ መሆናቸውን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በዚህም የእንቅልፍ ፍላጎታቸውን ያረካሉ፡፡ ሆኖም ይህ ሲደጋገም ለሱሰኝነት የሚያጋልጥ በመሆኑ ውጤቱ አስከፊ ነው፡፡ እንዲሁም ጫትና ዲያዜፓምን በአንድነት መጠቀም አእምሮን ለተወሳሰበ ጉዳትና ስቃይ መዳረግ ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የአልኮሆል ሱሰኞች የወሰዱት አልኮሆል ሳያረካቸው ቀርቶ እንቅልፋቸው የሚቋረጥ ወይም ለአጭር ጊዜ ብቻ ተኝተው የሚነሱ ከሆነ የተሟላ እንቅልፍ ለመተኛት በማለት ዲያዜፓም ይወስዳሉ፡፡ አልኮሆልና ዳያዜፓምን በአንድነት መውሰድ ለቅፅበታዊ ሞት ሊዳርግ ይችላል፡፡

የዲያዜፓም አለአግባብ አጠቃቀም አለም አቀፋዊ ባህሪይ ያለውና በጣም ብዙ ሰዎች ተዘፍቀውበት የሚገኝ ችግር በመሆኑ በቀላሉ ሊታይ አይገባም፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ማህበራዊ አደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች

እነዚህ አለም አቀፍ ቁጥጥር የማይደረግባቸውና ማኅበራዊ ግንኙቶችን ለማጠናከር ተደጋጋመው የሚወሰዱና ጉጅነታቸውን ባላገናዘበ መልኩ በማህበረሰቡ ተቀባይነትን ያገኙ ናቸው:: በአገራችን በዚህ መልክ በተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ጥቅም ላይ በመዋል ላይ የሚገኙት አልኮሆል፣ ጫት፣ ትምባሆና የሚሸተቱ ኬሚካሎች /ቤንዚን/ ይጠቀሳሉ::

### ሀ. የአልኮል መጠጦች፣

የአልኮሆል መጠጦች ከውሃና ከኢታኖል (Ethanol) የሚሠሩ ናቸው:: ኢታኖል ደግሞ የሚገኘው ፍራፍሬዎችን፣ አትክልቶችንና ሰብሎችን በማብላላት (Fermentation) ነው:: ቢራና የወይን ጠጅ ከቅድመ ታሪክ ጀምሮ ሰዎች በመጠጥነት ይጠቀሙባቸው እንደነበር ይታወቃል:: በአገራችንም ብዙ ባህላዊና ዘመናዊ የአልኮሆል መጠጦች እንዳሉ ይታወቃል:: ለመጥቀስም ያህል፣

- ከባህላዊ መጠጦች፣ - ጠላ፣ ጠጅ፣ ካቲካላ ... ወዘተ
- ከዘመናዊ መጠጦች፣- ቢራ፣ አረቂ፣ ጂን፣ ዊስኪ ... ወዘተ ናቸው:: አልኮሆልን አዘውትሮ መውሰድ ከጊዜ በኂላ ለአደገኛ ሱሰኝነት ስለሚዳርግ ጨርሶ ባይወሰድ ይመረጣል::

በአገራችን ባሉ የአልኮል መጠጦች ይዘት መጠን ላይ የተደረገ አንድ ጥናት ከዚህ በታች የተመለከተውን ውጤት ያሳያል::

| | ባሕላዊ መጠጦች | |
|---|---|---|
| ተ.ቁ. | ዓይነት | የአልኮል መጠን |
| 1. | ጠላ | 6.07 |
| 2. | ፊልተር ጠላ | 11.07 |
| 3. | ጠጅ | 13.36 |
| 4. | አረቂ | 34.09 |
| 5. | ዳግም አረቂ | 46.09 |

| | ዘመናዊ መጠጦች | |
|---|---|---|
| ተ.ቁ. | ዓይነት | የአልኮል መጠን |
| 1. | ቅ/ጊዮርጊስ ቢራ | 4.3 |
| 2. | ሜታ አቦ ቢራ | 4.2 |
| 3. | በደሌ ቢራ | 4.25 |
| 4. | ሳሪስ ወይን ጠጅ | 13.98 |
| 5. | ጂን | 38.91 |
| 6. | ውስኪ | 50.00 |

ከሠንጠረዡ ለመረዳት እንደሚቻለው አብዛኛው የሕብረተሰብ ክፍል የሚጠቀምባቸው ባህላዊ መጠጦች ከአንዳንድ ዘመናዊ መጠጦች የበለጠ የአልኮል ይዘት ያላቸው ሲሆን ጉዳታቸውም የዚያን ያህል ከባድ እንደሚሆን መገመት ይቻላል።

## በጤና ላይ የሚደርሰው ጉዳት፣

አልኮሆል ለረዥም ጊዜና በብዛት ሲወሰድ የሚከተሉትን የጤና ችግሮች ያስከትላል።

- የጨጓራና የአንጀት ሕመም
- የደም ግፊትና የልብ ሕመም
- የጉበት በሽታ
- በሴቶች አልኮሆል የተለያዩ የጤናና የማኀበራዊ ጉዳቶችን ስለሚያስከትል ከወንዶች በበለጠ አደገኛ ነው። በተለይም ለማህፀንና ለጡት ካንሰር ስለሚዳርግ ከእናትነት አኳያ ጉዳቱ የከፋ ነው።
- የቁም ቅዠት፣ የሰውነት መመረዝ፣
- የምግብ ፍላጐት መቀነስ፣ በዚህም ሣቢያ የኘሮቲንና የቫይታሚን እጥረት ስለሚያስከትል የሰውነት በሽታን የመቋቋም ብቃት ይቀንሳል፣
- የማመዛዘን፣ የማስተዋልና የመገንዘብ ችሎታ ይቀንሣል፣
- ስንፈተወሲብ ያስከትላል።
- ከጠጪ እናቶች በሚወለዱ ሕፃናት ላይ የአእምሮ ዝግመት ሊደርስ ይችላል።
- የአእምሮ ሕመም፣ የእጅ መንቀጥቀጥ፣
- ከፍተኛ የአልኮሆል መጠጥ በአንዴ በመውሰድ ለቅፅበታዊ ሞት ይዳርጋል።



ወጣቶች አልኮል ሲጠጡ




የስካር ውጤት

## ለ. ጫት

ጫት መሠረቱ ምስራቅ አፍሪካ ሲሆን ስርጭቱም እስከ ደቡብ አፍሪካ ከዚያም አልፎ በየመን አፍጋኒስታንና ቱርክ ውስጥ እንደሚበቅል ይታወቃል፡፡ ጫት ተራራማና እርጥበታማ በሆኑ ቦታዎች ይበቅላል፡፡

አንዳንድ ታሪክ አዋቂዎች እንደፃፉት ጫት መሠረቱ ኢትዮጵያ በተለይም ሐረርጌ እንደሆነና ከዚህ በመነሳት ወደ ሌሎች አገሮች እየተስፋፋ እንደሄደ ይናገራሉ፡፡

ኢትዮጵያ፣ ኬንያ፣ የመንና ማዳጋስካር በጫት አምራችነታቸውና ተጠቃሚነታቸው በዓለም የታወቁ አገሮች ሲሆኑ የሚያመርቱትም ጫት በተለያየ መንገድ ወደ ጎረቤትና ራቅ ወዳሉ አገሮች በሕጋዊም ሆነ በሕገወጥ መንገድ እንደሚዘዋወር ይታወቃል፡፡ በተለይም የአብቃይ አገሮች /ኢትዮጵያና ኬንያ/ ጎረቤት የሆኑት ሶማሊያና ጅቡቲ ከፍተኛ የጫት ተጠቃሚ ቁጥር መኖሩ በጥናት ተረጋግጧል፡፡

የጫት ተክል ዓለም አቀፋዊ ቁጥጥር የማይደረግበት ቢሆንም ከቅጠሉ ወይም ከሌላ አካሉ በቅመማ የሚገኙና የማነቃቃት ኃይል ያላቸው ካቲን (Cathine) ካቲኖን (Catahinone) እና ሜትካቲኖን (Methcathinone) የተባሉት ንጥረ ነገሮች በሚያደርሱት ከፍተኛ የጤና ጉዳት፣ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ችግሮች ከዚህ በፊት በቁጥጥር ከሚደረግባቸው ከአምፌታሚን ዝርያዎች ጋር ስለሚያመሳስላቸው ቁጥጥር ይደረግባቸዋል፡፡

በሌላ በኩል የአንዳንድ አገሮች /አሜሪካ፣ ካናዳና የተወሰኑ የአውሮፖ አገሮች/ የጫት ተክል በአገራቸው ውስጥ እንዳይመረት፣ እንዳይዘዋወርና ጥቅም ላይ እንዳይውል በተጠናል የመቆጣጠሪያ ሕግ አውጥተዋል፡፡




**የጫት ተክል**

**በጤና ላይ የሚደርሰው ጉዳት፣**

ጫትን አዘውትሮ በሚቅም ሰው የሚከተሉት የጤና ችግሮች ይደርሱበታል።

**☛ የጥርስ መበስበስ፣**

የጫት ቅጠል ከመቃሙ በፊት ንፅህናው የማይጠበቅ በመሆኑና በአፍ ውስጥ ለብዙ ደቂቃዎች ስለሚያዝ በአንዳንድ ተህዋስያንና ኬሚካሎች ጥርስ ሊበሰብስ ይችላል።



ወጣቶች ጫት ሲቅሙ



ጫትና መዘዙ

☛ **የምግብ ፍላጎት መቀነስ፣**

ጫት የምግብ ፍላጎትን ይቀንሳል:: በዚህም የተነሣ ቃሚው ቫይታሚን፣ ኘሮቲን ...ወዘተ በሚፈለገው መጠን ስለማያገኝ በሽታን የመቋቋም ኃይሉ ደካማ ይሆናል:: በመሆኑም በተለያዩ በሽታዎች በቀላሉ ሊጠቃ ይችላል::

☛ **የሆድ ድርቀት ያመጣል፣**

በዚህም የተነሣ ለአንጀት በሽታዎችና ለኪንታሮት (hemorrhoids) ያጋልጣል፣

- የአዕምሮ ሕመም መንስኤ መሆንና ማባባስ፣
- ከፍተኛ የድካም ስሜት፣

☛ **ለተላላፊ በሽታዎች ይዳርጋል፣**

ጫት ብዙውን ጊዜ በቡድን የሚቃም በመሆኑ በትንፋሽ የሚተላለፉ በሽታዎች ከአንዱ ወደ ሌላው በቀላሉ ሊተላለፍ ይችላል /ለምሳሌ ሣንባ ነቀርሳ/

- የስሜት መረበሽና መነጫነጭ፣ ራስን መጣል

☛ **ስንፈተ ወሲብ ያስከትላል፣**

ጫት ቃሚዎች የወሲብ ፍላጎት ቢኖራቸውም ወሲብ የመፈፀም ብቃታቸው ግን የተዳከመ ይሆናል::

በጫት ውስጥ የሚገኙ አነቃቂ ንጥረ ነገሮች ሱስ የማስያዝ ባህሪ ስላላቸው ተጠቃሚዎች ደጋግመው እንዲወስዱ ተፅዕኖ ስለሚያደርጉ ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች እየተባባሱ ይሄዳሉ::

## ሐ. ትምባሆ

ትምባሆ በተለያየ የአየር ንብረት ሊበቅል የሚችል ተክል ነው:: ቅጠሉ ከደረቀ በኋላ ሰዎች በሲጋራና በጋያ /ሺሻ/ መልክ ሲያጨሱት ሌሎች ደግሞ በከንፈርና በጥርስ መካከል ይዘው ለረዥም ጊዜ ይመጡታል::

ሲጋራ በመላው ዓለም በከፍተኛ ደረጃ እንደሚጨስ ይታወቃል። በየዓመቱ በመላው ዓለም ከ 6 ትሪሊዮን በላይ ሲጋራ ይጨሳል፤ የአጫሾቹም ቁጥር ከ1.3 ቢልዮን በላይ እንደሚሆን ይገመታል።

በትምባሆ ውስጥ የተለያዩ ንጥረ ነገሮች ያሉ ሲሆን ዋናውና የማነቃቃት ኃይል ያለው ኒኮቲን (Nicotine) ይባላል። ከዚህ በተጨማሪ ታር (Tar) የሚባል ዝቃጭ ነገር የሚገኝበት ሲሆን በዚህም ውስጥ እስከ 4000 የሚደርሱ የተለያዩ ንጥረ ነገሮች ይገኛሉ። ከነዚህም ከ250 የማያንሱት ለሰው ልጅ ጎጂዎች ሲሆኑ 50 የሚሆኑት ደግሞ ካንሠር የሚያመጡ ናቸው። አርሰኒክ (Arsenic) እና ቤንዞፕሪን (Benzoprine) ዋና ካንሠር አምጪ ንጥረ ነገሮች መሆናቸው ታውቋል።

## በጤና ላይ የሚያደርሰው ጉዳት፣

ትምባሆን የሚያጨሱ ሰዎች የሚከተሉት የጤና ችግሮች ይደርሱባቸዋል።

- የልብ ሕመምና የደም ግፊት መጨመር
- የአፍ፣ የጉሮሮ፣ የሳንባ፣ የማህፀን፣ የጡት፣ የቆዳ ካንሰር፣
- የሳንባ ሕመም (emphasyma)
- በሚያጨሱ ሴቶች ላይ ውርጃና ክብደቱ አነስተኛ የሆነና ያልተሟላ እድገት ያለው ሕፃን መውለድ፣
- የሰውነት ቆዳ መጨማደድ ሊያመጣ ይችላል።
- የማስታወስ ችሎታ መቀነስ፣
- የዓይን ሞራ ግርዶሽ፣ የፀጉር መመለጥ፣ የጥርስ መበስበስ፣
- የአፍ ጠረን መለወጥ፣ የመሥራት አቅምን መቀነስና ማዳከም፣
- ከአጫሽ ቤተሰብ ጋር የሚኖሩ ሕፃናት የመተንፈስ አካል ሕመም እንደ ጉንፋን፣ ብሮንካይትስና የሣንባ ምች ለመሳሰሉት በሽታዎች ይጋለጣሉ።

እነዚህ ከላይ በተጠቀሱት የጤና ችግሮች ምክንያት በመላው ዓለም ከሚገኙ አጫሾች ውስጥ በዓመት እስከ 5 ሚልዮን ሰዎች ይሞታሉ ከነዚህም ውስጥ 1.5 ሚልዮን የሚሆኑት ሴቶች ናቸው፣ ሁኔታው በዚህ ከቀጠለ ከ20 ዓመት በኋላ በየዓመቱ እስከ 10 ሚልዮን የሚደርሱ ሰዎች በትምባሆ ምክንያት ሊሞቱ ይችላል ከነዚህም ውስጥ 80% ከታደጊ አገሮች እንደሚሆን ይገመታል።

- እነዚህ የጤና ችግሮች በአጫሹ ብቻ ተወስነው የሚቀሩ አይደሉም:: አጫሹ ዋናው ተጎጂ ሲሆን የሲጃራ ጭስ በአካባቢው የሚገኝ ሰው በሁለተኛ ደረጃ ተጎጂ ይሆናል:: አጫሹ የሲጃራውን ⅔ ወደ ሰውነቱ ሲያስገባ በአካባቢው የሚገኝ ሰው ⅓ ጭስ ያስገባል::
- ወደ አካባቢው የሚወጣው ጭስ ወደአጫሹ ከሚገባ ጭስ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ካንሰር አምጪና ለጤና ጠንቅ የሆኑ ንጥረ ነገሮች አሉት፡፡
- በዓለም ላይ በሁለተኛ ወገን ጭስ ተጋላጭነት /Second Hand Smoke/ ሳቢያ ከ600, 000 በላይ ህፃናት በጨቅላነታቸው በየዓመቱ ይሞታሉ፡፡

## የትምባሆ አጠቃላይ ሁኔታ በኢትዮጵያ፤

በዓለም ላይ የተደረጉ የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ከሆነ የትምባሆ ተጠቃሚዎች ቁጥር በአደጉት ሀገራት በከፍተኛ ደረጃ እየቀነሰ ሲሆን በአንፃሩ ደግሞ በታዳጊ ሀገሮች በተለይም በአፍሪካና በኤሽያ በከፍተኛ ሁኔታ ከእለት ወደእለት እየጨመረ ነው፡፡ በሀገራችንም ምንም እንኳን ሰፋ ያሉ ጥናቶች ያልተደረጉ ቢሆንም አንዳንድ የዳሰሳ ጥናቶች ይፋ የሚያደርጉት እውነታ ከዚሁ የተለየ አይደለም፡፡

እ.ኤ.አ. በ1995 በአዲስ አበባና በሀሪቱ ውስጥ ባሉ 24 ከተሞች በተደረገው የአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች አጠቃቀም መሰረት የሲጋራ ተጠቃሚዎች ቁጥር ከአልኮልና ጫት ተጠቃሚዎች ቀጥሎ በ3ኛ ደረጃ ላይ ተቀምጧል፡፡

እ.ኤ.አ. በ2003 በአዲስ አበባ በሚገኙ 25 የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በተደረገው ጥናት መሰረት ከ9-12ኛ ክፍል ካሉ ተማሪዎች መካከል 10.1% የሚሆኑት የሲጋራ ተጠቃሚዎች እንደሆኑ ይፋ አድርጓል፡፡ በጥናቱ መሰረት በጊዜው ምንም አይነት የትምባሆ ዝግጅቶችን ከማይጠቀሙ ተማሪዎች መካከል 13.6% (ከሰባቱ አንዱ) በቀጣዩ ዓመት ሲጋራ እንደሚያጨሱ/ሊያጨሱ እንደሚፈልጉ ተናግረዋል፡፡ ጥናቱ በተጨማሪ እንዳሳየው ከሆነ የሁለተኛ ወገን አጫሽ ተጠቂዎች ላቅ ያለ እንደሆነ ነው፡፡ ይኸውም 10% (ከ አስር አንዱ) የሚሆኑት አብረዋቸው የሚኖሩ ቤተሰቦች እንሚያጨሱ፣እንዲሁም 44.6% የሚሆኑት ደግሞ በህዝብ ቦታዎች ለሁለተኛ ወገን ጭስ የተጋለጡ እንደሆኑ ይጠቁማል፡፡

## መ. የሚሸተቱ ኬሚካሎች (Inhalants)

የሚሸተቱ ኬሚካሎች (inhalants) የሚባሉት በጋዝ መልክ የሚተኑ ዝግጅቶች በውስጣቸው የያዙ ወይም ራሳቸው የመትነን ባህርይ ያላቸው ናቸው።

በአሁኑ ወቅት በዓለም ላይ ቁጥራቸው ወደ 600 የሚጠጉ ልዩ ልዩ ዓይነት ምርቶች የሚሸተቱ ኬሚካሎች እንዳሉዋቸው መረጃዎች ይገልፃሉ።

አብዛኞቹ የሚሸተቱ ኬሚካሎች በቤትና በሥራ አካባቢ የሚገኙ የተለያዩ ምርቶች ውስጥ የሚገኙ ሲሆን፣ ከነዚህም ውስጥ ቤንዚን፣ የመኪና ፖሊሽ፣ ቀለሞች (paints) የፀጉር ቀለም፣ ቀለም ማቅጠኛ፣ ማርከር፣ ጥፍር ቀለምና ማስለቀቂያው፣ የታይፕና የስቴንስል ፍሉድ፣ ሙጫ ... ወዘተ ይገኙበታል።

እነዚህ ኬሚካሎች ለቤት፣ ለቢሮና ለሌሎችም አገልግሎት የሚውሉ በመሆኑ በምርት፣ በሥርጭትና በአጠቃቀማቸው ላይ ምንም ዓይነት ቁጥጥር አይደረግባቸውም።

ኬሚካሎቹን የያዙ ምርቶች ሥራ ላይ በሚውሉበት ጊዜ በትነት መልክ ሲወጡ በአፍንጫ ወደ ሰውነት ገብተው የደስታ ወይም የመዝናናት ስሜትን ይፈጥራሉ። በዚህም የተነሣ ሰዎች ደጋግመው ለመውሰድ ይገፋፋሉ።

ከላይ እንደተገለፀው እነዚህን የሚተኑ ኬሚካሎች የያዙ ምርቶች ለቤት አገልግሎት (Household) የሚውሉ በመሆናቸው በቀላሉ በልጆች እጅ ስለሚገቡና ዋጋቸው አነስተኛ በመሆኑ በሱስ የተጠመዱትም በአብዛኛው ልጆችና ወጣቶች ናቸው። በተለይም ባደጉት አገሮች የነዚህ ኬሚካሎች ሱሰኞች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱን ሪፖርቶች ያሳያሉ።

በታዳጊ አገሮች ደግሞ ቤንዚን በስፋት በሕፃናትና ወጣቶች ይዘወተራል። በአገራችንም በአሁኑ ጊዜ ቤንዚን በጎዳና ተዳዳሪ ሕፃናትና ወጣቶች በከፍተኛ ደረጃ ጥቅም ላይ እንደሚውል በጥናት ተረጋግጧል። ቤንዚን የሚያሸቱት ሕፃናትና ወጣቶች ለምን ቤንዚን እንደሚያሸቱ ሲጠየቁ የሚያቀርቡት ምክንያት ብርድ ለመከላከልና ረሃብን ለማስታገስ የሚል ነው።




የሚሸቱቱ ኬሚካሎች





በእርግጥ ቤንዚንን ማሽተት ነርቮችን ስለሚያደነዝዝ ለጊዜው የረሀብም ሆነ የብርድ ስሜት ላይሰማቸው ይችላል። ነገር ግን ምግብ ካልበሉ በምግብ እጥረት ምክንያት ለሚመጡ በሽታዎች ይጋለጣሉ። ቤንዚን ብርድ የሚከላከል ሳይሆን ስሜቱ እንዳይኖር የሚያደርግ በመሆኑ በቂ ልብስ ሳይለብሱ ብርድ ላይ ከመተኛት ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።

**በጤና ላይ የሚደርሰው ጉዳት፣**

የሚሸተቱ ኬሚካሎችን አዘውትሮ መጠቀም ለሚከተሉት የጤና ችግሮች ይዳርጋል።

- የአፍ ሽታ መለወጥ /ከሰዎች የሚያርቅ/፣
- በአፍና አፍንጫ መካከል ያለው ቆዳ መቅላትና መቁሰል፣
- በፊት ቆዳ ላይ ለየት ያለ ቀለም ያላቸው ነጠብጣቦች መፈጠር፣
- የዓይን መቅላትና እንባ መፍሰስ፣
- የአፍንጫ ፈሳሽ መብዛት፣
- የማሽተት ችሎታ መቀነስ፣
- የሰውነት በሽታ የመከላከል ኃይል በማዳከም ለተለያዩ ሕመሞች መጋለጥ፣
- የእንቅልፍ ጊዜ መዛባት፣ ዘግይቶ መተኛት፣ አርፍዶ መነሳት/
- የደም ማነስ ሕመም፣ (Anaemea)
- የደም ካንሠር፣ (Leukimia)
- የስካር መንፈስና መፍዘዝ፣
- የተለያዩ የአእምሮ በሽታዎችን ያመጣሉ።
- የድምፅ/ንግግር መጐተት (Slurred Speech)

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ አንዳንድ ሱሰኞች ኬሚካሉ በተያዘበት ዕቃ ውስጥ ፊታቸውን ሸፍነው ስለሚያሸቱ በመተንፈስ ችግር /ስለሚታፈኑ/ የልብና የሣንባ ሥራ መዛነፍ ስለሚያጋጥማቸው ለሞት ይዳረጋሉ።

ኬሚካሎቹ በተለመደው ጊዜ ካልተወሰዱ ደግሞ የሚከተሉት ምልክቶች ሊታዩ ይችላሉ።

- የእጅ መንቀጥቀጥ፣
- የማያቋርጥ ራስ ምታት፣
- መነጫነጭ፣ ንዴትና ብስጭት፣
- ከመጠን በላይ በላብ መስመጥ ... ወዘተ ናቸው።

# ምዕራፍ ሶስት

# በአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ምክንያት የሚደርስ ፆታዊ ጥቃት

**መግቢያ**

ሀገራችን በዲሞክራሲ ሥርዓት በመልካም አስተዳደር ረገድ እያስመዘገበችዉ ያለዉን ፈጣን ልማት ቀጣይነት ለማረጋገጥ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል የዉጤቱ ተጠቃሚ ከማድረግ አንፃር ሴቶችንም እንደዜጋና የህብረተሰብ ክፍል የልማት ተሣታፊና ተጠቃሚ ለማድረግ በሕገ-መንግስቱና በሌሎች የልዩ ድጋፍ ተጠቃሚነት መብቶች መሠረት በርካታ አበረታች ተግባራት እየተከናወኑ ሲሆኑ ዉጤትም እየተገኘበት ነዉ፡፡ ስለሆነም እየተገኘ ያለዉን ዉጤት ለማረጋገጥ የዉጤቱ ተጠቃሚ የሆኑ ሴቶች ጉዳይን ከመንግሥት መዋቅሮች በተጨማሪም በባለቤትነት ይዘዉ ለተሻለ እድገትና የፆታ እኩልነት መረጋገጥ ቁርጠኝነት የሚጠበቅባቸዉ ሲሆን በተናጠል ከሚደረገዉ እንቅስቃሴ ባሻገር ያለዉን፣እዉቀትና አቅም አደራጅቶ በጋራ መንቀሳቀስ ለተሻለ ዉጤትና ተጠቃሚነት እንደሚያበቃ እዉን ነዉ፡፡

ይህንን ዓላማ መሠረት በማድረግ በሴቶች ለይ የሚፈፀም የአካላዊ፣ስነልቦናዊና ኢኮኖሚዊ ጉዳት የሚያስከትል ወይም ሊያስከትል የሚችል ፆታን መሰረት በማድረግ የሚፈፀም ድርጊት ነው ፡፡ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት በአሁኑ ጊዜ በአለማችን በከፍተኛ ሁኔታ እየተስፋፋ የመጣ የስብአዊ መብት ጥሰት ችግር ነዉ በተለያዩ ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ምክንያቶች የተነሳ እንዲህ አይነቱ ጥቃት በአብዛኛዉ የሚፈጸመዉ በሴቶች ላይ ሲሆን ጥቃቱ በግለሰብ ደረጃ ከሚያደርሰዉ ጉዳት በተጨማሪ ማህበራዊ ቀዉስን ያስከትላል፡፡

በአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ምክንያት ሴቶች ላይ በሚደርሰው ጉዳት ምክንያት ቤተሰብ ይበተናል፤ ማለትም ባሎቻቸው ዕፆችን በሚጠቀሙበት ወቅት ( በተለይም አልኮል በሚጠጡበት ወቅት) በሚስቶቻቸው አካላዊ ጥቃት ይፈፅማሉ በዚህም የተነሳ ቤተሰብ ይበተናል ልጆችም ለጎዳና ተዳዳሪነት ይጋለጣሉ፡፡

## በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶች ምንነት፤

እ.ኤ.አ. ዲሴንበር 20/1993 ዓ.ም በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶችን ለማስወገድ የወጣው የተባበሩት መንግስታት መግለጫ በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶችን እንደሚከተለው ይተረጉመዋል፡፡

***ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት***፡- ማለት በሴቶች ላይ የሚፈፀም ማንኛውም አይነት የአካላዊ፣ ስነ-ልቦናዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ጉዳት የሚያስከትል ወይም ሊያስከትል የሚችል ፆታን መሰረት በማድረግ የሚፈፀም ድርጊት ሲሆን የሚከተሉትን ተግባራት ያካትታል፡፡ መዛት፣ ማስፈራራት ወይም በሰላምም ሆነ በጦርነት ወቅት በግልም ሆነ በማህበራዊ ኑሮ የሰዎችን መሰረታዊ ነፃነቶች ከህግ ውጪ (Arbitrary) ገደቦች ማድረግን ይጨምራል በማለት ተረጉሞታል፡፡

የፆታዊ ጥቃት **መገለጫዎቹም** የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ✓ **አካላዊ ጥቃት**፡- ድብደባ፣ ጥፊ፣ ግርፋት እንዲሁም በተለያዩ መሳሪያዎች የሚፈፀሙ ጥቃትን ይጨምራል፡፡
- ✓ **ስነ- ልቦናዊ ጥቃት**፡- ማስፈራራትን፣ ማሸማቀቅንና ኢሰብአዊ አያያዝን ይጨምራል፡፡
- ✓ **ወሲባዊ ጥቃት**፡- አስገድዶ መድፈርን፣ ጠለፋንና አስነዋሪ ለሆነ የወሲብ ድርጊቶች ሴቶችን ማስገደድን፣ ወሲባዊ ትንኮሳን ያጠቃልላል፡፡
- ✓ **ኢኮኖሚያዊ ጥቃት**፡- ሴቶችን በኢኮኖሚ ለመቆጣጠር የፋይናንስና የሃብት አማራጮችን መገደብ ነው፡፡

## በአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ምክንያት የሚደርስ ፆታዊ ጥቃት

የአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ሕገወጥ አጠቃቀም በጤና ላይ ከሚያስከትሉት ችግሮች ባሻገር በሴቶች ላይ በኢኮኖሚያዊ እና በማህበራዊ ኑሮ ላይ ችግር እንደሚያደርሱ ይታወቃል፡፡የእነዚህ ድምር ውጤትም የሴቶች ጥቃት በሴቶች ላይ አካላዊ፣ ስነ-ልቦናዊ፣ ወሲባዊ ጥቃት እንዲሁም ማህበራዊ ጉዳቶችን ያስከትላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም

1. ዕጽ ተጠቃሚዎች በእፁ ተገፋፍተው ጾታዊ ጥቃትን ማለትም አስገድዶ መድፈርን እንዲሁም ዝሙትን ይፈፅሙባቸዋል፤ በዚህም የተነሳ ተጠቂዎች የጤና፣ የስነ- ልቦና እንዲሁም የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳት ይደርስባቸዋል፡፡
2. ጾታዊ ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች የደረሰባቸውን በደል ለመርሳት ሳይፈልጉ ወደ አደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ተጠቃሚነት ይገፋፋሉ፤ በዚህም የተነሳ ከዕፁ ጋር ተያያዥ የሆኑ የጤና የማህበራዊና የኢኮኖሚ ችግሮች ሰለባዎች ይሆናል፡፡

### ሀ. የጤና ችግሮች

የፆታዊ ጥቃት በደረሰባ ሴት ላይ የሚያደርሰው ሞት፣የአካል ጉዳት፣ ፌስቱላ፣ ኤች አይ ቪ/ኤድስን ጨምሮ በአባላዘር በሽታዎች መያዝ፣ያልተፈለገ እርግዝና፣ውርጃና ከዉርጃ ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ ችግሮች የሥነ-ልቦና አለመረጋጋት በወሲብ ጊዜ ህመም እርግዝናና በወሊድ ወቅት ለአደጋ መጋለጥ ይገኙበታል ፡፡ የኤች አይ ቪ/ ኤድስ መ/መ/ፅ/ቤት እንዲሁም የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚ/ር ይፋ ባደረጉት መረጃ መሰረት በኢትዮጵያ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ስርጭት በሴቶች ላይ 2.9% ሲሆን በወንዶች ላይ ግን 1.9% ነው፡፡ ሙሉ በሙሉ ችግሩ ከአደገኛ መድኃኒቶችና ዕጾች ጋር የተያያዘ ነው ብሎ መደምደም ባይቻልም አስገድዶ መድፍር ለችግሩ አስተዋፅኦ እንዳለው ለማወቅ አጠያያቂ አይደም፡፡

### ለ. ስሜታዊ፣ ማህበራዊና ሥነ-ልቦናዊ ችግሮች

የፆታዊ ጥቃት በደረሰባ ሴት ላይ የሚያደርሰዉ ጉዳት ሀፍረት፣ ፀፀት፣ ድብርት፣ ድንጋጤ፣ ፍርሐት፣ እራስን መጥላት፣ አለመረጋጋት፣ ብቸኝነት፣ መገለልና መድሎ፣ የአእምሮ

ሕመምና ተስፋ መቁረጥ ራስን ለማጥፋት ማሰብ፣ በራስ ያለመተማመን ችግር፣ ከትምህርት ቤት መኮብለል ይጠቀሳሉ፡፡

### ሐ. ኢኮኖሚያዊ ችግሮች

በሀገራችን በአብዛኛው ሴቶች በወንዶች ገቢ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ምክንያት ሱሰኛ የሆነ አባወራ ወይም የቤተሰብ አስተዳዳሪ/ ከሆነ የሚገኘውን ገንዘብ ወደሱስ ማርኪያነት ስለሚያውለው ሴቷን ለኢኮኖሚ ችግር ይዳርጋታል፡፡

በሱሰኝነት ምክንያት በሴቶች ለይ ከሚደርስባቸዉ ጥቃት የተነሳ ፍርሃትና አለመረጋጋት ይፈጥርባቸዋል፡፡ በዚህም የተነሳ ሴቶች ከእንደዚህ ዓይነት ጥቃት ለመጠበቅ በሚያደርጉት ጥረት ከሥራ፣ ከትምርት ቤትና መዝናኛ ራሳቸዉን ያገላሉ፡፡ሴቶች ከሀገሪቱ ህዝብ ብዛት ግማሽ ያህል ቁጥር ከመያዛቸዉ አንጻር ሴቶች በሱሰኝነት ምክንያት ከሚደርስባቸዉ ጾዎታዊ ጥቃት ከስራና ከትምህርት መስተጎል በኢኮኖሚዉ ለይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላል፡፡

## ለሴቶች ጥቃት መንስኤዎቹ

- አደገኛ መድኃኒቶች እና ዕጾችን መጠቀም፡፡
- ህብረተሰቡ ስለ ስነ-ፆታ ያለው ግንዛቤ አናሳ መሆኑ፡፡
- ስለአደገኛ መድኃኒቶች ወይም ዕጾች ሱሰኝነት ምክንያት ለሚደርሰው ጾዎታዊ ጥቃት ማህበረሰቡ (ወንዶችም ሆኑ ሰቶች) በሴቶች ለይ የሚደርሰ ጥቃትን መቀበላቸው፡፡
- የሴቶችን መብት የሚያሰከብር ህጎች አፈጻጸም አናሳ መሆን
- ልቅ የሆኑ ፊልሞች መስፋፋት የመሳሰሉት ተጠቃሽ ናቸዉ፡፡

አደገኛ መድኃኒቶች ወይም ዕፆችን መጠቀም ለበርካታ ተጓዳኝ የወንጀል ድርጊቶች መፈፀም ምክንያት የሚሆን ቢሆንም በሴቶች ላይ በተለይም አካለ መጠን ባልደረሱ ህፃናት ላይ የሚፈፀሙ የአስገድዶ መድፈር ወንጀል አንዱ ነው፡፡

## አስገድዶ መድፈር

- አደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆችን የሚጠቀሙ ግለሰቦች እድሚያቸዉ ለአካለ መጠን ያልደረሱ ህፃናት ሴቶችና ለአካለ መጠን የደረሱ ሴቶችን አስገድዶ በመድፈር ጉዳት ያደርሱባቸዋል፡፡
- አደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች በመስጠት ድርጊቱ ከተፈጸመባቸዉ በኃላ እንኳን ምን እንደተፈጸመባቸዉ እንዳያዉቁ በማድረግ ነዉ፡፡
- አስገድዶ በመደፈር ምክኒያት በሴቶች ለይ የሚያደርሰዉ አካላዊ፣ ስነ-ልቦናዊ፣ ወስባዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳት ከፍተኛ ነዉ፡፡
- ስለአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ያታዊ ጥቃት በሀገራችን ሰፋ ያለ የተጠና ጥናት ባይኖርም ግን ችግሩ በከፍተኛ ሁኔታ እንዳለ ያመለክታል ሆኖም ግን የሌሎች ሀገሮች ጥናት እደሚያመለክተዉ ከሆነ በጣም በከፍተኛ ሁኔታ ሰዎች አደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆችን በመጠቀም አስገድደዉ እደሚደፍሩ ያመለክታል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## አደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች በኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ ኑሮና በፖለቲካ ላይ የሚያደርሱት ችግር፣

የአደገኛ መደኃኒቶችና ዕፆች ሕገወጥ አጠቃቀም በጤና ላይ ከሚያስከትሉት ችግሮች ባሻገር በተጠቃሚው ኢኮኖሚና ማኀበራዊ ኑሮ ላይ ችግር እንደሚያደርሱ ይታወቃል። የእነዚህ ድምር ውጤትም የአገር ኢኮኖሚ መዋዠቅ፣ የእድገት መቀጨጭና በፖለቲካ ረገድም ሙስና፣ የሥነ ምግባር ጉድለት፣ የአገር ሉአላዊነት አለመከበር፣ ...ወዘተ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ለግንዛቤ ያህልም ችግሮቹ ከዚህ በታች እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል።

**ሀ. በኢኮኖሚ ላይ የሚያደርሰው ጉዳት፣**

በሱሰኝነት ምክንያት በግለሰብም ሆነ በአገር ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ይደርሳል።

**በግለሰብ ደረጃ፣**

- ሱሰኛው ሱሱን ለማርካት ሲል ከገቢው እየቀነሰ አደገኛ መድኃኒት፣ ወይም ዕፅ ስለሚገዛ ለመሠረታዊ ፍላጐት ማዋል የሚገባውን ገንዘብ በተሟላ መንገድ ሊያወጣ አይችልም። በተለይም ቤተሰብ ያለው ከሆነ ለቤቱ አስፈላጊውን ወጪ ስለማይሸፍን ቤተሰብ በረሀብና በእርዛት ይሰቃያል።

- ሱሰኛው ጤናው የተናጋ ስለሚሆን በተሰማራበት የሥራ መስክ ምርታማነቱ ዝቅተኛ በመሆኑ ከሥራ ሊባረር ይችላል።አደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆችን መጠቀም ከፍተኛ የጤና ችግር ስለሚያስከትል ሱሰኞች የጤና ችግሮቻቸውን ለመቅረፍ ብዙ ገንዘብ ለሕክምና ሊያወጡ ይችላሉ።

**በአገር ደረጃ፣**

- ሕገወጥ አጠቃቀምና ሱሰኝነት ባለበት አገር አምራች ኃይሉ ጊዜውን አደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆችን በመውሰድ የሚያሳልፍ ከሆነ ለማምረት የሚያውለው ጊዜና አቅም አናሳ ስለሚሆን የተፈለገውን ያህል አያመርትም፣ ምርታማነት ዝቅተኛ ስለሚሆን የአገር ኢኮኖሚ ይወድቃል።

- ሱሰኞች ጤናቸው አስተማማኝ ስለማይሆን መንግሥት ለሕክምና ተቋማት ማቋቋሚያ፣ ለባለሙያዎች ስልጠናና ደመወዝ፣ ለመድኃኒት መግዣ... ወዘተ ለከፍ ፍተኛ ወጪ ይዳረጋል::

- በዓለም አገሮች አደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆችን መጠቀምም ሆነ ማዘዋወር ሕገወጥ በመሆኑ ወንጀለኞችን መቆጣጠር የመንግሥት ኃላፊነት ነው:: በመሆኑም መንግሥት የፍትህና ተቆጣጣሪ አካላትን ማደራጀትና ማሰማራት ይኖርበታል:: ከፍተኛ የሱሰኛ ቁጥርና የተደራጀ ሕገወጥ አዘዋዋሪዎች ባሉበት አገር የተጠናከረ የፍትህ ተቋማትና ባለሙያዎች እንዲሁም በርካታ ቁጥር ያላቸው ተቆጣጣሪዎች፣ መሣሪያዎችና የሎጂስቲክ ድጋፍ አስፈላጊ ይሆናል:: በመሆኑም በአንድ አገር ኢኮኖሚ ላይ አላስፈላጊ ወጪ ያስከትላል::

- ለምግብ እህል ወይም ለወጪ ንግድ (Export) የሚሆኑ አዝርዕት፣ ፍራፍሬዎች... ወዘተ ማብቀያ መዋል ያለበት መሬት /ማሳ/ አደገኛ ዕፆች እንዲበቅሉበት ከተደረገ በአንድ በኩል ሕዝብ በረሃብ ይጠቃል፣ በመሆኑም ለምግብነት የሚያገለግሉ እህሎች ከውጪ አገር መንግሥት እንዲገዛ ይገደዳል:: በሌላ በኩል ወደ ውጪ ከሚላኩ የእርሻ ውጤቶች ይገኝ የነበረ የውጪ ምንዛሪ ይቀራል::

- አደገኛ ዕፆች ድብቅ ቦታ ላይ ስለሚበቅሉ መንግሥት ከዚህ ምርት ምንም ዓይነት ጥቅም አያገኝም፣ ነገር ግን መሬቱ ለሕጋዊ አዝርእት ወይም ተክሎች እርሻነት ቢውል የአገር ገቢ ይዳብራል፣ ሕዝብም በእርሻው ይጠቀማል::

- ለሕክምና ተግባር እንዲውሉ በውጪ ምንዛሪ የሚገዙ ናርኮቲክና ሣይኮትሮፒክ መድኃኒቶች በሕገወጥ መንገድ ጥቅም ላይ ሲውሉ በኢኮኖሚውም ሆነ በጤና አገልግሎቱ ላይ ተፅዕኖ ይኖረዋል::

- የአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ተጠቃሚዎች በሚሰሩባቸው ድርጅቶች ልዩ ልዩ አደጋዎች ሊያደርሱ ይችላሉ:: ለምሳሌ የእሳት ቃጠሎ፣ የማሽን መበላሸት፣ በራስ ላይ አደጋ ማድረስ ...ወዘተ ሊሆን ይችላል:: በመሆኑም ይህ ጥፋት የኢንሹራንስና የሕክምና ወጪን ይጨምራል:: ብሎም ኢኮኖሚያዊ ችግር ያስከትላል::

- የሐሰት ሰነዶች ይበረክታሉ፣ ገንዘብ አስመስሎ በመሥራት ሕገወጥ የገንዘብ ዝውውር እንዲኖር በማድረግ ሕጋዊ ሰነዶችን አስመስሎ መስራት የባለሥልጣናት ፊርማ አስመስሎ በመፈረም ገንዘብና ሌሎች ሰነዶችን በማጭበርበር ኢኮኖሚው ይዳከማል::
- ከሕገወጥ ምንጭ የተሰበሰበ ገንዘብ ወደ ሕጋዊነት በመለወጥ (Money Launderying) የኢኮኖሚ ቀውስ ይፈጠራል::

## ሰ. በማህበራዊ ኑሮ ላይ የሚከሰት ችግር፣

በሱሰኛው ላይ የሚደርሱ ችግሮች በግለሰብ ደረጃ ብቻ ተወስነው የሚቀሩ አይደሉም:: በቤተሰብና በማሕበረሰቡ ላይ ከፍተኛ ችግሮች ይደርሳሉ:: የነዚህም ችግሮች ዋና መንስኤዎች የጤናና የኢኮኖሚ ችግሮች ናቸው:: ከነዚህም ውስጥ ጥቂቶቹ፣

- ቀደም ብሎ እንደተገለፀው ሱሰኛው ከሚያገኘው ገቢ አብዛኛውን ለሱሱ ማርኪያ ስለሚያውለው ቤተሰቡንና ራሱን ኢኮኖሚያዊ ችግር ላይ ይጥላል:: በዚህም ሣቢያ ◆ ቤተሰቡ ይፈርሳል:-
  - ✓ የፈረሰው ቤተስብ አባላትም፣ እናት ለሴተኛ አዳሪነት ልትዳረግ ትችላለች፣ ልጆች ደግሞ ለጎዳና ተዳዳሪነት ይዳረጋሉ::
  - ✓ አባትም ከሥራ ተባሮ ስራ ፈት ሊሆን ይችላል::

- የብዙ ቤተስብ መፍረስ ከላይ የተዘረዘሩ ችግሮችን እያባባሰው ስለሚሄድ፣
  - ✓ የተመፅዋቾች፣
  - ✓ የሥራ አጦች፣
  - ✓ የጎዳና ተዳዳሪዎች፣
  - ✓ የቀማኞችና ሌቦች ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ ስለሚጨምር ማኅበራዊ
  - ✓ ቀውስ ይፈጥራል፣

- ሱሰኞች ከማኅበራዊ ተሳትፎ በሕግም ሆነ በልማድ ስለሚገለሉ ስነ አእምሮአዊ ችግር ይደርስባቸዋል:: በዚህ የተነሣ ፀረ ማህበረሰብ (antisocial) እርምጃዎች ሊወሰዱ ይችላሉ:: /በተለይም ወጣቶች/፣በዚህም ሣቢያ፣
  - ▪ የወንጀለኞች ቁጥር ይበራከታል፣ የረቀቁ የማፍያ መረቦች ይዘረጋሉ፣
  - ▪ የሕብረተሰብ ሰላም ይታወካል፣ ሽብር ይስፋፋል፣
  - ▪ የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ይበራከታል፣
  - ▪ የወጣት ጥፋተኞችና አደገኛ ቦዘኔዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ
  - ▪ ይሄዳል::
  - ▪ የተለያዩ የጠለፋ ተግባራትና ሌሎችም ችግሮች ይስፋፋሉ::

## ሐ. በፖለቲካ መረጋጋት ላይ የሚፈጠር ችግር፣

የአንድ አገር ፖለቲካ የተረጋጋ የሚሆነው ቀደም ብሎ የተጠቀሱት ጤና ነክ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮች ሲቀረፉ ነው:: አለበለዚያ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የአገርን ፖለቲካዊ ሕይወት አደጋ ላይ የሚጥሉ ችግሮች ናቸው:: በሱሰኝነትና በአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ሕገወጥ ዝውውር ሳቢያ የተለያዩ የፖለቲካ ችግሮች ይደርሳሉ፣ ከነዚህ ውስጥ አንዳንዶቹን ለመጥቀስ ያህል፣

- **ሙስናና የሥነ-ምግባር ብልሹነት መስፋፋት፣**

ሕገወጥ አዘዋዋሪዎች ንግዳቸውን ለማጧጧፍ ሲሉ የፍትህ አካላትና ተቆጣጣሪዎችን በገንዘብ በመደለል ኃላፊነታቸውን እንዲዘነጉ ያደርጋሉ:: ሕዝቡን ከማገልገል ይልቅ የሕገወጥ አዘዋዋሪዎች አገልጋይ ይሆናሉ::

- **የመንግሥት ንብረት መመዝበር፣**

የሕገወጥ አዘዋዋሪዎች መሣሪያ የሆኑ የመንግሥት ባለሥልጣናት የመንግሥትን ንብረት ለሕገወጥ አዘዋዋሪዎች መጠቀሚያ ያደርጉታል::

- **የአገር ሉአላዊነት አለመከበር፣**

አደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች በማዘዋወርና የጦር መሣሪያዎችን ወደ አገር ውስጥ በማስገባት የወንጀል ድርጊት እንዲስፋፋ ማድረግ፣ በአንድ አገር ውስጥ መስፈን ያለበትን መልካም አስተዳደር፣ ዲሞክራሲና የፍትሕ ስርዓት በእጅጉ በመፈታተን በመንግሥት የሚወጡ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ሕጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በተፈፃሚነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራሉ::

- **የወንጀል ድርጅቶች መበራከት፣**

የወንጀልና ሽብር ቡድኖች መደራጀት፣ መንቀሳቀስና የአገር ሰላምን ማወክ::

- ሕገወጥ አዘዋዋሪዎችን የመቆጣጠር ጠንካራ አቋምና ቁርጠኝነት ባላቸው የመንግሥት ባለሥልጣናትና ታዋቂ ግለሰቦች ላይ ማስፈራራት፣ በቤተሰቦቻቸውና በራሣቸው ሕይወትና ንብረት ላይ አደጋ መጣል፣
- በአገሮች መካከል የዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት መሻከር ወይም መቋረጥ፣ አንዳንድ ዲፕ ሎማቶች የሕገወጥ አዘዋዋሪዎች መሣሪያ ስለሚሆኑ በሕገወጥ ዝውውሩ ላይ ተሣታፊ

በመሆን ባላቸው ዲፕሎማስያዊ መብት በመጠቀም አደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች በማዘዋወር ሥራ ላይ ይሰማራሉ። ይህም ከዲፕሎማሲ ስነ ምግባር ውጪ ስለሆነ በዚህ ሣቢያ በአገሮች መካከል ያለው ግንኙነት ይሻክራል፣ ዲፕሎማቶች ሊባረሩ ይችላሉ፣ ከዚህ የባሱ እርምጃዎችም ሊወሰዱ ይችላሉ።

# ምዕራፍ አምስት

## ሰዎች ለምን አደገኛ መድኃኒቶችንና ዕፆችን ይጠቀማሉ?

የአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች አለአግባብ አጠቃቀም ምክንያቶቹ የሚመነጩት ከሶስት ክፍሎች ሲሆን፣

- መድኃኒቱ ወይም ዕጹ
- ተጠቃሚው /ሰው/
- አካባቢ /ሕብረተሰብና፣ ባህል፣ ሕግ፣ ፖሊሲ ...ወዘተ/ ናቸው።

እነዚህ ሶስት ክፍሎች (Agents) እርስ በርስ በሚያደርጉት መስተጋብር (Interaction) የአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች አለአግባብ አጠቃቀምን ምክንያቶች ይወስናሉ።

ከዚህ በመነሣትም የተለያዩ ሁኔታዎች እንደምክንያነት ይቀርባሉ። እዚህ ጽሑፍ ውስጥ ዋና ዋና  ምክንያቶች ቀርበዋል።

### ሀ. **አቅርቦት** (Availability)

የአደገኛ መድኃኒት ወይም ዕጽ በአንድ አካባቢ መገኘት ሰዎች እንዲጠቀሙ ይገፋፋል። ይህም ሲባል መድኃኒቱ ወይም ዕፁ የግድ እዚያ አካባቢ መብቀል ወይም መመረት ሳይኖርበት በሕጋዊ ወይም በሕገወጥ መንገድ በአካባቢው መገኘቱ በቂ ነው።

ለምሣሌ፣ ጫት በአገራችን የተለያዩ ክፍሎች የሚበቅል በመሆኑ በዚሁ አካባቢ ብቻ የሚኖሩ ሰዎች ይጠቀሙበታል ማለት አይደለም። ጫት በማይበቅልባቸው አካባቢዎች የሚገኙ ሰዎችም ሲጠቀሙ ይታያል።

በሌላ በኩል ደግሞ ጫት ደቡብ አሜሪካ ውስጥ አይታወቅም፣ ለምን ቢባል እዚያ አካባቢ ባለመገኘቱ ነው። ስለዚህ አቅርቦት ለሕገወጥ አጠቃቀም ወሳኝ ነው።

### ለ. የአቻ ላቻ ግፊት፣ (Peer Pressure)

የአቻ ግፊት አወንታዊም አሉታዊም ጎን አለው:: ይህ የሚወሰነው እንደየእኩዮች ቡድን ዓይነት ነው:: በአንድ ቡድን ውስጥ ያሉ አባላት ጥሩ ሥነምግባር ካላቸው በዚሁ አቅጣጫ የሚጓዙ ሲሆን ሥነምግባራቸው የተበላሸ ከሆነ ደግሞ የቡድኑ አባላት በሕብረተሰቡ የሚወገዙ ይሆናሉ::

በአንድ የዕድሜ ክልል ውስጥ ከሚገኙ ሰዎች አንዳንድ አባላት አለአግባብ አደገኛ መድኃኒት ወይም ዕጽ የሚጠቀሙ ከሆነ ይህ ድርጊታቸው በአካባቢያቸው ተቀባይነት እንዲኖረው ለማድረግ ሌሎችንም በተለያየ መንገድ በመገፋፋት ያስለምዳሉ::

በተለይም ወጣቶች በእኩዮቻቸው ግፊት ወደዚህ ማጥ የሚገቡበት ምክንያት በዚህ የዕድሜ ክልል የሚገኙ ወጣቶች አለአግባብ አደገኛ መድኃኒት ወይም ዕፅ በመጠቀማቸው ቤተሰብ ወይም ሕብረተሰብ የሚያደርስባቸውን ተፅዕኖ የተቋቋሙ ወይም ያሸነፉ ስለሚመስላቸው ነው::

### ሐ. አለማወቅ (Ignorance ...)

አደገኛ መድኃኒቶችና ዕጾች ስለሚያስከትሉት የጤና፣ የማኅበራዊ፣ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ችግር ካለማወቅ የተነሣ ሰዎች በስፋት ሊጠቀሙ ይችላሉ::

በሌላ በኩል ደግሞ ስለ አደገኛ መድኃኒቶችና ዕጾች ጠቃሚ ጐን ብቻ በሕገወጥ አዘዋዋሪዎችና ደላሎች በሚደረገው ቅስቀሳ፣ ሰዎችም በሚያደርጉት አንድ ሁለት ሙከራዎች በነዚህ ደላሎች የተገለፀላቸው ውጤት ለጊዜው እውነት መስሎ ስለሚታያቸው በዚህ ተገፋፍተው ሊጠቀሙ ይችላሉ:: ሆኖም አለአግባብ አጠቃቀሙን እየገፉበት ሲሄዱ ጎጂ ጎናቸው እየታየ ይበልጥ እየተባባሰ ሲመጣም ተጠቃሚው ተጠቃሎ ወደ ሱሰኝነት ጐራ ይገባና ለማቆም ወይም ከደረሰበት ጉዳት ለመመለስ በጣም አስቸጋሪ ይሆናል::

### መ. መገለል (Alienation)

ሰዎች በተፈጥሮአቸው አለኝታን ይፈልጋሉ፣ የቤተሰብና የብሔር አባልነታቸው፣ የአገር ተወላጅነት ...ወዘተ ሊኮሩበት ይፈልጋሉ:: ሆኖም አንድ ሰው እነዚህን ያጣና የተገለለ ከሆነ የእሱን መሰሎች /የተገለሉ/ ይፈልጋል፣ ይቀላቀላል:: እነዚህ የሚቀላቀላቸው ሰዎች ወይም ቡድኖች ምናልባት ከደረሰባቸው ስነልቦናዊ ቀውስ ለመሸሽ፣ የአደገኛ መድኃኒቶች ወይም ዕጾች ተጠቃሚ ከሆኑ ለሱሰኝነት ይዳርጋሉ::

መገለል ከፍተኛ ስነልቦናዊ ተፅዕኖ የሚያደርስ በመሆኑ በዚህ የሚሰቃዩ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ አደገኛ መድኃኒቶችና ዕጾችን ይጠቀማሉ:: አደገኛ መድኃኒቶችና ዕጾች አእምሮን የማደንዘዝ፣ አስተሳሰብን የማዛባት ኃይል ስላላቸው ለጊዜው ከጭንቀቱ የገላገሉት ስለሚመስለው አዘውትሮ ሊጠቀም ይችላል::

## ሠ. ፍልሰትና ሥራ አጥነት፣ (Migration & Unemployment)

በብዙ የዓለም ክፍሎች ላይ በሚፈጠሩት ክስተቶች ሕዝቦች ከቦታቸው በመፈናቀል አካባቢያቸውን ጥለው ወደ ሌላ አካባቢ ይሠደዳሉ:: ከድርቅ፣ ከጦርነት፣ ከድህነት ...ወዘተ ለመሸሽ ሰዎች ወደ ሌሎች አገሮች ወይም በራሳቸው አገር ውስጥ ወደሚገኙ ገጠሮችና ከተሞች ይፈልሳሉ:: ከቤተሰብ መለየትና ወደማያውቁት ባህል መቀላቀል ራሱ የመገለልን፣ የብቸኝነት ስሜትን ስለሚያሳድር ከዚህ የሚያመልጡበት መንገድ ማፈላለግ አይቀርም:: ለዚህም እንደመፍተሔ ተደርጎ የሚወሰደው አደገኛ መድኃኒቶች ወይም ዕጾችን መጠቀምና ካላቸው ስነልቦናዊ ተፅዕኖ ለጊዜውም ቢሆን መገላገል ወይም በሚያገኙት ጊዜያዊ ደስታና እርካታ ችግሩን መርሳት ይመርጣሉ::

በሌላ በኩል ደግሞ መፈናቀል በተለይም ከገጠር ወደ ከተማ መፍለስ አዲስና የተለየ ሕይወት ለመምራት ሥራ ማግኘት፣ መጠለያ ማግኘት ...ወዘተ ስለሚያስፈልግ ይህንን መወጣት አማራጭ የለውም:: ሆኖም ሁሉም በቀላሉ ስለማይገኝ ሥራ አጥነት፣ የመጠለያ እጦት አደገኛ መድኃኒቶችና ዕጾችን ወደ መጠቀም ልምድ ሊገፋፉ ይችላሉ:: ይህ በታዳጊ አገሮች ጎልቶ የሚታይ ችግር ነው::

## ረ. መምሰል፣ (Modeling)

የሰው ልጅ በተፈጥሮው ባህሪውን ከሌሎች ሰዎች ጋር ለማመሳሰል ጥረት ያደርጋል:: የቤተሰብ፣ የታላላቆች፣ የመምህራን፣ የታወቁ አርቲስቶች፣ ስፖርተኞች ...ወዘተ ባህሪን የመኮረጅ ፀባይ አለው:: ይህ ክስተት በብዛት የሚታየው በወጣቱ የሕብረተሰብ ክፍል ላይ ነው::

ጥናቶች እንደሚያሣዩት የአደገኛ መድኃኒቶችና ዕጾች ሱሰኛ ካልሆኑ ቤተሰቦች ከሚወለዱ ሕፃናት ይልቅ ሱሰኛ ከሆኑ ቤተሰቦች የሚወለዱ ሕፃናት በበለጠ ለሕገወጥ አጠቃቀም እንደሚጋለጡ ነው:: ወላጆች የሚያሳዩት በጎም ሆነ ጎጂ ባህሪይ በልጆቻቸው በቀላሉ ሊኮረጅ እንደሚችል ነው::

የፊልም ተዋንያን፣ ስፖርተኞች፣ ዘፋኞች የሚያሳዩትን ባህርይ ወጣቶች በቀላሉ የመከተል ልማድ አላቸው:: በአጋጣሚ ከላይ ከተጠቀሱት ሞዴሎች አንዳንዶቹ የአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ተጠቃሚ /ሱሰኛ/ ከሆኑ እነሱን መምሰል የሚፈልግ ወጣት የሚያደርጉትን በማድረግ ሱሰኛ ሊሆን ይችላል::

### ሰ. የአእምሮ መታወክ (Psychiatric Disturbances)፣

ጥናቶች እንደሚያሳዩት ከሆነ የተለያዩ የአእምሮ በሽታዎች ለሱሰኝነት እንደሚያጋልጡ ተረጋግጧል:: ለምሳሌ የጭንቀት (Anxiety) እና የመደበት (Depression) የአዕምሮ ችግር ያለባቸው ሰዎች ከዚህ ችግራቸው ለመውጣት ሲሉ የተለያዩ የአዕምሮ ሕክምና መድኃኒቶችን አዘውትረው ሊወስዱና ለሱስ ችግር ሊዳረጉ ይችላሉ:: በሌላ በኩል ከቤተሰብ መለየት፣ የቤተሰብ ደስታ ማጣትን በመሳሰሉት ሁኔታ ሰዎች ለአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች በመጋለጥ ለሱሰኝነት ሊዳረጉ ይችላሉ::

### ሸ. ጉጉት (Curiosity)፣

ሰዎች አንድን ነገር የማወቅና የመሞከር ባህርይ አላቸው:: ይህም በከፍተኛ ደረጃ በወጣትነት የዕድሜ ክልል የሚታይ የተፈጥሮ ክስተት ነው:: ከዚህ አኳያ ስለአደገኛ መድኃኒቶችና ዕጾች ጎጂ ገፅታ ቢነገራቸው እውነታውን ለማረጋገጥ ለሙከራ ሊጠቀሙ ይችላሉ:: በሌላ በኩል ሕገወጥ አዘዋዋሪዎችና ደላሎች ስለአደገኛ መድኃኒቶችና ዕጾች አስከፊ ገፅታ ሣይሆን ጥሩና በጎ ጐኖች እንዳሏቸው አድርገው ስለሚያወሩ በዚህ ተታለው ወይም ተገፋፍተው ወደ ሱሰኝነት ጐራ የሚገቡ ወጣቶች ቁጥር ከፍተኛ ነው::

እነዚህ ከላይ የተመለከቱት ዋና ዋና ምክንያቶች ሲሆኑ ሌሎች ግለሰባዊ፣ ስነ ልቦናዊና አካባቢያዊ ምክንያቶች እንዳሉ ሊታወቅ ይገባል::

# ምዕራፍ ስድስት

# አደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ከኤች አይ ቪ/ኤድስ ጋር ያላቸው ቁርኝት

## ሀ. መግቢያ

- የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እ.ኤ.አ. በ 2009 ዓ.ም ባወጣው መረጃ መሰረት በተለያዩ የአለማችን ክፍሎች 33.3 ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎች ከቫይረሱ ጋር እንደሚኖሩ ይገመታል፡፡
- በዚሁ ዓመትም 2.6 ሚሊዮን የሚሆኑ ወገኖች አዲስ በቫይረሱ የተያዙ ሲሆን 1.8 የሚሆኑ ደግሞ በአመቱ ውስጥ ህይወታቸውን በኤድስ ምክንያት አጥተዋል፡፡
- ኤች አይ ቪ/ኤድስ በሁሉም የአለማችን ክፍሎች የተሰራጨ ቢሆንም ከፍተኛ የስርጭት፣ አዲስ በቫይረሱ የመያዝ እንዲሁም የሞት መጠን የሚታየው ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገራት መሆኑን ከመረጃዎቹ መገንዘብ ይቻላል፡፡
- በሪፖርቱ መሰረት እ.ኤ.አ በ2009 ዓ.ም. ከቫይረሱ ጋር እንደሚኖሩ ከሚገመቱ ወገኖች 22.5 ሚሊዮን (67.6%) የሚሆኑት፣ በዚሁ ዓመት አዲስ በቫይረሱ ከተያዙት መካከል 1.8 ሚሊዮን (69.2%) የሚሆኑት እንዲሁም በአመቱ ውስጥ ህይወታቸውን በኤድስ ምክንያት እንዳጡ ከሚገመቱት ወገኖች 1.3 ሚሊዮን (72.2%) የሚሆኑት በዚሁ ከሰሃራ በታች በሚገኙ የአፍሪካ ሀገራት ነው፡፡

✓ **ኤች አይ ቪ/ኤድስ በአፍሪካ ቁጥር አንድ ገዳይ መሆኑን ለመረዳት አያዳግትም፡፡**

- **ኢትዮጵያ-** ከፌዴራል ኤች አይ ቪ/ኤድስ መ/መ/ጽ/ቤትና ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር መረጃ መገንዘብ እንደሚቻለው እ.ኤ.አ. በ2010 ዓ.ም. በኢትዮጵያ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ስርጭት መጠን 2.4% ሲሆን 1.2 ሚሊዮን የሚሆኑ ወገኖች ቫይረሱ በደማቸው ይገኛል፡፡
- ከነዚህም መካከል 79, 871 የሚሆኑት ህፃናት ናቸው፡፡ በዚሁ ዓመት 28, 073 የሚሆኑ ወገኖች ህይወታቸውን በኤድስ ምክንያት እንዳጡ የሚገት ሲሆን 137, 494 የሚሆኑ ደግሞ በአመቱ ውስጥ አዲስ በቫይረሱ እንደተያዙ ይገመታል፡፡

- ○ አጠቃላይ የስርጭቱ መጠን ከላይ የተጠቀሰው ይሁን እንጂ ከቦታ ቦታ እንዲሁም በፆታ፣በእድሜና በተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች የተለያየ የስርጭት መጠን ይታያል፡፡ በከተሞች ያለው አማካይ የስርጭት መጠን 7.7% ሲሆን በገጠር ያለው የስርጭት መጠን ደግሞ 0.9% መሆኑን መረጃዎች የሚያስረዱ ሲሆን ይህም የከተሞች የስርጭት መጠን በገጠር ካለው የስርጭት መጠን በ 8 እጥፍ በላይ መሆኑን ያሳያል፡፡
- ○ በፆታ ስንመለከት ደግሞ በሴቶች ያለው የስርጭት መጠን 2.9% ሲሆን በወንዶች ያለው ደግሞ 1.9% በመሆኑ በከፍተኛ ደረጃ ሴቶች ከወንዶች በበለጠ መልኩ በቫይረሱ እንደተጠቁ ያሳያል፡፡
- ○ የአደገኛ መድሃኒቶችና እፆች ሱሰኝነት ዘር ፣ ሀይማኖት ፣ ፆታና አገር ሳይለይ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል የሚያጠቃ ችግር ነው፡፡
- ○ ብዙ ሰዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አደገኛ መድህኒቶችና እፆች በሚያስከትሉት ችግር ለሞት ተዳርገዋል፡፡ለምሳሌ፡- በየዓመቱ በአለማችን ላይ 2.5 ሚሊዮን ሰዎች በአልኮል ምክንያት ህይወታቸውን ያጣሉ፡፡

የኤች አይ ቪ/ኤድስ መተላለፊያ መንገዶች፡-

1. የግብረ ስጋ ግንኙነት (ተቃራኒ ፆታ ወይም አንድ ፆታ)
2. በቫይረሱ የተበከለ ደም ወይም የደም ውጤቶች
3. ከእናት ወደ ልጅ፡፡

## ለ. አደገኛ መድኃኒቶችና እፆች እና ኤች አይ ቪ/ኤድስ

- ✓ አደገኛ መድኃኒቶችና እፆች ከኤች አይ ቪ/ኤድስ እና ሌሎች ደም ወለድ በሽታዎች ስርጭት ጋር ቀጥተኛ ትስስር አላቸው፡፡
- ✓ በዚህም ምክንያት የአደገኛ መድኃኒቶችና እፆች ጉዳይ እንደ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ጉዳይ በብዙ የአለም አገሮች ይወሳል፡፡
- ✓ አደገኛ መድኃኒቶችና እፆች ለኤች አይ ቪ/ኤድስ ቫይረስ በሁለት መንገድ ያጋልጣሉ፡፡

## 1. ልቅ የሆነ የግብረ ስጋ ግንኙነት /unprotected sex/

- ✓ አደገኛ መድኃኒቶችና እፆች ሲወሰዱ በዋነኛነት ስራቸውን የሚሰሩት በአዕምሮ ላይ ሁኖ የሚያጠቁት ክፍልም ንቃተ ህሊና /Consciousceness/ ፣ የግንዛቤ ማዕከል /Judgement/ ፣ የውሳኔ መወሰኛ ማዕከል /Decision Making Center/ ፣ የማስታወስ /Memory/ ፣ ወዘተ … ሲሆን በዚህም የተነሳ ሰዎች የማገናዘብ ችሎታቸው ስለተዛባ ትክክለኛ ውሳኔ ለመወሰን ስለሚያዳግታቸው ከሶስቱም የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያ መርሆች አንዱን ለመከተል አይችልም፡፡ ጥንቃቄ ያልተሞላበት የግብረ ስጋ ግንኙነት ላለመፈፀምም አይጥርም፡፡
- ✓ አደገኛ መድኃኒቶችና እፆች የማገናዘብ ችሎታን ስለሚያዛቡ ካልተፈለገ ሰው ጋር ጥንቃቄ ያልተሞላበት ግብረ ስጋ ግንኙነት የመፈጸም እድሉ ከፍተኛ ይሆናል፡፡
- ✓ በተባበሩት መንግስታት የአደገኛ መድኃኒቶችና እፆች እና ወንጀል ጽ/ቤት /UNODC/ ጥናቶች እንደሚያመላክቱት አብዛኛዎቹ አደገኛ መድኃኒቶችና እፆች ተጠቃሚዎች ግብረ ስጋ ግንኙነት ሲፈፅሙ ኮንደም እንደማይጠቀሙና ቢጠቀሙም እንኳን በአግባቡ አይጠቀሙም ፡፡ በኤች አይ ቪ/ኤድስ የመያዝ እድል በጣም ከፍተኛ ነው፡፡
- ✓ አደገኛ መድኃኒቶችና እፆች ተጠቃሚዎች ህገወጥ ድርጅቶች አንዱ አስገድዶ መድፈር ነው፡፡ በዚህን ጊዜ የሚወሰድ ጥንቃቄ ስለሌለ በቫይረሱ የመያዝ እድሉ በጣም ከፍተኛ ይሆናል፡፡
- ✓ በአጠቃላይ አደገኛ መድኃኒቶችና እፆች በቀጥታ ተጠቃሚዎችንና የተቃራኒ ፆታን ለኤች አይ ቪ/ኤድስ ያጋልጣል፣ ምክንያቱም፡-
    - ተጠቃሚው ጎጂና ጠቃሚ የሆነውን ነገር ለመለየት ስለሚያዳግተው
    - የተጠቃሚውን አእምሮና ግንዛቤን ስለሚያዛቡ
    - አይሆንም ለማለት ይቸገራሉ (unable to say no)
    - ጥንቃቄ የተሞላበት ግብረ ስጋ ግንኙነት ለማድረግ አለመቻል፡፡
- ✓ ፍች ፣ የቤተሰብ መበታተን ፣ የጎዳና ተዳዳሪነት ፣ ዝሙት ወ.ዘ.ተ… አደገኛ መድኃኒቶችና እፆች በሚያስከትሉት ችግር ምክንያት በቤተሰብና በህብረተሰብ ደረጃ የሚታዩ ችግሮች ናቸው፡፡

## 2. በቫይረሱ የተበከሉ መርፌዎች በጋራ መጠቀም /Use of contaminated needle/

- ✓ በተ.መ.ድ. የአደገኛ መድኃኒቶችና ወንጀል መከላከል ድርጅት/UNODC/ ባወጣው ፅሁፍ መሰረት በአለም ላይ 16 ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎች አደገኛ መድኃኒቶችንና እፆችን በመርፌ እንደሚወጉ ይገልፃል፡፡ ከነዚህም ውስጥ 3 ሚሊዮን የሚሆኑት ከኤች አይ ቪ/ኤድስ ጋር ይኖራሉ፡፡
- ✓ በአብዛኛው የአለም ክፍል አደገኛ መድኃኒቶችና እፆች በመርፌ መጠቀም/ Injecting Drug Use (IDU)/ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ዋነኛ መተላለፊያ ዘዴ እየሆነ መጥቷል፡፡
- ✓ በአፍሪካ በተለይም ደግሞ ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገሮች አደገኛ መድኃኒቶችንና እፆችን በመርፌ መጠቀም/ Injecting Drug Use (IDU)/ የቅርብ ጊዜ ክስተትና በከፍተኛ ደረጃ እየተስፋፋና እየተዛመተ እንደመጣ ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡
- ✓ በተባበሩት መንግስታት የኤች አይ ቪ/ኤድስ ማዕከል / UNAIDS/ እ.ኤ.አ በ2010 ባወጣው ሪፖርት እንደተቀመጠው ከሰሃራ በታች ባሉ ሀገሮች (በኬንያ 36%፣ በዛንዚባር 26%፣ በናይጀሪያ 10%) የሚሆኑ የአደገኛ መድኃኒቶችና እፆች በመርፌ ተጠቃሚዎች በኤች አይ ቪ/ ኤድስ እንደተያዙ ያስረዳል፡፡
- ✓ ዋነኛ የኤች አይ ቪ/ኤድስ መተላለፊያ ዘዴ ቫይረሱን በቀጥታ ወደ ደምስር በመውጋት ነው /በቫይረሱ በተበከለ መርፌ መጠቀም/፡፡
- ✓ ጥንቃቄ ከሌለበት ግብረስጋ ግንኙነት ይልቅ በቫይረሱ የተከለከለ መርፌ ለቫይረሱ የማጋለጥ ሀይሉ በጣም ከፍተኛ ነው፡፡
- ✓ አደገኛ መድኃኒቶችና እፆች በመርፌ መጠቀም ኤች አይ ቪ/ኤድስ ከሚያስተላልፉ ሶስቱም ዋና ዋና መንገዶች አንዱ ነው፡፡
- ✓ አደገኛ መድኃኒቶችና እፆች በመርፌ በመጠቀም የኤች አይ ቪ/ኤድስ ስርጭት መጨመር ለብዙ የዓለም አገሮች ትልቅ ስጋት ሆኗል፡፡
- ✓ በመርፌ መወጋት አደገኛ መድኃኒቱ በብዛት አንጎል ውስጥ መገኘቱን ያረጋግጣል፡፡

- ✓ አደገኛ መድኃኒቶችና እፆች ተጠቃሚዎች መርፌ በመወጋት /injecting/ እና ከመርፌውም በሌላ ዘዴ መጠቀም /non-injecting/ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ በዝሙት ዓለም /sex industry/ ይሳተፋሉ ፣ ይኸውም፡-
  - ○ ዝሙት ለአደገኛ መድኃኒቶችና እፆች /sex for drugs/
  - ○ ዝሙት ለገንዘብ /sex for money/
  - ○ ገንዘብ ለአደገኛ መድኃኒቶችና እፆች /money for drugs/

- ✓ አደገኛ መድኃኒቶችና እፆች ለኤች አይ ቪ/ኤድስ እንደሚያጋልጡ ሁሉ ኤች አይ ቪ/ ኤድስም ለአደገኛ መድኃኒቶችና እፆች ተጠቃሚነት ይዳርጋል፡፡
  - ከቫይረሱ ጋር አብረው የሚኖሩ ሰዎች ካላቸው የማህበራዊና ስነ ልቦናዊ ችግሮች ለጊዜውም ቢሆን ለመርሳት ሲባል አደገኛ መድኃኒቶችና እፆች ይጠቀማሉ፡፡
  - ይኸውም በዋነኛነት በህብረተሰቡ የሚደርስባቸውን የአድልዎና መገለልን ስሜት ለመርሳት ሲባል የሚደረግ ነው፡፡

- ✓ አደገኛ መድኃኒቶችና እፆች ከሚያደርሱት ዘርፈ ብዙ የጤና ችግሮች ከቫይረሱ ጋር አብረው የሚኖሩ ሰዎች አደገኛ መድኃኒቶችና እፆች ተጠቃሚ ከሆኑ የበሽታ መከላከልና መቋቋም አቅማቸው ከሚጠበቀው የበለጠ ይዳከምና ለበሽታ (ኤድስ) በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲጋለጡ ያደርጋል፤ **ሞትን ያፋጥናል፡፡**
- ✓ እስከ አሁን አደገኛ መድኃኒቶችና እፆች በመርፌ መጠቀም ኢትዮጵያን ጨምሮ ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገሮች ለኤች አይ ቪ/ኤድስ ስርጭት ዋነኛ መንገድ ሪፖርት ባይደረግም ችግሩ ግን በክፍለዓለሙ እንዳለ መረጃች ይጠቁማሉ፡፡

## ሐ. አደገኛ መድኃኒቶችና እፆች እና ኤች አይ ቪ/ኤድስ በኢትዮጵያ

- ✓ አደገኛ መድኃኒቶችና እፆች ስርጭቱ ፣ የችግሩ ስፋትና ሂደት ከኤች አይ ቪ/ኤድስ ስርጭት ጋር ያላቸው ተዛምዶ በአገር አቀፍ ደረጃ የተጠና ጥናት የለም፡፡
- ✓ ጫት፣ የአልኮል መጠጦች፣ በአፍንጫ የሚሸተቱ/ Inhelants and benzene/ እና ካናቢስ በሀገራችን በሰፊው ተጠቃሚ እንዳላቸው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

- ✓ እ.ኤ.አ. በ1995 ዓ.ም. በ25 በተመረጡ ከተሞች 3200 ተጠያቂዎች በተካተቱበት ጥናት/ Rapid Situation Assesement/ ጫት፣ አልኮል፣ ሲጋራና በአፍንጫ የሚሸተቱ ( ምሳሌ፣ ቤንዚን) በብዙ የህብረተሰብ ክፍል እንደሚዘወተሩ እና በተለይም እድሜአቸው ከ19-24 የሆኑ ወጣቶች በዚህ እድሜ እነዚህን አደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች መጠቀም እንደሚጀምሩ/Age of Initation/ መሆኑ ጥናቱ ይጠቁማል፡፡
- ✓ በ 4 በተመረጡ ከተሞች በ400 የጎዳና ተዳዳሪዎች በተካሄደው ጥናት 56.2% ጫት 51.9% አልኮል 46.8% ቤንዚንና 18% ካናቢስ(ሀሺሽ) ተጠቃሚ እንደሆኑ ጥናቱ ያመለክታል፡፡
- ✓ የአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ተጠቃሚነት ስርጭት እና ያለው ተፅዕኖ በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች/ Prevalence and Impact of Drug abuse among High school Students in Ethiopia/ 1999 እ.ኤ.አ. በ1780 ተማሪዎች ላይ በተካሄደው ጥናት 49.6% አልኮል፣ 40% ጫት፣ 20.7% ሲጋራና 11% ሀሺሽ ተጠቃሚ እንደሆኑ ጥናቱ ያመለክታል፡፡
- ✓ ከላይ የተጠቀሰው ጥናት እንደሚያመለክተው አብዛኞቹ ተማሪዎች 63.6 አደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች መጠቀም የጀመሩበት የእድሜ ክልል/ The age of drug experimentation/ ከ15-19 ዓመት እንደሆነ ያመለክታል፡፡
- ✓ ሰዎች በአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ያላቸው አመለካከት/Behavioural Survelance Survey/ ለማየት የተካሄደው ጥናት ከተካተቱት ተጠያቂዎች 2/3 ኛው ቢያንስ በሳምንት አንድ ጊዜ ጫትና አልኮል የሚጠቀሙ ሰዎች ቢያንስ በሳምንት አንድ ጊዜ ጥንቃቄ ያልተሞላበት( ያለኮንዶም) ከፆታ ጓደኛቸው ወይም ባለቤታቸው ውጭ ግብረስጋ ግኙኘነት እንደሚፈፅሙ ጥናቱ ያሰምርበታል፡፡
- ✓ ምንም እንኳ በሀገራችን አደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ከኤች አይ ቪ/ኤድስ ጋር ያላቸው ትስስር ምንያህል እንደሆነ የሚያሳይ የተጠና ጥናት ባይኖርም የችግሩ አሳሳቢነት ግን ጊዜ ሊሰጠው እንደማይገባ የሌሎች ሀገሮች ልምድና በሀገራችን በተደረጉ የተወሰኑ ጥናቶች በግልፅና በተጨባጭ ማየት ይቻላል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ህገ ወጥ ዝውውርና አጠቃቀምን የመከላከልና የመቆጣጠር ስልቶች

# መግቢያ

የአደገኛ መድኃኒቶችና ዕጾች ሕገወጥ ዝውውርና አጠቃቀም አስከፊ ገጽታን ለመከላከል የተለያዩ ስልቶችና አስትራቴጂዎች መጠቀም ያስፈልጋል:: አገሮች የተለያዩ ስልቶችና እስትራቴጂዎችን በመንደፍ ተግባራዊ በማድረግ ሲሰሩ ቢቆዩም ችግሩ እያንሰራራና እየሰፋ በመምጣት ላይ ይገኛል::

ማንኛውም የመከላከያ ዘዴ ከዚህ በታች በስዕሉ የተመለከቱትን ሁኔታዎች ዓላማ ያደረገ መሆን ይኖርበታል::




ከስዕሉ እንደምንገነዘበው ተጠቃሚ፣ አደገኛ መድኃኒትና እጽ እንዲሁም አካባቢ የተያያዙና አንዱ ከሌላው ተነጥሎ የማይታይ መሆኑን ነው:: አደገኛ መድኃኒቶችና እጾችን ሰዎች እንዳይጠቀሙ ለማድረግ ሁሉን ያካተተ ጥረት ያስፈልጋል:: በተጠቃሚው ላይ ብቻ ትኩረት ከተደረገ አደገኛ መድኃኒቶችና እጾች በአካባቢው አስካሉ ድረስ የምናካሂደው የመከላከል ጥረት ግቡን አይመታም:: እንዲሁም አደገኛ መድኃኒቶችንና እጾችን ከአካባቢው ለማስወገድ ብሎም ለማጥፋት የሚደረገው ጥረት ተጠቃሚ እስካለ ድረስ ፍላጎት ስለሚኖር ጥረቱ ውጤት አልባ ሆኖ ይቀራል:: በሌላ በኩል ተጠቃሚው አደገኛ መድኃኒቶችና እፆች እንዳይጠቀም ጥረት በማድረግና በአካባቢው እንዳይገኙ በመከላከል ብቻ ችግሩን ለማስወገድ አይቻልም::

ስለሆነም የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ሕገወጥ ዝውውርና አጠቃቀም አስከፊ ገጽታን ለመከላከል በስዕሉ በተጠቀሱት ሶስቱ አቢይ ሁኔታዎች ላይ ትኩረት በመስጠት የተለያዩ ስልቶችና ስትራቴጂዎች ሊነደፍ ይገባል:: ይህን መርህ መከተል ካልተቻለ የሚደረገው የመከላከል ጥረት ውጤታማ አይሆንም:: በመሆኑም የሚደረገውን ጥረት ከግብ ለማድረስና የሚፈለገውን ውጤት ለማግኘት፣

- የቁጥጥር
- የማስተማር
- የሕክምናና መልሶ ማቋቋም ተግባሮች፣ መካሄድ ይኖርባቸዋል፡፡

በዚህ ማንዋል የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ሕገወጥ ዝውውርና አጠቃቀም አስከፊ ገጽታን ለመከላከል የሚረዱ ስልቶች ከዚህ ቀጥሎ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና ድንጋጌዎች፣

ዓለም አቀፍ የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ቁጥጥርና ትብብር በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ እንደተጀመረ ይነገራል:: የመጀመሪያው እንቅስቃሴ እ.ኤ.አ. በ1909 ችግሩ ጎልቶ በታየበት ቀጠና በቻይና ሻንግሃይ የዓለም አቀፍ የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ዝውውር ቁጥጥር ኮንፍረንስ (First International Conference to Control Traffic of Drugs) ተካሄደ:: በዚህ ጉባኤ አሥራ ሶስት ሀገሮች ተካፍለው ነበር::

ይህ ጉባኤ የመጀመሪያው የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ቁጥጥር ስምምነት እንዲፈረም መንገድ ከፈተ:: በመሆኑም እ.ኤ.አ. በ1912 በኔዘርላንድ በሄግ ከተማ ዓለም አቀፍ የኦፒየም ስምምነት ተፈረመ:: ይህ ሰነድ ከሕክምና ውጪ ተገቢ ላልሆነ ተግባር ይውሉ የነበሩትን አደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ለመቆጣጠር ያስቻለ ነበር:: ከዚህ በኋላ ነበር የ1925፣ የ1931 እና የ1936 ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ሊፈረሙና የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ሕገወጥ አጠቃቀምን ይበልጥ ለመግታትና ለመቆጣጠር ጥረት የተደረገው::

የተባበሩት መንግስታት ከሊግ ኦፍ ኔሽንስ ሥልጣኑን ሲረከብ በርካታ ፕሮቶኮሎች በተለያዩ ጊዜያት ሲፈረሙና ስምምነት ላይ ሲደርሱ ቆይተዋል:: እ.ኤ.አ. በ1946፣ በ1948፣ እና በ1953 የተፈረሙት ፕሮቶኮሎች ምሣሌዎች ናቸው:: የነዚህ ፕሮቶኮሎችም መፈረም የአደገኛ መድኃኒቶችንና ዕጾችን ሕገወጥ ዝውውርና አጠቃቀምን ይበልጥ ለመቆጣጠርና ለመግታት ያስቻሉ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የናርኮቲክ መድኃኒት ኮሚሽን (UN Commission on Narcotic Drugs)፣ ቋሚ ማዕከላዊ ቦርድ (Permanent Central Board) ...ወዘተ በማቋቋም ፕ ሮቶኮሎቹንና ስምምነቶቹን ተግባራዊ ለማድረግ ተሞክሯል::

በአሁኑ ወቅት ዋንኛና ተቀዳሚ ሆነው የሚያገለግሉ ሦስት ዓለም አቀፍ የአደገኛ መድኃኒቶችና ዕጾች ቁጥጥር ስምምነቶችና አንድ ፕሮቶኮል ናቸው:: እነሱም:-

- እ.ኤ.አ. በ1961 የወጣው የናርኮቲክ መድኃኒቶች ስምምነት፣ (Single Convention on Narcotic Drugs, 1961)
- እ.ኤ.አ. በ1972 የ1961 የናርኮቲክ መድኃኒቶችን ስምምነት ያሻሸለው ፕሮ ቶኮል፣ (The 1972 Protocol Amending the Single Convention)
- እ.ኤ.አ. በ1971 የወጣው የሣይኮትሮፒክ መድኃኒቶች (Convention on Psychotropic Substances, 1971) እንዲሁም፣

- እ.ኤ.አ. በ1988 የወጣው የናርኮቲክና ሣይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ሕገወጥ ዝውውርን የሚገታው ስምምነት (Convention Against Illicit Traffic in Narcotic Drugs and Psychotropic Substances, 1988) ... ናቸው፡፡

የእነዚህን አራት ሰነዶች ይዘት በአጭሩ እንመልከት፣

## ሀ. እ.ኤ.አ. በ1961 የወጣው የናርኮቲክ መድኃኒቶች ስምምነት፣

በ1960ዎቹ በናርኮቲክ መድኃኒቶች ላይ የሚደረገው ቁጥጥር እያየለና እየተጠናከረ የመጣበት ወቅት ነበር፡፡ በመሆኑም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ስምምነቱ እንዲወጣ ግፊት ያደረገ ሲሆን የስምምነቱ መውጣት ዋንኛ ዓላማዎች፣

- ቀድሞ የነበሩትን ስምምነቶችና ኘሮቶኮሎች በአንድነት ለማጠቃለል፣
- የቁጥጥር አካላትን አሠራር አንድ ወጥ ለማድረግና ውስብስብነቱን ለማስቀረት፣
- ለናርኮቲክ መድኃኒት ጥሬ ዕቃ ሆነው የሚበቅሉ አደገኛ ዕፅዋት ላይ ጠበቅ ያለ ቁጥጥር ለማድረግ ነበር፡፡

በዚህም መሠረት ስምምነቱ ከዚህ በፊት የነበሩትን የተለያዩ ስምምነቶች አንድ ላይ አጠቃልሎ ሊይዝ ችሏል፡፡

ይህ ስምምነት ለመጀመሪያ ጊዜ በኮካና በካናቢስ አደገኛ እጾች ላይ ዓለም አቀፍ ቁጥጥር እንዲደረግና ኦኘየም የተባለውን አደገኛ እጽ ከሕክምና አገልግሎት ውጪ መጠቀምን አጥብቆ የከለከለ ሰነድ ነው፡፡ በተጨማሪም እንደ ኮኬይንና ሄሮይን የመሳሰሉ አደገኛ መድኃኒቶች ልዩ ቁጥጥር እንዲደረግባቸው ያስገነዘበ ነው፡፡

የስምምነቱ አንዳንድ ድንጋጌዎች ቀድሞ ከነበሩት ስምምነቶችና ኘሮቶኮሎች በይዘታቸው የተለዩና በተለይም የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ሱሰኞች የሕክምና እርዳታና ተሃድሶ እንዲያገኙ ይጠይቃል፡፡

ስምምነቱ በበርካታ ሀገሮች ተቀባይነትን በማግኘት የፀደቀ ሲሆን ሀገራችን ኢትዮጵያም ይህን ስምምነት ተቀብላ አፅድቃለች፡፡

## ለ.እ.ኤ.አ. በ1972 የወጣውና የ1961 የናርኮቲክ ስምምነትን ያሻሻለው ፕሮቶኮል፣

ይህ ኘሮቶኮል የ1961 የናርኮቲክ መድኃኒቶች ስምምነትን በማሻሻል ይበልጥ ያጠናከረና እ.ኤ.አ. ነሐሴ 8 ቀን 1975 የፀና ሰነድ ነው፡፡ ኘሮቶኮሉ የናርኮቲክ መድኃኒቶችን ሕገወጥ ዝውውርና አጠቃቀም እጅጉን ማውገዙና ይህንኑ መቆጣጠር የበለጠ ጥረት መደረግ ያለበት መሆኑን ያስገነዘበ ሰነድ ነው፡፡ በተለይ ደግሞ በዚህ ሰነድ የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ሕገወጥ ተጠቃሚዎችና አዘዋዋሪዎች አጥፊ ተብለው የእሥራት ቅጣት እንዲወሰንባቸውና ከእሥራቱ ቅጣት በተጨማሪ ትምህርት እንዲሰጣቸው፣ ተሃድሶና የማኀበራዊ ኑሮ ማሻሻያ ትምህርት እንዲደረግላቸው ያስገነዝባል፡፡

ኘሮቶኮሉ የዓለም አቀፍ ናርኮቲክ መድኃኒቶች ቁጥጥር ቦርድ አገሮች የገቡትን ግዴታ እንዲወጡ ግፊት እንዲያደርግ ከፍተኛ ኃላፊነት ሰጥቶታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ኘሮቶኮሉ ናርኮቲክ መድኃኒቶችን ለመቆጣጠር ዓለም አቀፋዊ ትብብር እንደሚያስፈልግ አጥብቆ ያስገነዘበ ነው፡፡

ይህን ስምምነት ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ አገሮች ተቀብለው አጽድቀውታል፡፡

## ሐ. እ.ኤ.አ. በ1971 የወጣው የሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ስምምነት፣

እስከ 1971 ዓለም አቀፍ ቁጥጥር ይደረግባቸው የነበሩት ናርኮቲክ መድኃኒቶች ብቻ ነበሩ፡፡ ሣይኮትሮፒክ መድኃኒቶች እንደ አንፌታሚንስ፣ ሄሎሲኖጂንስ፣ ወዘተ ... የመሳሰሉ ሰው ሠራሽ የሆኑና የሰውን ልጅ ባሕሪ በቀላሉ ሊቀይሩና ሱሰኛ ሊያደርጉ የሚችሉ አደገኛ መድኃኒቶች ሕገወጥ ዝውውርና አጠቃቀም በ1960ዎቹ መጨረሻ አሳሳቢ ሆነው በመገኘታቸው እ.ኤ.አ. የ1971 የሣይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ስምምነት በአስትሪያ (Austria) ቬይና በተጠራው ስብሰባ እንዲፀድቅ ምክንያት ሆነ፡፡

## መ. እ.ኤ.አ. በ1988 የወጣው የናርኮቲክና የሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ህገ ወጥ ዝውውርን ለመግታት የወጣው ስምምነት፣

የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ዝውውር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ በመምጣት የአንድ ሀገር ብቸኛ ችግር ከመሆኑ አልፎ ድንበር ዘለልና ዓለም አቀፋዊ ችግር ከሆነ ውሎ አድሯል:: በመሆኑም ችግሩን ለመግታት ዓለም አቀፋዊ ትብብር አስፈላጊ ሆኗል::

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዓለም አቀፋዊ ትብብርን ለማስፋት እ.ኤ.አ. በ1988 የናርኮቲክና ሣይኮትሮፒክ መድኃኒቶችን ሕገወጥ ዝውውር ለመግታት ስምምነት አወጣ::

በዚህ ስምምነት የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ሕገወጥ አዘዋዋሪዎችን ነፃ እንቅስቃሴ ለመግታት የሚያስችሉ አንቀጾች ተቀምጠዋል:: 34 አንቀጾች ያሉት ይህ ሰነድ በተለይም በሕገወጥ አደገኛ መድኃኒትና ዕጽ ንግድ የተካበተ ሀብትና ንብረት መውረስ ተቀዳሚ ተግባር መሆኑን ያስገነዝባል:: በዚህ መሠረት ፍርድ ቤቶች የባንክን፣ የፋይናንስን፣ የንግድ ሪኮርዶችን የመበርበርና የመያዝ መብት የተሰጣቸው በመሆኑ የባንኮች ሰነድ ምስጢር ነው የሚለው አባባል ተቀባይነት እንደሌለው ተመልክቷል::

በሰነዱ በርካታ የመድኃኒቶችና እጾች ዝውውር ድርጊቶች የወንጀል ድርጊት መሆናቸውና ቅጣትም እንደሚያስከትሉ በግልጽ የተደነገገ ሲሆን በተለይም ወንጀለኛን አሳልፎ ስለመስጠት ስምምነት እንዲሁም በአንድ ሀገር የተጀመረ ምርመራ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ወደ ሌላ ሀገር የሚተላለፍበትን ሁኔታ አባል ሀገሮች ሁሉ እንዲፈራረሙና ተግባራዊም በማድረግ ዓለም አቀፋዊ ችግሩን መዋጋት እንዳለባቸው በጥብቅ ያስገነዘበ ሰነድ ነው:: ከሁሉም በላይ በዚህ ሰነድ የናርኮቲክና ሣይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ፍላጎት ቅነሳ እንዲጠናከር አባል ሀገሮችን ቃል ያስገባ ሰነድ ነው፡ ሰነዱን ብዙ አገሮች ተቀብለው አጽድቀውታል:: አገራችን ኢትዮጵያም ስምምነቱን ተቀብላ ለተግባራዊነቱ ጥረት በማድረግ ላይ ትገኛለች::

ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው የዓለም አቀፍ ስምምነቶች ዓላማ አደገኛ መድኃኒቶችና እጾች በሕገወጥ መንገድ ጥቅም ላይ እንዳይውሉ አገሮች በቅንጅት እንዲሰሩ ከመርዳታቸው ባሻገር በአንድ ዓላማ ጥላ ሥር እንዲራመዱ ያደርጋል:: ስለሆነም የዓለም አቀፍ ስምምነቶችን መቀበል በአገሮች መካከል የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ሕገወጥ እንቅስቃሴን ለመከላከል የመረጃ ልውውጥና የሥራ ቅንጅት ለማጠናከር በጣም አስፈላጊ ነው::

## ሠ. የትምባሆ ዝግጅቶችን ለመቆጣጠር የወጣ አለማቀፍ ድንጋጌ/Frame Work Convention on Tobacco Control/

እ.ኤ.አ. ግንቦት 21/2003 በ56ኛው የአለም የጤና ድርጅት ጉባኤ ላይ ሁሉም የተ.መ.ድ አባል ሀገሮች በተገኙበት የትምባሆ ዝግጅቶችን ለመቆጣጠር የሚያስችል አለማቀፍ ድንጋጌ ፀደቀ፡፡ ይህ ድንጋጌ ለአለም ህዝቦች ጤና ትልቅ የመሰረት ድነጋይ የጣለ ሲሆን የአለም የጤና ድርጅትም ግቦቹን ለመምታት የሚያስችል አይነተኛ መሳሪያ አድርጎ ይቆጥረዋል፡፡

የድንጋጌው ዋና አላማ የትምባሆ ዝግጅቶችን በመጠቀምና ለሁለተኛ ወገን ጭስ በመጋለጥ ምክንያት በህብረተሰብ ጤና፣ ማህበራዊ ኑሮ፣አካባቢያዊ እንዲሁም የኢኮኖሚ ላይ የሚደርሰውን አሰቃቂ ችግር ለመቀነስ ሲሆን አባል ሀገራት ድንጋጌውን ተግባራዊ በማድረግ ይህንን አሳሳቢ ችግር እንዲከላከሉ ያስቀምጣል፡፡

ድንጋጌው በዋናነት ሁለት ዋና ዋና መርሆችን የያዘ ሲሆን እነሱም የትምባሆ ዝግጅቶች አቅርቦት ቅነሳ እና የትምባሆ ዝግጅቶች ፍላጎት ቅነሳ ናቸው፡፡ በኮንቬንሽኑ ውስጥ ከ አንቀፅ 6-14 የተቀመጡት ስለትምባሆ ዝግጅቶች ፍላጎት ቅነሳ የሚገልጹ ሲሆን የሚከተሉትን እንደ አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡

- ✓ ከቀረጥና ዋጋ ጋር የተያያዙ እርምጃዎች
- ✓ ከቀረጥና ዋጋ ጋር ተያያዥ ያልሆኑ እርምጃዎች
- ✓ ህብረተሰቡን ከሁለተኛ ወገን ጭስ የመከላከል እርምጃዎች
- ✓ የትምባሆ ዝግጅቶችን ንጥረ ነገር ይዘት የመቆጣጠር እርምጃዎች
- ✓ የትምባሆ ዝግጅቶችን አሥተሻሸግና ገላጭ ፅሁፍ የመቆጣጠር እርምጃዎች
- ✓ ለህብረተሰቡ ስለትምባሆ ዝግጅቶች ጉዳት የማስተማርና ግንዛቤ የመጨመር እርምጃዎች
- ✓ የትምባሆ ማስተዋወቅና ስፖንሰርን የመቆጣጠር እርምጃዎች እና የመሳሰሉት ሲሆኑ ከአቅርቦት ቅነሳ ጋር ተያያዥ የሆኑ የሚባሉት ደግሞ፡-
    - ○ የትምባሆ ዝግጅቶችን ህገወጥ ንግድና ዝውውር መግታት

- የትምባሆ ዝግጅቶች ለህጻናትና በህፃናት እንዳይሸጡ መቆጣጠርን
- እንዲሁም በትምባሆ የሚተዳደሩ ሰዎችን መደገፍን የሚያጠቃልሉ ናቸው፡፡

ይህን ድንጋጌ እስካሁን 174 የሚሆኑ የአለም ሀገራት አፅድቀው የሀገራቸው የህግ አካል ያደረጉት ሲሆን በአፈሪካ 9 ሀገሮች አላፀደቁትም፡፡ ኢትዮጵያ ድንጋጌውን ካላፀደቁት 9 የአፍሪካ ሀገሮች አንዷ ናት፡፡

## ረ.የተ.መ.ድ. አባል አገራት ህጎች

በአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ሕገወጥ ዝውውር የተሰማሩ ሰዎች ዕለት ከዕለት የሚፈጽሟቸውን የወንጀል ተግባራት በመቋቋሙና ተጠያቂ በማድረጉ ፣ እንዲሁም ጥፋተኛ ሆነው ሲገኙ የሚወሰንባቸው ቅጣት መጠን ማነስ መለያየት እና ወጥነት ያለው አሠራር አለመስፈን ምክንያት ስምምነቶቹን በማስፈጸሙ ረገድ ካጋጠሙት ችግሮች መካከል ሊጠቀሱ ከሚችሉት ዋና ዋናዎቹ እንደሆኑ የተ.መ.ድ. ጥናታዊ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በአንፃሩ የተ.መ.ድ. ድራግ ኮንትሮል ኘሮግራም (UNDCP) በአንድ ወቅት ካሰራጨው ሪፖርት መረዳት እንደተቻለው ፣የ47 የሚሆኑ ሀገሮች ሕጐች ከፍተኛ አደጋ የሚያስከትሉ ዕፆችን/መድኃኒቶችን፤

1. ከሀገር ሀገር ሲያዘዋውር የተገኘ (International Trafficking)......... 15 ዓመት እስራት
2. በአንድ ሀገር ክልል ሲያዘዋውር የተገኘ (National Trafficking)....10 ዓመት እስራት፣
3. አሳልፎ ለሌላ ሰው በመስጠት እንዲጠቀም የገፋፋ/ያበረታታ........ 5 ዓመት እስራት፣
4. ለሌላ ሰው በመስጠት ወንጀል እንዲፈጽም ያበረታታ ................. 2 ዓመት እስራት፣

የቅጣት ድንጋጌዎች ያሏቸው መሆናቸውን ያስረዳል፡፡

በአንዳንድ ሀገሮች በተለይም አደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆችን ማምረት ፣ ማዘዋወር፣ ይዞ መገኘት እንዲሁም በግል መጠቀም እስከ ሞት የሚያደርስ ቅጣት የሚያስከትሉ ሲሆን ለዚህም የሚከተሉት የ15 አገሮች ልምድ ከዚህ በታች በሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡

* High risk drugs (ለምሳሌ ኮኬይን፣ ሞርፊን፣ ፔቲዲን፣ ኦፒየምና ኮዴይን)

| ተ. ቁ | የሀገሩ ስም | የወንጀሉ ዓይነት | | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ማምረት | ማዘዋወር | ይዞ መገኘት | መጠቀም | |
| 1 | ግሪክ | እድሜ ልክ | እድሜ ልክ | እድሜ ልክ | ከ2 እስከ 5 ዓመት | |
| 2 | ቱርክ | ሞት | - | - | - | |
| 3 | አውስትራሊያ | እድሜ ልክ | እድሜ ልክ | እድሜ ልክ | - | |
| 4 | ብሪታንያ | - | እድሜ ልክ | እድሜ ልክ | - | |
| 5 | ስሪላንካ | እድሜ ልክ ወይም ሞት | እድሜ ልክ ወይም ሞት | እድሜ ልክ | - | |
| 6 | ግብፅ | ሞት | እድሜ ልክ ወይም ሞት | - | ከ3 እስከ 5 ዓመት | |
| 7 | ናይጀሪያ | እድሜ ልክ | - | - | - | |
| 8 | ኢንዶኔዥያ | እድሜ ልክ | እድሜ ልክ ወይም ሞት | እድሜ ልክ | - | |
| 9 | ሳውድ አረቢያ | - | ሞት | እድሜ ልክ | - | |
| 10 | ታይላንድ | - | - | እድሜ ልክ | ከ 1 እስከ 15 ዓመት | |
| 11 | ጃፓን | - | - | እድሜ ልክ | - | |
| 12 | ቬኑዙላ | ከ10 እስከ 20 ዓመት | - | እድሜ ልክ | - | |
| 13 | ኮሎምቢያ | ከ4 እስከ 12 ዓመት | - | - | - | |
| 14 | ኮስታሪካ | - | - | እድሜ ልክ | - | |
| 15 | ብራዚል | - | ከ3 እስከ 15 ዓመት | - | - | |

- ይህ ስለቅጣቱ መጠን መረጃ ያልተገኘለትን የወንጀል ድርጊት ለማመልከት ነው።

# ምዕራፍ ሁለት

# የአገራችን ህጎች

አገራችን ኢትዮጵያ ከላይ የተመለከቱትን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ከአለም አቀፉ የትምባሆ ድንጋጌ በስተቀር ካፀደቀች አገሮች አንዷ እንደሆነች ከላይ ተገልጿል። በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግስት አንቀጽ 9(4) መሠረትም ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የአገሪቱ ሕግ መሆናቸው ተደንግጓል።

በዓለም አቀፍ ስምምነቶቹ ያሉ ግዴታዎችን በአግባቡ ለመወጣትም በእያንዳንዱ ስምምነቶቹን በተቀበለ አገር መንግስት ሊወስዱ የሚገባቸው የአፈጻጸም እርምጃዎች ያሉ ሲሆን፣ ከእነዚህ መካከልም አደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆችን ማብቀል፣ ማምረት/መፈብረክ፣ ዝውውር፣ ንግድ እና አጠቃቀምን የሚመለከቱ ሕጎችን ማውጣትና ተፈጻሚ ማድረግ የሚሉት በዋነኝነት የሚጠቀሱ ይሆናሉ።

በዚሁም መሠረት አገራችን ከላይ በተጠቀሱት የአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆችን ሕገወጥ ምርት ፣ ዝውውርና አጠቃቀም በተመለከተ ያሉ ግዴታዎችን ለመወጣት ሕጎችን በማውጣት ተግባራዊ በማድረግ ላይ ትገኛለች።

ለዚህም አገሪቱ ያሏትና ቀደም ብሎ ሲሰራባቸው የነበሩና በአሁኑ ወቅት እየተሰራባቸው ያሉት ሕጎች፣ በ1949 የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ እና የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ 661/2002 ሲሆኑ፣ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ በርካታ ዓመታትን ያስቆጠረ፣ በዓለም አቀፍ ስምምነቶቹ የተመለከቱትን የወንጀል ተግባራት በተሟላ ሁኔታ ያላካተተና የቅጣቱም መጠን አነስተኛ በመሆኑ ምክንያት በአፈጻጸም ረገድ ከፍተኛ የሆኑ ችግሮች የነበሩት ስለ መሆኑ በዚሁ ዘርፍ ያሉ ጉዳዮች በሚመለከቷቸው የቁጥጥር እና የፍትሕ አካላት በሚገባ ይታወቃል።

በመሆኑም ሕጉ፣ የነበሩበትን የአፈጻጸም ችግሮች በማጤን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት በ1996 ዓ.ም መጨረሻ ላይ ባፀደቀው አዲስ የወንጀል ሕግ እንዲተካ ተደርጓል።

ይኸው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ ከግንቦት ወር 1997 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ ውሏል።

ቀጥለንም ዓመታት ያስቆጠረውን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የተካውን የወንጀል ሕግ እና የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ 661/2002 አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች በአጭሩ ለማየት እንሞክራለን::

## ሀ. አዲሱ የወንጀል ህግ

## 1. ስለናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶችና ዕፆች ህገወጥ አመራረት፣ዝውውርና አጠቃቀም

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ ያለ ልዩ ፈቃድ መርዛማ ነገሮችን ወይም የናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶችን ወይም ዕፆችን ማምረት ወይም መሥራት እንዲዘዋወሩ ማድረግ የተከለከለና በወንጀል የሚያስቀጣ ድርጊት መሆኑን ይደነግጋል::

የወንጀል ሕጉ፣ አንቀጽ 525 እንደሚከተለው የሚነበብ ሆኖ እናገኘዋለን፣

1) ማንም ሰው ሕጋዊ ልዩ ፈቃድ ሳይኖረው ፣

ሀ) መርዛማ ነገሮችን ወይም ናርኮቲክ ወይም ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶችን ወይም እጾችን ያቀበለ፣ ያመረተ፣ የሠራ፣ የለዋወጠ ወይም የፈበረከ፣

ለ) ከላይ በፊደል (ሀ) ከተዘረዘሩት ነገሮች አንዱን ይዞ የተገኘ፣ ወደ አገር ያስገባ፣ ወደ ውጭ አገር የላከ፣ ያጓጓዘ፣ ያከማቸ፣ የደለለ፣ የገዛ፣ ለሽያጭ ያቀረበ፣ የለዋወጠ፣ ያሰራጨ፣ ያዘዋወረ፣ አሳልፎ የሰጠ ወይም ለሌላ ያስገኘ፣

ሐ) ከዚህ በላይ በፊደል (ሀ) ከተዘረዘሩት ነገሮች አንዱን ለማምረት፣ ለማቀነባበር ወይም ለመፈብረክ የሚያገለግሉ መሣሪያዎችን የሠራ፣ ይዞ የተገኘ፣ ወደ አገር ውስጥ ያስገባ ወይም ወደ ውጭ አገር የላከ፣ ወይም

መ) በፊደል (ሀ) ለተገለጹት ነገሮች መሥሪያነት፣ ማቀነባበሪያነት፣ ማምረቻነት፣ መሸጫነት፣ ወይም ማከፋፈያነት ባለቤት ወይም ባለይዞታ የሆነበትን ቤቱን ፣ ግቢውን ወይም ቦታውን የሰጠ፣ ያከራየ ወይም የፈቀደ እንደሆነ፣ ከአምስት ዓመት በማያንስ ጽኑ እስራትና እስከ አንድ መቶ ሺህ ብር ሊደርስ በሚችል መቀጮ ይቀጣል፣

ከላይ በተመለከተው የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 525 (1) ከፊደል (ሀ) እስከ (መ) የተዘረዘሩት የናርኮቲክ ወይም ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ሕገወጥ ንግድ ሥራ እንቅስቃሴዎችን የሚመለከቱ የወንጀል ተግባራት ሲሆኑ፣ ማንም ሰው በቅድሚያ አግባብነት ካለው የመንግስት አካል ልዩ ፈቃድ ሳይኖረው የትኛውንም ድርጊት የፈፀመ እንደሆነ በንዑስ አንቀጹ የተመለከተው ቅጣት ይፈፀምበታል ማለት ነው፡፡

2) ቅጣቱ ከአሥር ዓመት የማያንስ ፅኑ እሥራትና እስከ ሁለት መቶ ሺህ ብር የሚደርስ መቀጮ የሚሆነው፣

ሀ) ወንጀሉ የተፈፀመው ለዚሁ ንግድ ወይም በዓለም አቀፍም ሆነ በሀገር ደረጃ ወንጀል ለመፈፀም በተደራጀ ቡድን ወይም ማህበር አባል በሆነ ወይም ይህንኑ ሕገወጥ ድርጊት ሙያው አድርጐ የያዘ ሰው እንደሆነ፣

ለ) ጥፋተኛው የተከለከለውን ሕገወጥ ነገር ወይም የመጠቀሚያ ቦታ እያወቀ የሰጠው ወይም የፈቀደው በአፍቅሮ ነዋይ ፣ በወራዳነት ወይም አግባብ በሌለው ሌላ አላማ እንደሆነ፣ ተጠቃሚው ሕጻን ለአካለ መጠን ያልደረሰ ወጣት ወይም የአእምሮ በሽተኛ ወይም የእጽ ሱስ ያለበት እንደሆነ፣

ሐ) ወንጀለኛው ወንጀሉን የፈፀመው ሕጻናትን ወይም የአእምሮ በሽታ ያደረበትን ሰው ለወንጀል ድርጊቶቹ አፈጻጸም መጠቀሚያ በማድረግ እንደሆነ፣

መ) ወንጀለኛው ወንጀሉን የፈፀመው በማረሚያ ቤት ፣ በትምህርት ቤት ወይም በሌላ ማህበራዊ አገልግሎት ተቋም ቅጥር ግቢ ውስጥ ወይም ህጻናት እና ወጣት ተማሪዎች ለትምህርት፣ ለስፖርት ወይም ለሌሎች ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች በሚጠቀሙበት ቦታ እንደሆነ ወይም፣

ሠ) ወንጀለኛው ከዚህ ቀደም በፈፀመው ተመሳሳይ ወንጀል ምክንያት የጥፋተኛ ነት ውሳኔ ተላልፎበት የነበረ እንደሆነ፣ ነው ይላል፡፡

በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከፊደል (ሀ) እስከ (ሠ) ድረስ በዓለም አቀፍ ስምምነቶች የተመለከቱት የቅጣት ማክበጃ ሁኔታዎች የተካተቱ ሲሆን ወንጀሉ የተፈፀመው ለመርዛማ ወይም ናርኮቲክ ወይም ሣይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ሕገወጥ ንግድ በተደራጀ ቡድን ወይም አባል እንደሆነ ወይም ለወንጀሉ አፈጻጸም ሕጻናትን ወይም የአእምሮ በሽታ ያደረበትን ሰው መጠቀሚያ በማድረግ ወይም እንደትምህርት ቤቶችና በመሳሰሉ ሕጻናትና ወጣት ተማሪዎች ለትምህርት ፣ ለስፖርት

ወይም ለሌሎች ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች በሚጠቀሙበት ቦታ ወይም ቅጥር ግቢ ወዘተ እንደሆነ የቅጣት ማክበጃ ሁኔታዎቹ ወንጀሉን በፈፀመው ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ ማለት ነው:: ሕጻናትና ለአካለ መጠን ያልደረሱ ወጣቶች ከላይ ከተመለከቱት የትኛውንም የወንጀል ድርጊት የፈፀሙ እንደሆነ በወንጀል ሕጉ የሚስተናገዱት ከዚህ በታች በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት ይሆናል::

ዕድሜያቸው ዘጠኝ ዓመት ያልሞላ «ሕፃናት» የሚያስቀጣ ወንጀል ቢፈጽሙም ቤተዘመዶቻቸው ፣ አስተማሪዎቻቸው፣ አስተዳዳሪዎቻቸው ወይም ሌሎች አግባብነት ያላቸው አካላት ተገቢ የሆኑ ጥንቃቄዎችን እንዲያደርጉላቸው ከማድረግ በስተቀር ለፈፀሙት የወንጀል ድርጊት ኃላፊዎች ሆነው አይቆጠሩም:: (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 52)

- ዕድሜያቸው ከዘጠኝ ዓመት እስከ አሥራ አምስት ዓመት የሞላቸው ወጣቶች ወንጀል የፈፀሙ እንደሆነ የሚወሰኑባቸው ቅጣቶች እና የጥንቃቄ እርምጃዎች በወንጀል ሕጉ ተለይተው የተቀመጡት ይሆናሉ:: ለአዋቂ ጥፋተኞች የተደነገጉት መደበኛ ቅጣቶች ለወጣት የወንጀል አድራጊዎች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም:: ወጣት ወንጀል አድራጊዎች ከአዋቂዎች ጋር አይታሰሩም፣ (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 53)፣

- ዕድሜያቸው ከ15 ዓመት በላይ ፣ ከ18 ዓመት በታች ያሉ ወጣት ወንጀል አድራጊዎች የፈፀሙት የወንጀል ድርጊት የሚታየው በሕጉ ላይ በተመለከቱት መደበኛ ድንጋጌዎች መሠረት ቢሆንም፣ ቅጣት የሚወሰንባቸው ከወጣትነት ዕድሜያቸው መጠን፣ ሊታረሙ ያለመቻልና የአደገኛነቱን፣ ዓመሉ ሊሻሻል የሚችልበት ዕድል የሚኖረው መሆን አለመሆኑን በማገናዘብ መደበኛ የቅጣት ማቅለያ ድንጋጌዎችን (አንቀጽ 179) ወይም እንደአግባብነቱ ለአካለ መጠን ላልደረሱ ወንጀለኞች የተመደበውን የልዩ ቅጣት አወሳሰን (ከአንቀጽ 166-168) በመከተል ይሆናል::

ማንም ሰው ከላይ በንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) በተገለፁት ድርጊቶች በቀጥታ ተሳታፊ ባይሆንም ሁኔታውን እያወቀ በንዑስ አንቀጾቹ የተመለከቱትን የወንጀል ድርጊቶች የፈፀመ እንደሆነ በወንጀል የሚቀጣ እንደሚሆን በአንቀጽ 526 ተደንግጓል:: የአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ (3) እንደሚከተለው ይነበባል፣

«ማንም ሰው መርዛማ ነገሮች ወይም ናርኮቲክ ወይም ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ወይም ዕፆች የተገኙት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) ከተዘረዘሩት የወንጀል ተግባሮች በአንዱ አማካይነት መሆኑን ወይም ከተዘረዘሩት የወንጀል ተግባሮች አንዱን ለመፈፀም የታቀዱ

መሆኑን እያወቀ ፣ እነዚህን ነገሮች ይዞ የተገኘ ፣ ያጓጓዘ ፣ ያከማቸ ወይም አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ፣

ከአምስት ዓመት በማያንስ ፅኑ እሥራትና እስከ አንድ መቶ ሺህ ብር ሊደርስ በሚችል መቀጮ ይቀጣል»

በሌላ በኩል ከዚህ በላይ ባሉት ንዑሳን አንቀጾች ከተገለፁት ምክንያቶች ውጭ ባለ ሁኔታ፣ ማንኛውም ሰው ራሱ ወይም ሌላ ሰው በግሉ እንዲጠቀምበት በማሰብ የተከለከሉትን ነገሮች በተመለከተ ለፈፀመው ወንጀል የሚቀጣበት ሁኔታ በአንቀጽ 525 ተደንግጓል:: ንዑስ አንቀጽ (4) እንደሚከተለው ይነበባል፣

«ማንም ሰው፣

ሀ) ራሱ ወይም ሌላ ሰው በግል እንዲጠቀምበት በማሰብ፣ ከላይ በንዑስ አንቀጽ (1) የተገለፁትን ነገሮች ያበቀለ፣ የገዛ፣ የተቀበለ፣ የሠራ፣ ይዞ የተገኘ፣ የሸጠ ፣ የሰጠ ወይም፣

ለ) በእነዚህ ነገሮች ያለሐኪም ፈቃድ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ የተጠቀመ ወይም ሌላ ሰው እንዲጠቀምባቸው ያደረገ እንደሆነ እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራትና እስከ ሃምሳ ሺህ ብር ሊደርስ በሚችል መቀጮ ይቀጣል፣

5) ናርኮቲክ ወይም ሳይካትሮፒክ ነገሮችን ለሕገወጥ ዓላማ ሲል የሕክምና ባለሙያን በማጭበርበር የመድኃኒት ማዘዣው እንዲጻፍለት ያደረገ ወይም በዚህ ሕገወጥ መንገድ ያገኘውን ማዘዣ ላልተፈቀደለት ሶስተኛ ወገን ያስተላለፈ ሰው ወይም አስቦ ሕገወጥ የመድኃኒት ማዘዣ የፃፈ የሕክምና ባለሙያ፣

እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል:: አንቀጽ (525 (5) )

በዚህ ንዑስ አንቀጽ ድንጋጌ መሠረትም ማንኛውም ሰው የመድኃኒት ማዘዣው በሕገወጥ መንገድ እንዲፃፍለት በማድረግም ሆነ ይህንኑ በሕገወጥ መንገድ ያስፃፈውን የመድኃኒት ማዘዣ ለሌላ ላልተፈቀደለት ሶስተኛ ወገን በማስተላለፍ እንዲሁም አስቦ ሕገወጥ የመድኃኒት ማዘዣውን በመፃፍ የሚፈፀመው የወንጀል ድርጊት ለሕገወጥ ዓላማ በማሰብ መሆኑ ከተረጋገጠ በንዑስ አንቀጹ የተመለከተው ቅጣት የሚፈፀምበት ይሆናል ማለት ነው::

የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 525 (6)፣ ደግሞ በዚህ ሕግ ለመንግስት ገቢ ሊሆን ስለሚገባው ሀብት (አንቀጽ 140) እና በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ስለማቅረብና በወንጀሉ ስለመርዳት (አንቀጽ 684) የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ናቸው» በሚል ወደ ሌሎች የሕጉ አንቀጾች የሚመራ ሆኖ እናገኘዋለን::

ይህም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 525 (1) እስከ (5) የተደነገጉት የወንጀል ቅጣቶች በዚሁ ሕግ አንቀጽ 140 እና አንቀጽ 684 የተደነገጉትን ተፈጻሚነት የሚያስቀሩ አለመሆናቸውን የሚያስገነዝበን ድንጋጌ ነው::

- የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 140 (1) እንደሚከተለው ይነበባል፣ «ወንጀልን ለመፈፀም ሊያገለግሉ የሚችሉ ወይም ለወንጀል ተግባር ያገለገሉ ወይም የወንጀል ተግባር ፍሬ የሆኑ ማናቸውም ነገሮች የሕዝብን ሰላማዊ ኑሮ ሥርዓትን፣ ጤናን ወይም መልካም ጠባይን ሊጐዱ የሚችሉ ሲሆኑ ፍርድ ቤቱ እንዲወረሱ ያዛል፣

- የተወረሱት ነገሮች እንዲጠፉ፣ ከአገልግሎት ውጭ እንዲሆኑ ወይም ለፖሊስ ወይም ለወንጀል ምርመራ ክፍል እንዲሰጡ ፍ/ቤቱ ለማዘዝ ይችላል::

- በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብና በወንጀሉ መርዳት የተከለከሉና የተፈፀሙ እንደሆነም ከባድ የወንጀል ቅጣት የሚያስከትሉ የወንጀል ተግባራት ስለመሆናቸው ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 684 ድንጋጌዎች መገንዘብ እንችላለን:: የአንቀጽ 684 (1) እና (2) እንደሚከተለው የሚነበቡ ሆነው እናገኛቸዋለን፣

«1) ማንም ሰው በሙስና ፣ በአደንዣዥ ዕፅ ወይም መድኃኒት ዝውውር፣ በሕገወጥ የጦር መሣሪያ ንግድ፣ በአሸባሪነት ተግባር ወይም በማናቸውም ተመሣሣይ ከባድ ወንጀል አማካኝነት ያገኘውን ገንዘብ ወይም ንብረት ሕገወጥ አመጣጥ ሰውሮ በጥቅም ወይም በሥራ ላይ በማዋል ፣ በማዛወር ፣ ወይም በማስተላለፍ ሕጋዊ አስመስሎ ያቀረበ እንደሆነ፣

ከአምስት እስከ አስራ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ፅኑ እስራትና እስከ መቶ ሺህ ብር ለመድረስ በሚችል መቀጮ ይቀጣል::

2) ማንም ሰው በንዑስ አንቀጽ (1) ከተመለከቱት የወንጀል ድርጊቶች በአንዱ የተገኘ መሆኑን እያወቀ፣ ሕገወጥ የሆነ ገንዘብ ወይም ንብረት የለወጠ፣ ያስተላለፈ ፣ የተቀበለ፣ ይዞ የተገኘ

ወይም በዚሁ ገንዘብ ወይም ንብረት የተጠቀመበት እንደሆነ ከላይ በንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው ቅጣት ይቀጣል፡፡»

ይህን አንቀጽ ከላይ በአንቀጽ 525 ሥር ከተመለከቱት ፍፁም የተለየ የሚያደርገው በ1949 በወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ጭራሹንም ያልተካተተ እና በአሁኑ ወቅት በመላው ዓለም እየተንሰራፋ ያለውን የገንዘብ ማጽዳት (Money laundering) የወንጀል ድርጊት የሚመለከት መሆኑ ነው፡፡ በአንቀጽ 684 ስያሜና በዝርዝር የተመለከቱት የወንጀል ተግባራት በአመዛኙ ተያያዥነት ባለው ሁኔታ የሚፈፀሙ እና ጥብቅ ቁርኝትም ያላቸው ስለመሆኑ ልንገነዘበው የሚገባን ጉዳይ ነው፡፡

በአጠቃላይም አንቀጽ 684 ስድስት ንዑሳን አንቀጾች ያሉት ሲሆን ፣ በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በዋና ወንጀል አድራጊነት ተጠያቂ ከሚሆነው በተጨማሪ ድርጊቱን እያወቀ ሕገወጡን ገንዘብ ወይም ንብረት የለወጠ፣ ያስተላለፈ፣ የተቀበለ፣ ይዞ የተገኘ ወይም በዚሁ ገንዘብ ወይም ንብረት የተጠቀመ፣ ለፖሊስ ያላስታወቀ ወይም ምርመራውን ያስናከለ ወዘተ ሰውም እንዲቀጣ የሚያደርግ ነው፡፡

## 2. ስለ አልኮል መጠጦች

ምንም እንኳን ከላይ በተመለከቱት ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ያልተካተተ ቢሆንም አልኮሆል መጠጦችን ያለአግባብ መጠቀምን በተመለከተ ቁጥጥር (ክልከላ) ለማድረግ በተለያዩ አገሮች ጥረቶች ሲደረጉ የቆዩ ስለመሆናቸው ጥናታዊ መረጃዎች ይጠቀማሉ፡፡

በአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ላይ የሚደረገው ቁጥጥርም አልኮሆል፣ ትምባሆና የትምባሆ ውጤቶችንም ሊያካትት ይገባል የሚሉ አመለካከቶችም አሉ፡፡

ይኸውም አደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች የሚባሉት ደረጃቸው ቢለያይም በሰው ልጅ አእምሮ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ወይም አእምሮን የሚለውጡ ነገሮች ሁሉ ሊያካትቱና በአደገኛነት ለመፈረጅም የሚያደርሱትን አካላዊና አእምሮአዊ ጉዳት ከግምት ውስጥ በማስገባት ሊሆን ይገባዋል፡፡ ከዚህም አንፃር በሰው ልጅ ላይ አካላዊም ሆነ አእምሮአዊ ጉዳት በማስከተልም ሆነ ፣ ለወንጀሎች መስፋፋትና መበራከት ምክንያት በመሆኑም ረገድ፣ የአልኮሆልና ትምባሆ ሕጋዊ ወይም ቁጥጥር የማይደረግባቸው ሆኖ መቆየት አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ ጥናታዊ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

ይህ እንዳለ ሆኖ፣ እ.ኤ.አ. በ2003 በትምባሆና ትምባሆ ውጤቶች ዝውውርና አጠቃቀም ላይ ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል ዓለም አቀፍ ስምምነት በዓለም የጤና ድርጅት (WHO) ተዘጋጅቶ በመንግሥታት መካከል ተፈርሟል፡፡

አገራችን ኢትዮጵያም እስካሁን ዝርዝር የአፈጻጸም ሕግ ያላወጣች ቢሆንም ስምምነቱን ግን እ.ኤ.አ. በ2004 ተቀብላዋለች፡፡ የአልኮል መጠጦችን በተመለከተ ግን በየአገሮች ከሚደረግ የተናጠል ጥረት ያለፈ የዓለም አቀፋዊነት ገፅታን የተላበሰ ስምምነት የለም፡፡

በእኛ አገር ግን አልኮሆል መጠጦችን ያለአግባብ መስጠትም ሆነ መጠጣት ክልክል ስለመሆኑ በወንጀል ሕጋችን የተደነገገና በአልኮሆል ወይም በእስፒርቶ መጠጦች የሌላውን ሰው ጤንነት ለአደጋ ማጋለጥ በወንጀል የሚያስቀጣ ተግባር ነው፡፡

የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 531 እንደሚከተለው ይደነግጋል፣

1) ማንኛውም ሰው አስቦ የመጠጦች ዓይነት ወይም ብዛት የሚጐዳ መሆኑን እርግጠኛ የሆነውን ወይም ሊጐዳ የሚችለውን አልኮሆል ወይም እስፒርቶ ያለባቸውን መጠጦች አካለ መጠን ላልደረሰ ወጣት ወይም ከልክ አሳልፎ የጠጣ መሆኑ በግልጽ ለታወቀ ሰው፣ የአልኮሆል ወይም የእስፒርቶ መጠጥ በማቅረብ ወይም በመስጠት ወይም እንዲቀርብ ወይም እንዲሰጥ በማድረግ የሌላውን ሰው ጤንነት ለአደጋ ያጋለጠ እንደሆነ፣እስከ አንድ ዓመት ሊደርስ በሚችል ቀላል እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል» ይላል፣

ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው አካለ መጠን ያልደረሱ ወጣቶች አልኮሆል መጠጣት የማይፈቀድላቸው መሆኑን፣ ማንኛውም አልኮሆል ጠማቂም ሆነ ሻጭ ሊጐዳ የሚችልን ወይም እስፒርቶ ያለበትን መጠጥ አካለ መጠን ላልደረሰ ወጣት መስጠት በወንጀል እንደሚያስቀጣው ነው:: ይህ የወንጀል ቅጣት አልኮሆል መጠጦችን አካለ መጠን ላልደረሰ ወጣት በመስጠት ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ከልክ አሳልፎ የጠጣ መሆኑ በግልጽ ለታወቀ ሰው መስጠትንም ያካትታል፣

2) ወንጀሉ ተደጋግሞ የተፈፀመ እንደሆነ የሞያ ሥራውን መከልከሉ የተጠበቀ ሆኖ፣ ከስድስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት ያስቀጣል» በሚል በአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ (2) ተደንግጓል::

ይህም ከላይ በንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱትን የወንጀል ድርጊቶች ደጋግሞ የፈፀመ ማንኛውም የአልኮሆል መጠጦች ነጋዴ የንግድ ሥራ ፈቃዱንም የሚከለክልበት ሁኔታ መኖሩን ያስገነዝበናል::

3) ወንጀሉ የተፈፀመው በቸልተኝነት እንደሆነ ከሶስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት ያስቀጣል» የሚለው የአንቀጽ 5031 (3) ድንጋጌ ሲታይም ድርጊቱ በቸልተኝነት የተፈፀመም ቢሆን የሚያስቀጣ መሆኑን እና ይህም ለጉዳዩ ምን ያህል ትኩረት የተሰጠው መሆኑን የሚያስገነዝብ ይሆናል::

ከላይ እንደተመለከተው አልኮሆልን መሸጥ ወይም መስጠት ብቻ ሳይሆን በመጠጣትም የሚፈፀም ወይም ሊፈፀም የሚችልን ወንጀል በተመለከተም በሕጋችን ተደንግጐ ይገኛል:: ይኸውም ፣ በስካር ወይም በሌላ ተመሳሳይ ሁኔታ በተፈጠረ ኢ-ኃላፊነት የሚደረጉ ወንጀሎች ከኃላፊነት የሚያድኑ አለመሆናቸውም በወንጀል ሕጉ ተመልክቷል:: ይህንንም «ማንም ሰው አንድን ወንጀል ለመፈፀም በማቀድ ወይም ሊፈፅም እንደሚችል እያወቀ በአልኮሆል መጠጥ ወይም አእምሮን በሚያደነዝዝ ነገር ወይም በሌላ ዓይነት ዘዴ አስቦ ራሱን ወደ ፍፁም ኢ-ኃላፊነት ወይም ወደ ተቀነሰ ኃላፊነት በማስገባት ወንጀሉን የፈፀመ እንደሆነ ነፃ የሚያወጡ ወይም ቅጣትን የሚቀንሱ ድንጋጌዎች አይፀኑለትም» በማለት የወንጀሉ ሕጉ አንቀጽ 50(1)

ይደነግጋል፡፡ ይህም በእንደዚህ ዓይነቱ ጉዳይ ላይ ጠቅላላዎቹ የወንጀል ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል ማለት ነው፡፡

የአልኮሆል መጠጦችን ያለአግባብ መሸጥ፣ መስጠት ወይም መጠቀም በሕዝብ ሰላም፣ ፀጥታና ሥርዓት ላይ የደንብ ተላላፊነት ጥፋቶችን ሊያስከትሉ የሚችሉ ድርጊቶች ስለመሆናቸውም በወንጀል ሕጋችን ተደንግጓዋል፡፡

የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 818 እንደሚከተለው ይነበባል፣ ማንም ሰው በወንጀል ሕግ ከተመለከተው ውጭ፣

ሀ) አልኮሆልና እስፒርቶ ያለባቸውን መጠጦች በፋብሪካ ስለመሥራትና በነ ዚሁ ስለመነገድ የወጣውን የመቆጣጠር ሕግና ትዕዛዝ የተላለፈ እንደሆነ ፣

ለ) በሕግ ከተፈቀደው ጊዜ ወጭ በሆነ ሰዓት ለሕዝብ ከተከፈቱት የንግድ ቤቶች ውስጥ የአልኮሆል መጠጦችን የሸጠ ፣ የገዛ፣ የጠጣ እንደሆነ፣

ሐ) እነዚህኑ አልኮሆል ያለባቸውን መጠጦች አካለ መጠን ላልደረሱ አእምሮአ ቸው ትክክለኛ ባለመሆኑ በሙሉ ኃላፊነት ለማይጠየቁ ወይም በጣም መስከራቸውና አደገኛ መሆናቸው በግልጽ ለሚታዩ ሰዎች ከመጠን ባለፈ ብዛት ለሕዝብ ክፍት በሆኑ ቦታዎች የሸጠ፣ የሰጠ፣ ወይም ያቀረበ እንዲሰጣቸው ወይም እንዲሸጥላቸው ያደረገ እንደሆነ፣

መ) በሕዝብ መሰብሰቢያ አደባባይ ወይም ለሕዝብ በተከፈተና ሕዝብ በሚያየው ሥፍራ አስቦ ሌላው ሰው እንዲሰክር ያግባባ ፣ ሌላውን ሰው ያሰከረ ወይም ራሱ የሰከረ እንደሆነ፣በመቀጮ ወይም ከአንድ ወር በማይበልጥ የማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል» ይላል፡፡

አልኮሆል መጠጣት ሊያስከትለው የሚችለው የሥነ ምግባር ብልሹነትም በወንጀል ሕጋችን የተወገዘ ስለመሆኑ አንቀጽ 819 ተደንግጓል፡፡

«አንቀጽ 819 ሰክሮ ወይም አእምሮ የሚያናውፅ ነገር ቀምሶ ሕዝቡን ማወክ፣

ማንም ሰው በሕዝብ አደባባይ የሚያስነቅፍና የሚያስነውር ሥራ የፈፀመ ፣ የማስፈራራት ንግግር የተናገረ እንደሆነ ፣ በአስተዳደር ክፍል በኩል ሊፈፁሙበት የሚገባቸው የፀጥታ አጠባበቅ የጥንቃቄ ቅጣቶች የሚፈፁሙበት መሆናቸው ሳይቀር እስከ አንድ መቶ ብር

ለመድረስ በሚችል መቀጮ ወይም እስከ ስምንት ቀን ለመድረስ በሚችል በማረፊያ ቤት እሥራት ይቀጣል» ይላል።

በዚህ አንቀጽ የሚያስነቅፍና የሚያስነወር ሥራ በሚል የተገለፀው ለምሳሌ ፣ በሕዝብ ፊት ወይም ሕዝብ በሚያዘወትርበት ቦታ የግብረ ሥጋ ድርጊትን ወይም ለመልካም ጠባይ ወይም ሥነ ምግባር ተቃራኒ የሆነ ፀያፍ ድርጊት ወይም ግለሰቡ ባይሰክር ኖሮ ሊፈፅማቸው የማይቻለው ማናቸውም የሥነ ምግባር ብልሹነትን የሚያንፀባርቁ ድርጊቶችን ለማመልከት ነው።

# 3. ከአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ህገወጥ አጠቃቀምና ንግድ ጋር በተያያዘ ስለሚፈፀሙ ተጓዳኝ ወንጀሎች

## 3.1 አደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆችን ያለአግባብ በመጠቀም ስለሚፈፀሙ ተጓዳኝ ወንጀሎች

ማንም ሰው ሕጋዊ ልዩ ፈቃድ ሳይኖረው መርዛማ ነገሮችን ወይም የናርኮቲክ ወይም ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶችን ወይም ዕፆችን ያመረተ፣ የሠራ ፣እንዲዘዋወሩ ያደረገ እንዲሁም ያለአግባብ የተጠቀመም ሆነ ሌሎች እንዲጠቀሙ ያደረገ እንደሆነ በእነዚሁ ድርጊቶች በወንጀለኝነት እንደሚቀጣ ከላይ ለማየት ሞክረናል።

ይህ እንዳለ ሆኖ ፣ አደገኛ መድኃኒቶችን ወይም ዕፆችን ፣ ማህበራዊ አደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ፣ (social drugs) በሚል የተገለፁትን አልኮሆል ፣ ጫት፣ ትምባሆና የትምባሆ ወጤቶች ወዘተ ጭምር ፣ ያለአግባብ የሚጠቀም ሰው ከዋናው ወንጀል በተጨማሪ የሚፈጽማቸው ሌሎች በርካታ ተጓዳኝ ወንጀሎች እንዳሉ ጥናታዊ መረጃዎች ይጠቀማሉ።

አደገኛ መድኃኒቶች ወይም ዕፆችን ያለአግባብ መጠቀም ለበርካታ ተጓዳኝ የወንጀል ድርጊቶች መፈፀም ምክንያት የሚሆን ቢሆንም በዚህ ርዕስ ሥር የምናየው ግን ስለስርቆትና ዘረፋ በሴቶች በተለይም አካለ መጠን ባልደረሱ ወጣቶች ላይ የሚፈፀሙ የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል ወይም የግብረ ሥጋ ጥቃት (ሴሰኝነት) ፣ የዝሙት ተግባራት ወዘተ ... ይሆናል።

## ሀ) ሥርቆትና ዘረፋ

አደገኛ መድኃኒቶች ወይም ዕፆች ያለአግባብ የሚጠቀሙ ግለሰቦች የተለያዩ ወንጀሎችን በተለይም ገንዘብ ሊያስገኙላቸው የሚችሉ (money making crimes ) ፣ የስርቆት፣ ዘረፋ ፣ እና ሌሎችንም የማጭበርበርና የኃይል ተግባራት ይፈጽማሉ:: በአንድ ወቅት ከበለፀጉት አገሮች ጉዳናዎች ተይዘው የነበሩት በርካታ ወንጀለኞች መካከል 50% ያህሉ የአንድና ከአንድ በላይ አደገኛ መድኃኒቶች ወይም ዕፆች ተጠቃሚዎች መሆናቸው የተረጋገጠ መሆኑን አንድ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጥናታዊ መረጃ ይጠቁማል::

በእንደዚህ ዓይነት የወንጀል ድርጊቶች ምክንያትም ምን ያህል ንፁሃን ሰዎች ሰለባ እንዲሆኑ መገመት ይቻላል:: በስርቆትና ዘረፋ ንብረታቸውን ያጣሉ ፣ በሚፈፀሙባቸው የኃይል ተግባራት አካለ ጉደሎ ሊሆኑ ወይም ሕይወታቸው ሊያልፍ ይችላል:: ከላይ የተገለፁት የወንጀል ተግባራት ሙሉ በሙሉ በአደገኛ መድኃኒቶች ወይም ዕፆች ተጠቃሚዎች የሚፈፀሙ ናቸው ብሎ መደምደም ባይቻልም በርካታ ወንጀሎች በእነዚሁ አደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ተጠቃሚነት ምክንያት የሚፈፀሙ እንደሆኑ አግባብነት ያላቸው አካላት መረጃዎች ይጠቁማሉ::

## ለ) የግብረ ስጋ ድፍረት በደል

ዕድሜያቸው አሥራ ሶስት ዓመት በሆነና አሥራ ስምንት ዓመት ባልሞላቸው ልጆች ላይ የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል መፈፀም በሕጋችን የተከለከሉና በወንጀል የሚያስቀጣ ድርጊት ነው::

የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 626 (1) የሚከተለውን ይደነግጋል፣

« ማንም ሰው ተቃራኒ ፆታ ካላት ዕድሜዋ ከዘጠኝ ዓመት በላይ ሆኖ አሥራ ስምንት ዓመት ካልሞላት ልጅ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙት የፈፀመ ወይም ይህችው ልጅ እንዲህ ዓይነቱን ድርጊት ከእርሱ ጋር እንድትፈጽም ያደረገ እንደሆነ ከሦስት ዓመት እስከ አሥራ አምስት ለመድረስ በሚችል ፅኑ እስራት ይቀጣል» ይላል::

ይህ አንቀጽ የሚደነግገው አገሪቱ በፈረመችው የህጻናት መብቶች ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና በሕገመንግስቱ መሠረት ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች ሊፈፀምባቸው ከሚችሉ የግብረስጋ ጥቃት ወይም መሰል ወንጀሎች አንጻር ተገቢውን ጥበቃ እንዲያገኙ ማድረጉን አስፈላጊነት

የሚመለከት ሲሆን እንደዚህ ዓይነት ወንጀሎችን በአመዛኙ የሚፈፀሙት የአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ተጠቃሚዎች በሆኑ ግለሰቦች ስለመሆኑ በተለያዩ ጊዜያት በመገናኛ ብዙሃን ከሚደመጡት የፖሊስ እና ሌሎችም አግባብነት ያላቸው አካላት ዘገባዎች ልናገናዝበው የምንችለው ጉዳይ ነው::

እንዲሁም በሴት ሕፃናት ላይ የሚፈፀም የግብረ ሥጋ ጥቃቶችን አስመልክቶ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 627 የሚከተሉትን የሚደነግግ  ሆኖ እናገኘዋለን፣

1) ማንም ሰው ከእርሱ ጋር ተቃራኒ ፆታ ካላት፣ ዕድሜዋ አሥራ ሶስት ዓመት ካልሞላት ልጅ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈፀመ እንደሆነ፣ ከአሥራ አምስት ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል::

2) የግብረ ሥጋ ጥቃት በተጐጂዋ ላይ ከባድ የአካል ጉዳትን ወይም ሞትን ያስከተለ እንደሆነ፣ ቅጣቱ የዕድሜ ልክ ፅኑ እሥራት ይሆናል» (627(5))

በዚህ አንቀጽ የተመለከቱት ድርጊቶች የወንጀል ማክበጃ  ሌሎች ምክንያቶች ደግሞ በአንቀጽ 628 ተመልክተዋል::

## ሐ) አስገድዶ መድፈር

በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 620 (1) እና (2) (ሀ) ስለ አስገድዶ መድፈር የሚከተለው ተደንግጓል::

1) ማንም ሰው የኃይል ድርጊት በመጠቀም ወይም በብርቱ ዛቻ ወይም ሕሊናዋን እንድትስት ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ መከላከል እንዳትችል በማድረግ ከጋብቻ ውጭ አስገድዶ ከአንዲት ሴት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈፀመ እንደሆነ፣ ከአምስት እስከ አሥራ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ፅኑ እሥራት ይቀጣል፣

2) ወንጀሉ የተፈፀመው ዕድሜዋ ከአሥራ ሶስት ዓመት በላይ ሆኖ አሥራ ስምንት ዓመት ባልሞላት ልጅ ላይ ሲሆን ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ ዓመት ለመድረስ የሚችል ፅኑ እሥራት ይሆናል::

## መ) ዝሙት

የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 635- ሴቶችንና አካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን ለዝሙት አዳሪነት በማቃጠር መነገድን በሚመለከት እንደሚከተለው ይደነግጋል፣ ማንም ሰው ለጥቅም ሲል ወይም የሌላውን ሰው ፍትወተ ሥጋ ለማርካት፣

ሀ) በፈቃዳቸውም ቢሆን በዝሙት አዳሪነት እንዲሰማሩ በማሳት፣ በማባበል ፣ በማቅረብ ወይም በማናቸውም ዘዴ በመገፋፋት ሴቶችን ወይም አካለ መጠን ያላደረሱ ልጆችን በማቃጠር የነገደ ወይም ከቦታ ቦታ ያዟዟረ ወይም፣

ለ) የተባለውን ሰው ለዝሙት ለማቅረብ በዝሙት አዳሪ ቤት ያስቀመጠ እንደሆነ፣

በተለይ ከሕግ ውጭ በግድ ይዞ የማስቀመጥ ድርጊት በተፈፀመ ጊዜ ያሉ ከበድ ያሉ ቅጣቶች ተፈጻሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ እስከ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ፅኑ እሥራትና እስከ አሥር ሺህ ብር ለመድረስ በሚችል መቀጮ ይቀጣል::

ይህ ወንጀል የተፈፀመው ሞያ ተብሎ በተያዘ፣ ሰዎችን ለዝሙት የማቅረብ ወይም ከቦታ ቦታ የማዟዟር ሥራ በተሰማራ ሰው ሆኖ በደሉም የተፈፀመበት አካለ መጠን ያልደረሰ እንደሆነ ቅጣቱ ከሶስት እስከ አሥር ዓመት ለመድረስ በሚችል ፅኑ እሥራት እና እስከ ሃያ ሺህ ብር ለመድረስ በሚችል መቀጮ ይሆናል:: (አንቀጽ 636)

## ሠ) በሽታዎችን ስለማስተላለፍ

ከዚህ በላይ ከተመለከቱት የግብረ ሥጋ በደል፣ ጥቃት ወይም አስገድዶ መድፈር የወንጀል ድርጊቶች ጋር ተያያዥነት ያለውና በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ ጉዳት እያስከተለ ላለው የኤች.አይ ቪ/ ኤድስ ወረርሽኝ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው ጉዳይንም በተመለከተ በወንጀል ሕጉ ተደንግጓል::

«የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 514 (2) (ሀ) እንደሚከተለው የሚነበብ ሆኖ እናገኘዋለን፣

«ጥፋተኛው ፣ በጥላቻ ፣ በቂመኝነት ፣ በክፋት ወይም በወራዳነት መንፈስ በሌላ ሰው ላይ ከባድ ጉዳትን ወይም ሞትን የሚያስከትል በሽታ ያሰራጨ ወይም ያስተላለፈ እንደሆነ እስከ ሃያ

ዓመት ሊደርስ በሚችል ፅኑ እሥራት ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ በዕድሜ ልክ ፅኑ እሥራት ወይም በሞት ይቀጣል፡፡»

በአጠቃላይም ማንም ሰው በማናቸወም ምክንያት የትኛውንም ዓይነት አደገኛ መድኃኒት ወይም ዕፅ የሚጠቀም ከሆነ፣ ከዋና የወንጀል ድርጊቱ በተጨማሪ በርካታ ተጓዳኝ የሆኑ ወንጀሎችን መፈፀሙ የማይቀር ስለመሆኑ በዚህ ዙሪያ የተደረጉ ጥናታዊ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ እነዚህ የወንጀል ተግባራትም በአንድ በኩል አደገኛ መድኃኒቶቹን እና ዕፆቹን ከተጠቀሙ በኋላ የሚፈጽሟቸው እና ወይም በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህኑ መድኃኒቶች እና ዕፆች ለመግዛት የሚያስፈልግ ገንዘብ ለማግኘት መድኃኒቶቹን/ዕፆችን ያለአግባብ በሚጠቀሙ ሰዎች የሚፈፀሙ ወንጀሎች በሚል ሊፈረጁ የሚችሉ ናቸው፡፡

## 3.2 በአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ህገወጥ አዘዋዋሪዎች/ሽያጮች የሚፈፀሙ ተጓዳኝ ወንጀሎች

የአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ሕገወጥ አዘዋዋሪዎች ወይም ሻጮችም ከዋና የወንጀል ድርጊቶቻቸው ጋር በተያያዘ የሚፈጽሟቸው በርካታ ተጓዳኝ ወንጀሎች ስለመኖራቸው ጥናታዊ መረጃዎች ያስገነዝባሉ፡፡ የአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ሕገወጥ አዘዋዋሪዎች/ሻጮች በአብዛኛው በቡድን በመደራጀት በተጓዳኝ ከሚፈጽሟቸው የወንጀል ድርጊቶች መካከልም ፣

- በአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ሕገወጥ ዝውውር፣ ከሚያገኙት በርካታ ሚሊዮን ዶላር ትርፍ በየአገሩ፣ ለመንግስት አካላት ማለትም ለፖሊስ፣ ጉምሩክ፣ አቃቤ ሕግ፣ ፍርድቤቶችና ሌሎችም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛው ደረጃ ያሉ የቁጥጥር አካላት/ ባለሥልጣናት እንዲሁም ለሕግ አውጪ አካላት በመስጠትና ለዓላማቸው ተገዢ እንዲሆኑ ማድረግ እና፣
- በሚሰጡት ገንዘብ አልገዛ ያላቸውን የትኛውም የመንግስት አካል/ባልደረባ ላይ ዛቻ ፣ ማስፈራራት ወይም የግድያ እርምጃ መወሰድ፣ የሚሉት በዋነኛነት የሚጠቀሱ ይሆናሉ፡፡

እነዚህ ቡድኖች በየአገሩ የመንግስት አካላትን/ባለሥልጣናቱን በገንዘባቸው በመግዛት የሚፈጽሙት የመድኃኒት ሕገወጥ ዝውውር/ሽያጭ ወንጀል ሕዝቡ በሕግ የበላይነት ላይ እምነት እንዳይኖረው በማድረግ ረገድ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ ቀላል ግምት የሚሰጠው

አይሆንም:: ይህም «የመልካም አስተዳደር ሥርዓት» ለማስፈን በተለይም በታዳጊ አገሮች በሚደረጉ ጥረቶች ሁሉ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ከፍተኛ መሆኑ ሊገናዘብና ልዩ ትኩረትም ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ይሆናል:: የመንግስት አካላትም ምን ያህል የሞራል ጥንካሬ ሊኖራቸው እንደሚገባና ይህ ካልሆነ ግን በተሰየሙበት የሥራ ድርሻቸው መንግስትን በማገልገል ፈንታ የወንጀለኛ ቡድኖቹ ሕገወጥ ድርጊቶች አፈጻጸም መጠቀሚያ መሣሪያዎች እንደሚሆኑ ይገመታል::

## 4. የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 661/2002

የአደገኛ መድኃኒቶች እና ዕፆች ሕገወጥ ዝውውርና አጠቃቀምን ለመግታት አገራችን ካሏት ሕጎች መካከል አንዱ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ 661/2002 መሆኑ ከላይ ተገልጿል::

በዚህ ዘርፍ ለሚደረጉት የቁጥጥር ሥራዎች አግባብነት ካላቸው የአዋጁ ድንጋጌዎች ዋና ዋናዎቹም እንደሚከተለው የሚነበቡ ሆነው እናገኛቸዋለን::

- አንቀጽ 4(12) የናርኮቲክና ሣይኮትሮፒክ መድኃኒቶችን እንዲሁም ፕሪከርሰር ኬሚካሎችን አመራረት ፣ ማስመጣት፣ መላክ፣ ሥርጭትና አጠቃቀምን በተመለከተ፣ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን የመከታተልና የመቆጣጠር ኃላፊነት ተሰጥቶታል፣
- ልዩ ፈቃድ ስለማስፈለጉ በሚለው የአዋጅ አንቀጽ 18 ሥር፣

1) የናርኮቲክ መድኃኒቶች፣ሳይኮትሮፒክ ንጥረ ነገሮች ወይም ፕሪከርሰር ኬሚካሎችን ለማስመጣት፣ ለመላክ፣ለማምረት፣ ለማከፋፈል፣ ለማከማቸት ወይም ለመያዝ ከአስፈጻሚ አካሉ ልዩ ፈቃድ ማውጣት አለበት፡፡

2) አስፈጻሚ አካሉ ልዩ ፈቃድ የሚሰጠው መድኃኒት ማስመጣትን፣ መላክን፣ ማምረትን፣ ማከፋፈልን ወይም ማከማቸትን ወይም የጤና አገልግሎት መስጠትን በሚመለከት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ላለው ሰው ብቻ ይሆናል፡፡

- በሕገወጥነት የተያዙ ናርኮቲክ መድኃኒቶች፣ ሳይኮትሮፒክ ንጥረ ነገሮች ወይም ፕሪከርሰር ኬሚካሎች ስለሚወገዱበት ሁኔታ ባለሥልጣኑ መመሪያ የሚያወጣ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 21 ተደንግጓል፡፡

በሌላም በኩል የምግብ፣¾መድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 661/2002 አንቀጽ 53፣ የናርኮቲክ መድኃኒቶች፣ የሳይኮትሮፒክ ንጥረ ነገሮች ወይም የፕሪከርሰር ኬሚካሎችን ሕገወጥ አጠቃቀም የሚገፋፉ ድርጊቶችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች አሉት፡፡

እነዚህ የወንጀል ድንጋጌዎችም ማንኛውም ሰው የናርኮቲክ መድኃኒቶች ወይም ሳይኮትሮፒክ ንጥረ ነገሮች ሕገ-ወጥ አጠቃቀም ለመገፋፋት በማናቸውም መንገድ ካስተዋወቀ ወይም ሌሎች እንዲያስተዋውቁ ካደረገ ወይም ከፈቀደ ወይም ፕሪከርሰር ኬሚካሎች ከሚኖራቸው አግባብነት ያለው ጠቀሜታ ውጭ በሆነ ሁኔታና ለሕገ-ወጥ የናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ማምረት ተግባር ያዋለ እንደሆነ ከሰባት ዓመት በማያንስና ከአስራ አምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት እና ከብር 30,000 በማያንስና ከብር 50,000 በማይበልጥ መቀጮ እንደሚቀጣ ይደነግጋል፡፡

በአዋጁ ውስጥ የትምባሆ ዝግጅቶችን የመቆጣጠር ኃላፊነት የተሰጠው ባለስልጣኑ ሲሆን ማንኛውም ሰው ትምባሆ ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት ወይም ለማከፋፈል ከባለስልጣኑ ልዩ ፈቃድ ማግኘት እንዳለበት በአንቀፅ 22 (1) ላይ ተደንግጓል፡፡

የትምባሆ ማስመጣት፣ ማከፋፈል፣ ሽያጭ፣ አጠቃቀም፣ አስተሻሸግና ገላጭ ጽሁፍ፣ የማስተዋወቅና የአወጋገድ ተግባራት በተመለከተ አዋጁን ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ መሰረት እንደሚሆን በዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 ላይ ተገልጿል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# የአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ቁጥጥር ተግባር፣

የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች እንቅስቃሴ ቁጥጥር ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ አብይ ጉዳይ ነው፡፡ የቁጥጥሩ ተግባር በተለያዩ መስኮች ሊከናወን ቢችልም የሚከተሉት ተግባራት ቅድሚያ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

- በዓለም አቀፍና አገር አቀፍ ደረጃ የቁጥጥሩ ተግባር በተጠናከረ መልክ ማከናወን፣ ለዚህም የሚረዱ የዓለም አቀፍ ስምምነቶችን መቀበልና የአገርን ሕግና ደንብ በማውጣት ተግባራዊ ማድረግ፣
- የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች አቅርቦት ከፍላጎት ቅነሳ ጋር በተጣጣመ መልኩ እንዲካሄድ ማድረግ፣
- በሕገወጥ መንገድ የሚቀርቡ አደገኛ መድኃኒቶችና እጾች በተቻለ አቅም ማስወገድ፣ እንዲሁም ሕገወጥ ዝውውር እንዲቀንስ ማድረግና የመሳሰሉት ተግባራት ከተከናወኑ አሁን የሚታዩት የመድኃኒቶቹና የእጾቹ ሕገወጥ ዝውውርና አጠቃቀም ሊቀንስ ይችላል፡፡

በዚህ ጽሁፍ የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ሕገወጥ ዝውውርና አጠቃቀምን ለመቀነስ የቁጥጥር ተግባር የሚጫወተውን ጉልህ ሚና ለማሳየትና በቁጥጥር ተግባር ውስጥ የግለሰብ፣ የቤተሰብና የሕብረተሰብ ተሳትፎ ይጠቀሳል፡፡ ሌላው የቁጥጥር ተግባር የአንድ አካል ሥራ ድርሻ ብቻ ሳይሆን የተለያዩ መሥሪያ ቤቶችን የሚያሳትፍ ነው፡፡

## ሀ. ቅንጅታዊ አሠራርን ማዳበር፣

የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ሕገወጥ ዝውውርና አጠቃቀም የመከላከል ሥራ በአንድ መሥሪያ ቤት የሚከናወን አይደለም፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃም የሁሉም አገሮች ትብብር ያስፈልገዋል፡፡

በቁጥጥሩ ተግባር ከሚሳተፉት መሥሪያ ቤቶች አንዱ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ነው፡፡ ባለሥልጣኑ በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት አገራችን የተቀበለቻቸውን የቁጥጥር ስምምነቶች ተግባራዊነት ከመከታተሉ ባሻገር ለሕክምናና ለሣይንሳዊ ምርምር ከውጭ የምናስመጣቸው ናርኮቲክና ሣይኮትሮፒክ መድኃኒቶች እስከ ተጠቃሚው ድረስ ያለውን የሥርጭት ሂደት የሚቆጣጠር አካል ነው፡፡

ሌላው ጉዳዩ የሚመለከተው መ/ቤት የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ነው፡፡ በኮሚሽኑ ሥር የተዋቀረው የአደገኛ እጽዋት መቆጣጠሪያ ዋና ክፍል የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ሕገወጥ ምርትና ዝውውርን ለመግታት የበኩሉን አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ዋና ክፍል በመግቢያ ኬላዎች በኩል ከውጪ አገር የሚገቡትን፣ በአገር ውስጥ የሚበቅሉትንና የሚዘዋወሩትን አደገኛ መድኃኒቶችና እጾች እንዲሁም በወንጀሉ ተግባር ተሣትፎ ያላቸውን ተከታትሎ በመያዝ ወደ ሕግ ያቀርባል፡፡

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣንም በዚህ መስክ ከሚሠሩት መ/ቤቶች መካከል አንዱ ነው፡፡ የጉምሩክ ባለሥልጣን ገቢና ወጪ ዕቃዎችን የመፈተሽ ሥልጣን በሕግ ተሰጥቶታል፡፡ መ/ቤቱ በተለያዩ የመግቢያ ኬላዎች የሚገቡ ዕቃዎችን በመፈተሽ አደገኛ መድኃኒቶችና እጾች በሕገወጥ ዝውውር ላይ እንዳሉ የሚይዝ አካል ነው፡፡ ይህን ተግባር ከፖሊስ ጋር በመተባበር ይሰራል፡፡

የፍትሕ አካላት ሕግን በማስከበር በኩል ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ ሲሆን ፖሊስና የገቢዎችና ጉምሩክ ባልደረቦች ወንጀለኞችን ለፍርድ ሲያቀርቡ ተገቢውን ቅጣት በመስጠት ሕግ እንዲከበር ያደርጋል፡፡

ለክልሎች በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የክልል አካላት በየክልላቸው የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ሕገወጥ ዝውውርና አጠቃቀምን ለመግታት አስፈላጊውን የመቆጣጠር ተግባር ያካሂዳሉ፡፡ በክልሎች የሚገኙ የጤና ቢሮዎች፣ የፖሊስ ኮሚሽኖች፣ ገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶችና የሕግና ፍትሕ ጉዳይ ቢሮዎች በቁጥጥር ተግባር የሚሳተፉ መ/ቤቶች ናቸው፡፡ እነዚህ መ/ቤቶች ከማዕከላዊ መ/ቤቶች ግንኙነት በመፍጠር ይሰራሉ፡፡

የናርኮቲክና ሣይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ሕገወጥ ዝውውርና አጠቃቀምን ለመግታት ጉዳዩ በሚመለከታቸው መ/ቤቶች መካከል ቅንጅታዊ አሠራር ሊኖር ይገባል። በዚሁ መሠረት የቁጥጥሩ ተግባር በተጠናከረ መልኩ እንዲካሄድ ካስፈለገ በተቆጣጣሪ አካላት መካከል የመረጃ ልውውጥና ቅንጅታዊ አሠራር መስፈን ይኖርበታል።

በሌላ በኩል በአገሮች መካከል የመረጃ ልውውጥ ከሰፈነ የቁጥጥር ተግባሩ አመርቂ ውጤት ሊያስመዘግብ ይችላል። አንድ ወንጀለኛ ከአገር ወደ አገር በሚዘዋወርበት ወቅት ፖሊስ በኢንተርፖል በኩል ገቢዎችና ጉምሩክ ደግሞ በዓለም አቀፍ የጉምሩክ ሕብረት በኩል መረጃ ከተለዋወጡ ወንጀለኛው ጥፋት ከማድረሱ በፊት በቀላሉ ሊያዝ ይችላል። እንዲሁም በየአካባቢው የመረጃ መረብ ከተቋቋመ የወንጀለኞችን እንቅስቃሴ በቀላሉ ለመከታተል ያስችላል። በእነዚህና በሌሎች መሰል ተግባሮች በአገር አቀፍና አለም አቀፍ ደረጃ የትብብርና የቅንጅት ሥራ ሊዳብር ከቻለ የሚካሄደው የቁጥጥር ተግባር ፍሬያማ ውጤት ሊያበረክት ይችላል። ሌላው ጉዳዩ የሚመለከታቸው መ/ቤቶች የሚሳተፉበት ብሔራዊ ኮሚቴ ወይም ኮሚሽን ቢቋቋም የቅንጅት ሥራው ይበልጥ ይዳብራል። በዚህ ረገድ ከተለያዩ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች የተውጣጣ ብሄራዊ ኮሚቴ ተቋቁሞ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ የኮሚቴው ሊቀመንበር የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚ/ር ሲሆን የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ ቁጥጥርና አስተዳደር ባስልጣን በፀኃፊነት ያገለግላል፡፡ የጋራ ኮሚቴው ዋና ዓላማ የቁጥጥሩና የማስተማሩ ስራ ለ አንድ መ/ቤት የሚተው ሳይሆን ሁሉም የሚመለከተው አካል የራሱን ድርሻ በመውሰድ አስተዋፅኦ እንዲያበረክት ለማስቻል ነው፡፡

## ለ. የፍተሻ ተግባር ማጠናከር፣

የአንድ አገር ሕግና ደንብ ጠንካራ ካልሆነ የሚካሄደው የቁጥጥር ተግባር ፍሬያማ ሊሆን አይችልም። ተቆጣጣሪውን አካል የሚደግፍ ጠንካራ ሕግና ደንብ ሊኖር ይገባል። ባለው ሕግና ደንብ ተጠቅሞ የቁጥጥሩ አካል የሆነው የፍተሻ ተግባር ማካሄድ ያስፈልጋል።

በመግቢያ ኬላዎች የሚደረገው ቁጥጥር በሰለጠነ የሰው ኃይልና በዘመናዊ መሣሪያዎች የተደራጀ ካልሆነ ሕገወጥ አዘዋዋሪ ግለሰቦች የቁጥጥሩን መረብ በቀላሉ ያልፉታል።

በዚህ ረገድ፡-

- የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ሕገወጥ ዝውውር እንዴት መቆጣጠርናመከላከል እንደሚቻልና ዓይነታቸውን እንዴት መለየት እንደሚገባ በአሁኑጊዜ በዓለም ላይ ወንጀለኞች የሚጠቀሙበትን የተለያዩ ዘዴዎች በተመለከተበቁጥጥር ተግባር ለተሰማሩ ባለሙያዎች በየጊዜው ትምህርት መስጠት፣

- የመቆጣጠርና የመከላከሉን ብቃት ለማሳደግ በቀጥታ በፍተሻ ሥራው ላይለተሰማሩ ባለሙያዎች አደገኛ መድኃኒቶችና እጾች የሚጓጓዙበትን ዘዴ፣የአደባበቅ ስልት፣ የአጠቃቀም፣ የመረጃ አሰባሰብና አያያዝ ዘዴ ከተያዙበኋላ ያለውን ጥንቃቄና ምርመራ አስመልክቶ ስልጠና መስጠት ያስፈልጋል፡፡

- የፍተሻ ተግባር በተጠናከረ መልኩ በማካሄድ በአገራችን በኩል ወደ ሌሎችአገሮች በሕገወጥ መንገድ የሚዘዋወሩትን አደገኛ መድኃኒቶችና እጾችመግታት ይቻላል፡፡ ይህ ተግባር በሰፊው ካልተከናወነ ችግሩ አገራችን ውስጥተንሰራፍቶ ለሌሎች አገሮች ችግር ልንተርፍ እንችላለን፡፡ ስለሆነም ፍተሻውን በማጠናከር አገራችንና ሌሎች አገሮችን መከላከል ይጠበቅብናል፡፡

## ሐ. ምንጩን ማድረቅ፣

የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾችን ሕገወጥ ዝውውር ለመከላከል መጀመሪያ ምንጩን ማድረቅ ያስፈልጋል፡፡ ምንጩ ላይ እርምጃ ሳይወሰድ መድረሻ ላይ ለመከላከል መሞከር ፋይዳ አይኖረውም፡፡ ስለሆነም እነዚህ እጾች የሚበቅሉባቸው አካባቢዎች እየተለዩ እጾችን ማስወገድ መቻል አለበት፡፡ ይህ ዓይነት እርምጃ የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ሕገወጥ አቅርቦትን ለመቀነስ ዓይነተኛ መሣሪያ ነው፡፡ እጾቹን ማስወገድ ብቻ ሣይሆን ሌሎች ሰብሎች በምትካቸው ገበሬው ማብቀል እንዲችል አማራጭ መቅረብ ይኖርበታል፡፡
አደገኛ መድኃኒቶች በሕገወጥ መንገድ የሚፈበረኩ ሕገወጥ ላቦራቶሪዎች ያሉበት አካባቢ እየተለየ የሚወገዱበት ስልት መፍጠር ይኖርበታል፡፡ እነዚህ ሕገወጥ ላቦራቶሪዎች ካልተወገዱ የአደገኛ መድኃኒቶች አቅርቦትን ለመቀነስ በጣም ሊያስቸግር ይችላል፡፡ ስለሆነም ከምንጩ እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል፡፡
ሌላው ለሕክምና ተግባር የሚውሉት ናርኮቲክና ሣይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ከታለመላቸው ወደ አልተፈለገው ዓላማ እንዳይውሉ አስፈላጊውን ቁጥጥር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህም ወደሚፈለጉበት አካባቢ ሲጓጓዙ ወደ ሕገወጥ መንገድ እንዳይገቡና በጤና ድርጅቶችም በስርቆትና በማታለል ሕገወጥ ተጠቃሚዎች እጅ እንዳይገቡ አስፈላጊውን የስርጭት ሂደት መዘርጋትና ትክክለኛ አጠቃቀምን ማስፈን ይጠይቃል

# ምዕራፍ አራት

# ስለአደገኛ መድኃኒቶችና ዕፆች ህገወጥ ዝውውርና አጠቃቀም ማስተማር

የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ሕገወጥ አጠቃቀምን ለመከላከል በሚደረገው ጥረት ትምህርት በተጓዳኝ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ በጣም ከፍተኛ ነው። ትምህርት በመደበኛ ስርዓተ ትምህርት ለሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል ይተላለፋል። በዚህ ረገድ የሚተላለፈው የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ሕገወጥ ዝውውርና አጠቃቀም አስከፊ ገጽታን የሚያስተጋቡ የትምህርት ኘሮግራሞች ግለሰቦች ወደዚህ አዘቅት እንዳይገቡ ቀድሞ ለመከላከልና ሱሰኞችም ከሱሱ እንዲላቀቁ ይረዳል። በትምህርት አማካይነት ዘለቄታ ያለው የባሕርይ ለውጥ ማምጣት ይቻላል። ምን ጊዜም ሰዎች ስለአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ሊኖራቸው የሚችለው አመለካከት ላይ በቅድሚያ የሚያገኙት ዕውቀትና መረጃ ተጽዕኖ ስለሚኖረው የትምህርት ኘሮግራሙ ሂደት ወደ ኋላ ሊባል የሚችል አይደለም።

**ዓላማ፣**

## የትምህርት ኘሮግራሙ ሂደት ዋና ዋና ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው።

- የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ምንነትና አለአግባብ አጠቃቀም ስለሚያስከትለው ችግር ዕውቀት ለማዳበር፣
- የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች አለአግባብ አጠቃቀም እንዳይኖር የሰዎች ዝንባሌና ባሕሪ እንዲጎለብት ለማድረግ፣
- ሰዎች አደገኛ መድኃኒቶችና እጾች አለአግባብ እንዲጠቀሙ የሚደረገውን ግፊት ተቋቁመው አያስፈልገንም እንዲሉ ማስቻል፣
- ግለሰብ ቤተሰብና ሕብረተሰብ በሚካሄደው የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ፍላጎት ቅነሳ ላይ እንዲሳተፉ ማስቻል።

## የሚከናወኑ ተግባራት፣

የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ሕገወጥ ዝውውርና አጠቃቀም አስከፊ ገጽታን ለመከላከል ትምህርት ዓይነተኛ መሣሪያ መሆኑ ቀደም ሲል ተገልጿል:: ይህን ዓብይ ሥራ ለመተግበር የሚከተሉት ሥራዎች መከናወን ይኖርባቸዋል::

- መረጃ የማሰራጨት ሥራ፣
- በመደበኛ ስርዓተ ትምህርት የሚሰጠው ትምህርትና
- የሕብረተሰብ ተሳትፎ፣

## ሀ. መረጃ የማሰራጨት ሥራ፣

የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ሕገወጥ ዝውውርና አጠቃቀም አስከፊ ገጽታ ለተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች መረጃ ማስተላለፍ በጣም አስፈላጊና በተግባር ተፈትኖ ውጤት ያስገኘ ሥራ ነው::

## 1.0 ስልት፣

## 1.1 የሕገወጥ አጠቃቀምን ጉዳቶች በግልጽ የማስተላለፍ ስልት፣

ይህ ስልት የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ሕገወጥ ዝውውርና አጠቃቀም በጤና፣ በማኅበራዊ ኑሮ፣ በኢኮኖሚና በፖለቲካ አለመረጋጋት የሚያደርሰውን አስከፊ ገጽታ በግልጽ መረጃ ማስተላለፍ ከተቻለ ተጠቃሚ ያልሆኑ ሰዎች እንዳይጠቀሙ ለማድረግ እየተጠቀሙ ያሉ ግለሰቦች ከሆኑ ከተጠቃሚነት ሊታቀቡ ይችላሉ የሚል ነው::

## 1.2 በእውነትነት ላይ የተመረኮዙ መረጃዎችን የማስተላለፍ ስልት፣

ይህ ስልት የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ሕገወጥ ዝውውርና አጠቃቀም አስከፊ ገጽታ ትክክለኛ የሆነ እውቀት የሚያስጨብጡ መረጃዎች በማስተላለፍ ሰዎች ጭራሽ እንዳይጠቀሙ ለማድረግ ወይም በጣም አደገኛ የሆኑትን እንዳይጠቀሙ ለማድረግ ያስችላል የሚል ነው::

## 2.0 መረጃዎች ለማንና እንዴት ይሰራጫሉ?

በሁለቱ ስልቶች በመጠቀም የሚሰራጨት መረጃዎች ለሁሉም የሕብረተሰቡ ክፍሎች መድረስ ይገባቸዋል:: ለምሳሌ፣

- ተማሪዎች፣
- ወላጆች፣ አስተማሪዎች፣

- ፖሊስ፣ ማኅበራዊ ሠራተኛ፣ ገቢዎችና ጉምሩክ ፣ ሌሎች በዚህ መስክ የተሰማሩ አካላት፣
- ፖሊሲ፣ህግ አውጪ አካላት፣ ...ወዘተ

## 2.1 ተግባራት፣

መረጃዎችን ለማስራጨት የሚከተሉትን መንገዶች መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

- በቡድን ተደራጅቶ መወያየት፣ በቡድኑ ውስጥ የሚሳተፉት ተጠቃሚዎች፣ የአካባቢ ነዋሪዎች፣ የሕብረተሰብ መሪዎች፣ ተማሪዎች፣ የሃይማኖት መሪዎች ...ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ፣
- በበራሪ ጽሑፎችና በፖስተሮች ለተለያዩ የሕብረተሰቡ ክፍሎች በተገኙ መንገዶች ማሰራጨት፣
- በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን፣ በጋዜጣና መጽሔቶች አማካኝነት ማሰራጨት፣
- በድራማ፣ ስነጽሑፍና፣ ፊልም አስፈላጊውን መረጃ ማሰራጨት፣
- ኣብያተክርስቲያናት፣ መስጊዶች፣ ዕድሮችና በመሳሰሉት በመገኘት መረጃ በቃል ማስተላለፍ፣ ጽሑፍ መበተን፣ ወ.ዘ.ተ.
- የመገናኛ ብዙሃን ጋዜጠኞችን በማስተማር ሕብረተሰቡን እንዲቀሰቅሱ ማድረግ፣
- በየትምህርት ቤቱ ፀረ አደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ክበቦች በማቋቋም ተማሪው መረጃ እንዲደርሰው ማድረግ፣

## 2.2 መረጃ በማሰራጨቱ ሂደት መወሰድ ያለባቸው ጥንቃቄዎች፣

- መረጃ ሲሰራጭ ትክክለኛነቱ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ትክክለኛ ያለሆነ መረጃ ከተሰራጨ ከዚህ በፊት የተላለፉትንና ለወደፊትም የሚተላለፉ መረጃዎች በሕዝቡ ተቀባይነት አይኖራቸውም፡፡
- መረጃ በየጊዜው በማያቋርጥ ሁኔታ መሰራጨት ይኖርበታል፣ አልፎ አልፎ የሚተላለፉት መረጃዎች የሚፈለገውን ግብ አይመቱም፡፡ በአንድ ወቅት የተላ ለፈው መረጃ ተከታታይነት ከሌለው ስለሚረሳ ነው፡፡
- አንዳንድ አደገኛ መድኃኒት ወይም እጽ የሚያስከትለው ችግር የተለያየ በሚሆ ንበት ጊዜ የያንዳንዱ ችግር በተናጠል መተላለፍ ይኖርበታል፡፡ ስለ ካናቢስ ችግር ሲተላለፍ የካናቢስ ብቻ መሆን ይኖርበታል፡፡ ይህ ካልሆነ የሚተላለፈው መረጃ በተቀባዩ ትክክለኛ ግብረምላሽ አያገኝም፡፡
- በመገናኛ ብዙሃን የሚተላለፉ መረጃዎች ለሁሉም የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚተ ላለፉ በመሆናቸው ለሁሉም በሚገባቸው ቋንቋና ቃላቶች መሆን ይኖርበታል፡፡

## ለ. በመደበኛ ስርዓተ ትምህርት የሚሰጠው ትምህርት፣

የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ሕገወጥ ዝውውርና አጠቃቀም አስከፊ ገጽታን ለመከላከል እንዲቻል ተማሪዎች በመደበኛ ስርዓተ ትምህርታቸው እንዲማሩ ያስፈልጋል፡፡ ስርዓተ ትምህርቱ በተናጠል ራሱን ችሎ ወይም ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር በማዋሃድ ሊዘጋጅ ይችላል፡፡ በዚህ ዓይነት በሚሰጠው ትምህርት ተማሪዎች ለአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ያላቸውን ወይም ሊኖራቸው የሚችለውን ዝንባሌና ባሕሪ መለወጥ ይቻላል፡፡ ወጣቱ ክፍል ከትምህርት ቤት ጀምሮ ስለአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች አስከፊ ገጽታ ማወቅ ከቻለ በቀላሉ ተታሎ በዚህ ችግር ውስጥ ሊገባ አይችልም፡፡

## 1.ኘሮግራም ተይዞ ትምህርት የመስጠት ስልት፣

ይህ ስልት ስለ አደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ኮርሶች ወይም ትምህርታዊ ስልጠና በማዘጋጀት፣ የቡድን ውይይትና የምክር አገልግሎት በመስጠትና የግል ጥናት እንዲደረግ የቤት ሥራ በመስጠት የሚከናወን ነው፡፡ እነዚህን ተግባራት ለማከናወን ኘሮግራም ተይዞ መካሄድ ይኖርበታል፡፡ የዚህ ስልት ተጠቃሚዎች የያንዳንዱ ት/ቤት ተማሪዎች ናቸው፡፡ በእኛ አገር ስልቱ በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ይመረጣል፡፡

ኮርሶች በማዘጋጀት የሚተላለፈውን ትምህርት ለመተግበር በየሳምንቱ የተወሰኑ ጊዜያት ለዚህ እንዲውሉ የትምህርት ቤቱ አመራር መወሰን ይኖርበታል፡፡ ለዚህ ተግባር ማስፈጸሚያ የሚሆኑ የማስተማሪያ ጽሑፎችና የአስተማሪዎች መመሪያ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህንን ሥራ ተግባራዊ ለማድረግ አስተማሪዎችን ማሰልጠን ያስፈልጋል፡፡

የቡድን ውይይትና የምክር አገልግሎት በአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ሕገወጥ ዝውውርና አጠቃቀም አስከፊ ገጽታ ማስተማር ላይ ከፍተኛ የሆነ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ ይህም ከልምድ በመነሣትና ከአጀንዳው ጋር በተያያዙ ቁምነገሮች ሰፊ የሆነ ውይይት በማድረግ ስለ ችግሩ በይበልጥ ለመረዳትና ወደ ሱሰኝነት እንዳይገቡ መውሰድ የሚገባቸውን እርምጃ አብረው ተወያይተው ስለሚወስኑ ፍሬያማ የሆነ ውጤት ማስመዝገብ ይቻላል፡፡ በዚህ ዓይነት አካሄድ የተማሪዎችና የአስተማሪዎችን ግንኙነት ከማሻሻሉ ባሻገር የሰዎች ለሰዎች ግንኙነትና ክህሎት ያጎለብታል፡፡ በውይይቱ ከትምህርት ቤቱ ውጭ ያሉ ወጣቶች፣ ባለሙያዎች፣ ቤተሰብና ሕብረተሰብ ቢሳተፉ ከፍተኛ ውጤት ይኖረዋል፡፡

እያንዳንዱ ተማሪ የግል ጥናት እንዲያደርግ የቤት ሥራ መስጠት በግሉ አጥንቶና በችግሩ ላይ ተመራምሮ የራሱ ውሣኔ ላይ ሊደርስ ይችላል፡፡ ተማሪው የራሱ ውሣኔ ላይ ደረሰ ማለት

ደግሞ በአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች አስከፊ ገጽታ ላይ ግንዛቤ በማዳበር ወደ ችግሩ እንዳይገባ ያደርገዋል፡፡

ይህን አመለካከት ተግባራዊ ለማድረግ በቂ የሚነበቡ ጽሑፎች ማዘጋጀትናጥያቄዎች በሚነሱበት ጊዜ ትክክለኛ መልስ የሚሰጡ አስተማሪዎች እንዲኖሩ ያስፈልጋል፡፡

## 3. ከስርዓተ ትምህርት ጋር በማቀናጀት ትምህርት የመስጠት ስልት፣

የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ሕገወጥ ዝውውርና አጠቃቀም አስከፊ ገጽታን ለመከላከል በስርዓተ ትምህርት ውስጥ በማካተት ተከታታይ የሆነ ትምህርት መስጠት ስለሚቻል አመርቂ የሆነ ውጤት ማስመዝገብ ይቻላል፡፡

### ስልቱ፣

- ከባዮሎጂ ትምህርት ጋር በማቀናጀት አደገኛ መድኃኒቶችና እጾች በሰውነታችን ፊዝዮሎጂ ላይ የሚያደርሱትን ለውጥ በማስተማር፣
- ከስቪክ ትምህርት ጋር በማቀናጀት አደገኛ መድኃኒቶችና እጾችን አስመልክቶ ስላሉ አለም አቀፍ ስምምነቶች፣ ብሔራዊ ሕጎችና ደንቦች በማስተማር፣
- ከኬሚስትሪ ትምህርት ጋር በማቀናጀት የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ኬሚካላዊ ባሕሪ በማስተማር፣
- ከማኅበራዊ ትምህርት ጋር በማቀናጀት የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ገጽታ፣ ከወንጀል፣ ከድህንነትና ከዕድገት ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት በማስተማር፣ ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል፡፡
- በሌሎች የትምህርት ዘርፎችም /ቋንቋ፣ ታሪክ፣ ሕግ፣ እርሻ ወ.ዘ.ተ./ ያላቸውን ግንኙነት በማመላከትና ምሳሌ በማጣቀስ ግንዛቤ እንዲዳብር ማድረግ ይቻላል፡፡

## 4. የጤና ትምህርት ኘሮግራሞች፣

የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ሕገወጥ ዝውውርና አጠቃቀም አስከፊ ገጽታ ትምህርት፣ ከጤና ትምህርት ኘሮግራሞች ጋር ተቀናጅቶ በሚሰጥበት ጊዜ ችግሩ ከጤና ጋር በተገናዘበ መልኩ ስለሚሰጥ የሚጠቀሱት መድኃኒቶችና እጾች በተጠቃሚው ጤንነት ላይ ከፍተኛ የሆነ ተጽዕኖ ስለሚያደርሱ ስልቱን ተመራጭ ያደርገዋል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የጤና ትምህርት እየተሰጠ በመሆኑ በዚህ ስርዓተ ትምህርት ስለአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ሕገወጥ አጠቃቀም በጤና ላይ ስለሚያደርሰው ችግር አስተማሪዎች ግንዛቤ እንዲያገኙ በማድረግ ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ ይቻላል፡፡

## ሐ. የህብረተሰብ ተሳትፎ፣

የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ሕገወጥ ዝውውርና አጠቃቀምን ለመከላከል የሁሉም ተሳትፎ ወሣኝ ነው፡፡ ጉዳዩ የሚመለከታቸው መ/ቤቶችና የተለያዩ የሕብረተሰቡ ክፍሎች በመከላከሉ ተግባር ውስጥ እንዲሳተፉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም ሕብረተሰቡን ያላሳተፈ ጥረት የተሳካ እንደማይሆን ቀደም ብለው ከነበሩት ተሞክሮዎች መገንዘብ ተችሏል፡፡

የሕብረተሰቡ ተሳትፎ ስንል ወጣቱ፣ ተማሪው፣ ሠራተኛው የሃይማኖትና የሕብረተሰብ መሪዎች...ወዘተ ማለታችን ሲሆን እነዚህ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ባሉዋቸው ማሕበራትና የመሳሰሉት ተቋማት በኩል ትምህርት በመስጠቱና መረጃ በማስተላለፉ ተግባር ላይ መሳተፍ ይኖርባቸዋል፡፡ የተለያዩ የሕብረተሰቡ ክፍሎች የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ሱሰኞች የወደፊት ዕጣ ላይ የመመካከርና የመወያየት ተግባር በማከናወን የተለያዩ አማራጮች ማፍለቅ ይቻላል፡፡ በመሆኑም የሕብረተሰቡ ተሳትፎ ወሳኝ ነው፡፡ ሕብረተሰቡ የምክር አገልግሎት ተቋሞችን በማቋቋም ችግሩ ውስጥ የገቡ ወጣቶችን ወደ ጤናማ ኑሮ መመለስ ይችላል፡፡ በሌላው በኩል ወጣቱን ወደዚህ ችግር እንዲገባ ያስገደዱት ወይም የገፋፉት ምክንያቶችን በማወቅ ከችግሩ የሚላቀቅበትን መንገድ ለመጠቆም ስለሚያስችል ተጠናክሮ መሠራት ይኖርበታል፡፡

ሕብረተሰቡ፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ወጣቱ የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ሕገወጥ ዝውውርና አጠቃቀም ተግባር ውስጥ እንዳይሰማራ የእረፍት ጊዜውን የሚያሳልፍባቸውን ማዕከሎች ማቋቋም አለባቸው፡፡ ማዕከሎቹ ከተቋቋሙ ወጣቱ መጽሐፍ ለማንበብና ለመዝናናት /ሙዚቃ፣ ኳስ፣ ከራምቦላ፣ ዳማ፣ ቼዝ ...ወዘተ ጨዋታዎች/ ስለሚረዱት በአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ሕገወጥ ዝውውርና አጠቃቀም ተግባር ከመሰማራት ይቆጠባል፡፡ ማዕከሎቹ በሕብረተሰቡ ተሳትፎ ከተቋቋሙ በሂደት ወጪያቸውን ሸፍነው ወደ ተሻለ ደረጃ ሊሸጋገሩ ይችላሉ፡፡




በፀረ-አደገኛ መድኃኒቶችና ዕጾች ዘመቻ የሕብረተሰብ ተሣትፎ

አንዳንድ ወጣቶች /ለምሳሌ ጎዳና ተዳዳሪዎች/ የሚኖሩበት ቤት፣ የሚለብሱትና የሚበሉበት ገንዘብ ስለማይኖራቸው ከችግራቸው ለመላቀቅ ሲሉ ወደ ወንጀል ተግባራትና ወደ አደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ሕገወጥ ዝውውርና አጠቃቀም ሊገቡ ይችላሉ፡፡ እንደነዚህ ዓይነት ወጣቶች አማራጭ ካልተሰጣቸው የአገር ሸክም ከመሆን አልፈው በሕገወጥ ሥራ መሳተፍ ብሎም የአገርን ሰላም ከማደፍረስ ወደኋላ አይሉም፡፡ ስለሆነም መንግስትና ሕብረተሰቡ ለነዚህ ወጣቶች አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህን ተግባር በተጠናከረ መልኩ ማካሄድ ከተቻለ የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ሕገወጥ ተጠቃሚዎች በመቀነስ አሉታዊ ተጽዕኖውን መከላከል ስለሚቻል ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

ሥራ አጥነት የአደገኛ መድኃኒቶችና እጾች ሕገወጥ ዝውውርና አጠቃቀም እንዲስፋፋ እንደ አንድ ምክንያት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ሥራ አጥ ወጣት የቤተሰቡ፣ የሕብረተሰቡና የአገሩ ሸክም ስለሚሆን ተስፋ የመቁረጥና ወደ አልተፈለገ ሥራ ለመሰማራት ይገደዳል፡፡ በመሆኑም ዘለቄታ ያለው የመከላከል ጥረት ለማካሄድ እንደነዚህ ላሉ ወጣቶች ካሉባቸው ችግሮች ለማውጣት ሕብረተሰቡ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ በዚህም መሠረት የተለያዩ አማራጮች መፈጠር አለባቸው፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ህክምናና መልሶ ማቋቋም

ሰዎች በተለያዩ ምክንያቶች አደገኛ መድኃኒቶችና እጾችን በሕገወጥ መንገድ ሊጠቀሙ እንደሚችሉና አላግባብ አጠቃቀም ለተጨማሪ ፍላጎት እንደሚዳርግና ለሱሰኝነት እንደሚያበቃ ግልጽ ነው፡፡ በአለማችን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰወች ለተለያዩ አደገኛ መድኃኒቶችና እፆች ሱሰኝነት መጋለጣቸውን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

በአገራችንም በርካታ ሰዎች ለተለያዩ ማኅበራዊ አደገኛ መድኃኒቶችና እፆች እንዲሁም ለካናቢስና ለመሳሰሉት ሱስ አምጭ ነገሮች መጋለጣቸውን የተለያዩ ምንጮች ያመላክታሉ፡፡ በሱስ የተጠመደ ሰው እሱነቱን ለመድኃኒቱ ወይም ለእፁ አሳልፎ በመስጠት ተገዥ ስለሚሆን በዚህ የተነሳ ከሱሱ በተጨማሪ ሌሎች የጤናና የማኅበራዊ ችግሮች ይደርሱበታል፡፡ ሱሰኛ መሆን አደገኛ መድኃኒቶችና እፆችን ከመጠቀም ሌላ ዓለም የለም እስከ ማለት የሚያደርስ ነው፡፡ ይህ ዓይነት ውሣኔ ላይ የደረሰ ሱሰኛ መድኃኒቶቹንና እፆቹን አግኝቶ ሱሱን ለማርካት ሲል የተፈለገውን እርምጃ ከመውሰድ ወደኃላ አይልም፡፡ በመሆኑም ለሱሰኛው መፍትሔ መፈለግ በጣም ወሳኝ ነው፡፡

## ሀ. ህክምና፣

የአደገኛ መድኃኒቶችና እፆች ሱሰኞችን ከደረሰባቸው የጤና ችግር ለማላቀቅ የሕክምና አገልግሎት ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡ ሕክምናው ሊሰጥ የሚችለው ለአጭር ጊዜ ወይም ለወራት ሊሆን ይችላል፡፡ በሌላ በኩል የሕክምናውን ዓይነትና ጊዜ የሚወስነው የሱስኛው አጠቃላይ ሁኔታ ይሆናል፡፡ የሕክምና አገልግሎት ዋናው ቁም ነገር ሱሰኛው የለመደውን አደገኛ መድኃኒትና እፅ እንዲያቆም መርዳትና ከሱሰኝነት ለመውጣት በሚደረግ ሂደት ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን መቋቋም ማስቻል ነው፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ የተለያዩ የመድኃኒት ዓይነቶች ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡

የሕክምናው ተግባር በስነ አእምሮ ሕክምና ሆስፒታሎች፣ በሌሎች ሆስፒታሎችና ጤና ጣቢያዎች ይሰጣል፡፡ ሕክምናው ለዚሁ ተግባር በሰለጠኑ የጤና ባለሙያዎች የማኅበራዊ አገልግሎት ሠራተኞችና ሳይኮሎጂስቶች /የስነ-ልቦና ባለሙያዎች/ ይካሄዳል፡፡ በዚህ መስክ የሰለጠኑ ባለሙያዎች መኖር አስፈላጊ ነው፡፡

## ለ. መልሶ ማቋቋም፣

ሱሰኛው በሕክምና ተቋማት ውስጥ ገብቶ ለጥቂት ቀናት የመድኃኒት ሕክምና ከተደረገለትና ራሱን ለመቆጣጠር የሚያስችል ሁኔታ ከተፈጠረለት በኃላ በቀጣይነት የመልሶ ማቋቋም እርዳታ ከጥቂት እስከ ረዘም ላሉ ወራቶች እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

መልሶ ማቋቋም ስንል አንድ ሕክምና ያጠናቀቀ ግለሰብ በሱሱ አማካኝነት ያጣውን ችሎታና ስብዕና የተለያዩ የመልሶ ማቋቋም እርዳታ በመስጠት ወደነበረበት የቀድሞ ጤናማ ሕይወት መመለስ ማለት ነው፡፡ ይህም ማለት፡-

- ያልተማረ ከሆነ ትምህርቱን እንዲከታተል፣
- የሥራ ልምድ ከሌለው የተለያዩ የሥራ ዓይነቶች እንዲማርና ብቁ እንዲሆን፣
- ሥራ አጥ ከሆነ ሥራ እንዲያገኝ፣
- ከቤተሰብና ከሕብረተሰቡ ጋር መልሶ እንዲቀላቀል መርዳት/ማስቻል
- ቤተሰብ ከሌለው ቤተሰብ እንዲኖረው ወይም እንዲመሰርት ማድረግ
  ...ወዘተ ማለት ነው፡፡

ሱሰኛው ወደነበረበት የሱስ ሕይወት እንዳይመለስ የመልሶ ማቋቋም እርዳታ ወሳኝ ነው፡፡ ሱሰኛ ው በመልሶ ማቋቋሙ ሂዳት ውስጥ እንዲያልፍ የሚደረገው በርካታ ክህሎቶችን አግኝቶ ራሱን ከሕብረተሰቡ ጋር በማቀላቀልና እንደማንኛውም ግለሰብ ሰርቶ ለመኖር በራስ የመተማመን መንፈስ እንዲያዳብር ለመርዳት ነው፡፡



ከሱስ ነፃ የሆነ ቤተሰብ